እንኳን ደና መጡ


PDF Compressor Free Version

ማንበብ ለህይወት @worldbook0

pdf መፅሐፍትን በቀላሉ የሚያገኙበት የቴሌግራም ቻናል

እንዲሁም ምርጥ ምርጥ ትረካዎችን ያገኛሉ

ይቀላቀሉን ቤተሰብ እንሁን የሚፈልጉትን መፅሐፍ በቀላሉ ያግኙ



PDF Compressor Free Version

ግይፍጠት አየ እንግዳው? ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ ነውና ከሥሩ ላምጣው::"

"እሺ የኔታ ያምጡት" አለ ታሪኩ ፈጠን ፈጠን ብሎ በመናገሩ ራሱን እየወቀሰ::

ግን'ንደር የ'ሕይወት ውኃ' እንዳለች ሁሉ በጎንጅ ደብረ ጥበብም 'ታቦር' የምትባል መወድስ ቅኔ እንደጠል ከሳይ የምታወርድ ውኃ አለች ይባላል:: ታቦር የሚለው ቃል በሁለት ቋንቋ የሚተረጎም ሲሆን በግእዝ "ዘታበርህ ኵሉ" ማለት ነው:: በሌላ ሀገር ቋንቋ ደግሞ 'ታየርያ' ካለው ቃል የተቀነጨበ ይመስለኛል:: ታየርያ ማለት የነፍስ ምሥጢር ማለት ነው:: በትርጉሙ ከተስማማን "ታቦር" ማለትም የነፍስ ምሥጢር እንደማለት ነው:: የጎንጅ ሊቃውንት ግን "ታቦር ከሚቲተ-ምሥጢር" ሲሉ ይገልጧታል:: ቅኔን የምትገልጥላቸው እሷ እንደሆነች ያምናሉ:: ተዋነይ የሚባለው ቅድመ አያታቸው የቅኔ ሰው እንደሆነ ዓለም ያውቀዋል:: አባታቸው ተዋነይ ሊቀ-ሊቃውንት ሆኖ በዓለም የነገሠው ደግሞ ከዚች ውኃ ጠጥቶ ነው ይባላል:: ውኃዋን ሲጠጣ በደመና ተጭኖ ጎንደር ቤተ-መንግሥት እጅ ነሥቶ ጎንደር ውስጥ የሕይወት ውኃን ተጎንጭቶ በደመና ተመልሶ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ጉባኤ ይዘረጋ እንደነበር ይተርካሉ:: በዚች ተአምረኛ ውኃ ተዋነይ እንደአስማተኛ ተቆጥሮባታል:: ምትሐታም ተብሎባታል:: ዐጤ በካፋም ከሐሜት አላመለጡም:: የአስማታመ የተዋነይ ደቀ መዛሙር፣ የባዕድ አምልኮ ተከታይ ተብለው ክፉኛ ጥላሸት ተቀብተዋል:: መልእክ-ነበልባል ተዋነይም ሆነ ንጉሡ ዐጤ በካፋ የታቦር ደቀመዛሙርት እንጂ የሰይጣን

PDF Compressor Free Version
ተከታይ ግን አልነበሩም። ያንን ክፉ ሰም የቀጸለላቸው ጠላት ነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ዕጣ ፈንታ እንዲህ ጎበጣ ከሆኑ ምንጮች ጋር ይዛመዳል። የጎንደርም ሆነ የጎጃም ልዕልና አሁን ከነገርኩህ ምሥጢር ጋር ይያያዛል። ለአብነት ያክል ጎጃምና ጎንደርን አነሣሁ እንጂ ዐራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናትና መልክዐ ምድሮች የዚህ ምሥጢር ባለቤቶች ናቸው። ይህንን ምሥጢር እኔ በሕይወት ሳለሁ ለማንም እንደማታወጠው ተስፋ አደርጋለሁ።" አሉ ሊቁ ፋሪስ።

ከዚያም "ጎንደር እየኖርህ በዚያውም ላይ የቅኔ ተማሪ ሆነህ ስለዚህች ምሥጢራዊት ውኃ አላውቅም ማለትህ ነው?" አሉ ሊቁ ፋሪስ አለማወቁን በደንብ ለማረጋገጥ።

"እመቤቴን! የኔታ ገና ዛሬ መስማቴ ነው!" አለ ታሪኩ እየተቅለሰለሰ።

"ግድ የለም ቀሪውን ወደ ፊት እንነጋገራለን። ቅኔውን በደንብ ቀጽል። ቅኔ ባፍላው ነው እንጂ ነፋስ ከገባበት ውኃ የገባበት ቅራሪ ማለት ነው።" ብለው በግራ በኩል በቀይ ግምጃ ተጠቅልሎ ወደ ተጋደመው ግዙፍ መጽሐፍ አቀረቀሩ።

ታሪኩ ያንን የዋንጫ ጠላ እልም አድርጎ በአንድ ትንፋሽ ጠጥቶ ወደ ጎደው አመራ።

PDF Compressor Free Version

ብቸኛው ጠቢብ ሐረ ትንሽ ቀዝቀዝ ብሰዋል። አልባሌ ልብስ ለብሰው በሐሳብ ከስምነዋል። ጢማቸውን በእጃቸው ወደታች ላማ ላማ እያደረጉ ሊቁ መፅሐፉን ይመለከታሉ።

"ግድ የለም ተስፋ ሳንቆርጥ መቀጠል ነው።" አሉ ሊቅ መፅቁ ትናንት መጽሐፉ የቀሃ ወንዝን ሳያነደው በመቅረቱ ጠቢቡ ሐረ ገጻቸው ሲከፋ ተመልከተው። ቀሃ ወንዝ ተንደግድጎ ነድዶ ቢሆን ኑሮ አስካሁን ሊቅ መፅቁ የልባቸው ደርሶ ጠቢቡ ሐረም ከማየ ሕይወት ጠጥተው ሐሸማል ነበሩ።

"መንደዱስ ይቅር። መጽሐፉ በውኃው ሳይርስ መቅረቱ ለምንድን ነው?" አሉ ጠቢቡ ሐረ።

"እንዲህ አንዳንድ መጻሕፍት ውኃ ውስጥ ሲጥሏቸው ሊርሱ አይችሉም" አሉ ሊቅ መፅቁ ሁለተኛውን መንገድ ለመሞከር እያሰላሰሉ። ሁለተኛውን "የ-ክመ ታእምር" ቀመር ደግሞ አንገረብ ላይ መሞከር እንዳሳባቸው አምነዋል። ከዚያ በፊት ግን የጎንደርን ወንዞች ሲቆጥሩ ሲሰፍሩ ነበር ያደሩት። ቀሃ፣ ማንኪት፣ የፋሲል መዋኛ ገንዳ ወዘተርፈ እያሉ። በእነዚህ ሁሉ ሞክረው ካልተሳካ ባሕረ ቀልቀል ላይም ቢሆን መሞከራቸው እንደማይቀር አምነዋል። ባሕረ-ቀልቀል በአሲምባ አካባቢ የሚገኝ ስፍራ ሲሆን ቅዱሳኑ በአንድ ዋሻ ጠቢባኑ ደግሞ በአንድ ዋሻ የከተሙበት መዝገበ-ቅዱሳን እንደሆነ ታሪኩ ይናገራል።

እነዚህም በምግብ በኩል ከሦስት ወገን ይከፈላሉ።

PDF Compressor Free Version

ጠቢባኑ በቀን አንድ ጊዜ ያውሃሙ በሃሙስት ላይ ኩርማን እንደሌ
ይቀምሳሉ። ስሟንም ሠርሐ-ጎብስት ይሏታል። ከቅድስናና ከተባለ
መምረጥ አቅቷቸው ብቅ ጥልቅ እያሉ ጥበብንና ቅድስናን በመሰማመጃ
ላይ ያሉት ደገሞ ዙቀን ግማሽ እንጀራና በአንዲት የተምር ፍሬ
ራሳቸውን ይቀንሳሉ።

ሦስተኛው ክፍል ክፍሬዉ ሆነ ከሠርክ ጎብስቱ የሉበትም። በመዓዛ ፅዕ
ጠግበው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖሩበታል ሲል ታሪኩ ይናገራል።
ሲት ዐዕቀ ግን እንዲያውም የአቡነ ፊልጶስዘደብረ ቢዘንን ታሪክ ባሕረ
ቀልቀል ላይ እደሣመዋለሁ እያሉ በውስጣቸው ሲፎክሩ ነበር ያደሩት።
ጻድቁ ፊልጶስ የደብረ ቢዘን ገዳም መሠራች ሲሆኑ በተአምር ባሕረ
ቀልቀልን በእሳትእንዳነደዱት ዜና-ንድሳቸው ይናገራል። ጻድቁ በተአምር
ያነደዱትን ባሕር ሊት ዐዕቁ ደግሞ በሐሽሣል መጽሐፍ አንድደው
የአበውን ጥበብ ለዚህ ትውልድ መግለጥ እንዳለባቸው ዝተዋል።
"በውኃ ውስጥ እንደ ዓሣ እየተንከባለሉ ውኃ ሊያረጥባቸው የማይችሉ
መጻሕፍት ከምን ምንም የተሠሩ ናቸው" አሉ ጠቢቡ ሐረ በድንጋጤ።
"በኢትዮጵያ ዕፀዋት ተጽፈው በታብር የተፈተኑ በሙሉ የዚህ
ምሥጢር ባለቤቶች ናቸው። መጻሕፍቱ በየጊዜው የተጻፉ ሲሆኑ
አብዛኞቹቹ ከሊቃውንቱ ጋር መታብር ወርደዋል። ጥቂቶች ግን አሁንም
አሉ። እዚህ በኢትዮጵያ ቀሰም የተጠመሩ ሲሆኑ ውኃ ውስጥ
ተዘፍዝፈው ውኃ አያርሳቸውም። እነሀም መጽያሕተ ባሕር ይባላሉ።
በአማርኛው የባሕር መስታውቶች እንደ ማለት ነው። መስታውት ፊት
ገልያ ከፈት ላይ ያሰ ጉድፍ ልቅም አድርጎ እንዲያሳይ እኒህም

PDF Compressor Free Version

መጻሕፍት በውኃ ውስጥ ያሉ ሥርጥ መንገዶችን በቀያይ ብርሃናቸው ልቅም አድርገው ያሳያሉ። የባሕር መለታውቶች መሳላቸው ከዚህ የተነሣ ነው። በድሮ ጊዜ የጥበብ መጻሕፍቱ በኢትዮጵያ ቀለም በሀገርኛ ሊቅ በሀገርኛ ብዕር ተጽፈው ሲያበቁ ከታቦር ውኃ ውስጥ ይዘፈዘፋሉ። ታቦር ውስጥ ሲዘፈዘፉ ቀለማቸው ቅርፁን ሳይለቅ የታቦርን ውኃ በፈያላቱ ዐይን ልክ ይጠጣል። ከታቦር ደኅና ሲወጡ ፈያላቱ በጣም ጎላ ጎላ ብለው ብርሃን ለብሰው ቀይ መብራት ጎርሰው ይወጣሉ። ከታቦር ደኅና ከወጡ ወደ ሕይወት ውኃ ይሳላሉ። በሕይወት ውኃ ድጋሜ ሲዘፈዘፉ ቀለማቱ በዚያው ጸንተው ድጋሜ ግዘፍ ይነሣሉ። ከዚያም በእኒህ መጻሕፍት ብርሃን እየተመራ በባሕር ውስጥ መንሳቀስ ለፈለገ ባሕሩ ውስጥ መንቀሳቀስ ይችላል። ይህንን መንገድ ጠቢቡ ትልቁ አስክንድርም ሞክሮት ነበር ይባላል።" አሉ ሊቅ ዐፅቁ።

...ይህንን ብለው አንገረብ ሲደርሱ ታሪኩም አበቃ። እንደ ተለመደው መጽሐፉን ወደ አንገረብ ሲጥሉት አንገረብ ላይ የብርሃን ፍንጣቂ ተረጨ። ባሕሩ የተቃጠለ መስሏቸው ሊቅ ዐፅቁ በደስታ ዐይናቸውን ጨፈኑ። ጥቂት ቆይተው ሲገልጡ ግን የባሕሩ ጸዳለ-ብርሃን ከመጽሐፉ ጸዳለ-ብርሃን ጋር ሲዋሐድ የተፈጠረ ብልጭታ እንጂ ባሕሩ ነድዶ በውስጡ የሕይወትን ውኃ ማስገኘቱ አልነበረም። ሊቅ ዐፅቁ በሁኔታው ተበሳጩ። ጠቢቡ ሐረ ግን ይህንንም እንደ አንድ ፍንጭ ቆጥረውት ፍሥሓቸው በፊታቸው ላይ ተረጨ። በዚህም እንደ ተለመደው ፍንጭት ጥርሳቸውን ፈንጭተው ሳቅ አሉ።

PDF Compressor Free Version

፳፫

ሃንጅ መገረቱ ሌሊት

ታሪኩ ከሊቁ ቤት ራት በልቶ ጠላ ጠጥቶ እንደተመለሰ ከቶማስ ጎ
ሲገባ ገሞራውና ቶማስ ጥሬ እየቆረጠሙ ያወጋሉ። ታሪኩ ወደ ጎጆው
እንደገባ በዝምታ ተውጦ ስለ ጎንደር ውኃ ያወጣ ያወርድ ጀመር።
አእምሮው በሐሳብ ወደ ጎንደር ሰገረ። ሰሜን ጎንደር ገባ። ከዓመታት
በፊት ትልቋ ጎንደር ውስጥ ለሴቶች ውኃ በጀራካ እየቀዳ የሰሉት ራት
እያገነ ቅኔ ተምሯል። በወርሃ ወራቱ አድባራት እየተዘዋወረ መወድስ
ዘርፏል። ጎንደር ላለ የሕይወት ውኃ ነገር በገለጥለት ኑሮ በአጎታ
መወድስ መዝረፉ የማይቀር ጉዳይ ነበር። እረ እንዲያም ሐረንም ሆነ
ፋሪስን ቀድሞ ሐሽማል ሊሆንም ይችል ነበር።

"ተጫዎት እንጂ ታሪኩ?" አለ ገሞራው ከቶማስ ጋር ትንሽ ሲጫዎት
ቆይቶ።

"የራስ ምታት ነበረችብኝ ተነሥታ ረበሸችኝ" አለ ታሪኩ የምሩን እየሳቀ
ሲቀ ፋሪስ የገነሩት የሕይወት ውኃ ምሥጢር ራሱን አዙሮት "ወይ
ሀገሬ! ወይ ኢትዮጵያ! ወይ ጎንደር! ብለሽ ብለሽ ደግሞ የሞት
መድኃኒት ማብቀል ጀመርሽ?" እያለ በውስጡ።

"ስመሆኑ የየኔታ የራት ድግስ እንዴት ነበር?" አለ ቶማስ።

"ጠላው አንዱ በቃኝ ነው! እንደጉድ ጨለጥሁት። ድግሱም በጣም
ተስማምቶኝ ነበር! ድግሱን ተከትሎም አንዳንድ ምሥጢር አወራኝ
ራሴ ላይ የወጣ ያ ይመስለኛል።" አለ ታሪኩ።

"ምንድን ነው?" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

ምሥጢሩን ለማወቅን ያስቸኩል። ከየኔታ አንደበት ባይወጣ ኑሮ ከመጨናነቅ አልቆጥረውም ነበር። የኔታ ሲናገሩት ግን አዲስ ስሜት ፈጠረብኝ።"

"ምንድን ነው እሱ! እኛ መስማት አንችልም እንዴ?" አለ ቶማስ

"ይቻላል"

"እንግዲያማ ንገረንና እንወያይበት።"

ታሪኩ ቀጠለ።

"የኔታ ማለት የቅኔ ሰው ብቻ አይደሉም። ራሳቸው ቅኔ ጭምር ናቸው። ከቅኔው ጎን ለጎን ረቂቅ ጥበብ ናቸው። ሰምና ወርቅ ቅኔ እየዘረፉ ራሳቸው ግን ቅኔ ሲገልጣቸው የማይችል ግሩም ሰምና ወርቅ ናቸው። ከላይ ከላይ ሰም ብቻ። ከውስጥ ደግሞ ድብቅ ሰምና ወርቅ። ሰሙ በሰም፣ ወርቁ በወርቅ ተደብቆ ይኖር ነበር። ዛሬ ግን ተገለጠ።"

"እንዴት ስትል?" አለ ገሞራው

"ቅድም ከዚያ ሁሉ ተማሪ መርጠው ቤታቸው ጠሩኝ። ጥቂት እንደ ተጨዋወትን ጎንደር እንዴት ናት አሉኝ። ደህና ናት አልኳቸው። የኢትዮጵያ መልክዐ-ምድር በጥበብ የታጠረ ነው። ሉል ዝባድ፣ ተንከራ ዘኢትዮጵያ ከሚባሉት የወርቅና የብር ዐይነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ወንዞች ደግሞ የራሳቸው ምሥጢር አሳቸው አሉኝ።" ብሎ ወደ ጎንደር ውኃ ምሥጢር እሄዳለሁ ሲል

'ይህንን ምሥጢር ለማንም እንደማታወጣው ተስፋ አደርጋለሁ' ብለው ሲቁ ያስጠነቀቁት ትዝ ሲለው ሐሳቡን ወደ ውስጥ ዋጠና ዝም አለ።

"ታዲያ ይህ ምሥጢር ስራስ ምታት ይዳርጋል እንዴ? አልል ያሰኛል እንጂ" አለ ገራገሩ ቶማስ።

PDF Compressor Free Version

"አይደለም አይደለም ማመን የተሣነኸ የተንከራ ዘኢትዮጵያ ምሥጢር ነው።" አለ ታሪኩ።

"ያም ቢሆን እኮ ቀላል ነው። ኢትዮጵያ ምሥጢራዊት ሀገር ናት። በውስጧ "ተንከራ ዘኢትዮጵያ" ቀርቶ የሕይወት ውኃ፣ የሕይወት ዛፍ፣ ቢኖሩ ምን ክፋት አለው። የኢትዮጵያ መልክዐ ምድር አፈር ምሥጢር አዘል ደሰል ነው። ጥቁር አፈር ብቻ አይደለም። ይህንን ሊቁ ተርቶ እኔ እግረ ተማሪውም ብሆን አውቃለሁ።" አለ ገሞራው።

"ሰሁሉም ሰላም እደሩ" ብሎ መጽሐፉን አጥፎ ወደ ቆጥ አልጋው ሲወጣ "አሁን ጀምረህ አትተኛ ይጫንኻል ይልቅስ ቁጭ በልና ቅኔ እንዴት እንደገለጠልህ አውራን። ወግህ ይመስጣል።" ገሞራው በሀይት ተማፀነው።

ታሪኩ ምን ገድደኝ ብሎ ማውጋት ቀጠለ።

"ከትውልድ መንደሬ ስጀመር ሀገሬ ላይ ጋይንት ደራ መስቀል ነው። ከሊቃውንት ሀገር ጎንደር መፈጠሬን እንደ ዕድል አቆጥረዋለሁ።" አለ ታሪኩ።

ገሞራው እንደ ተለመደው በደንብ ለመስማት ዐይኖቹን ጨፈነ።

ታሪኩ ቀጠለ።

"ጎንደር ተወልጀ በተለያዩ ገዳማትና አድባራት ተዘዋውሬ ተምሬያለሁ። በከፊል ጎንደር ባሉ አድባራትና ገዳማት ተዘዋውሬ ብዙ ትምህርት ቀስሚያለሁ። ከዚማ ቤት፣ ከቅኔ ቤት፣ ከአቋቋም ቤት፣ ስዘዋወር ነው የኖርሁት። ባለተራ ጲያቆን ሁኜ ዜማ በመማር ላይ ሳለሁ ወደ ሦስት ደብር አዳርሻለሁ። ከጋይንት ተራሮች ጥበብ ለጥቻለሁ። ደራ መስቀል፣

PDF Compressor Free Version

ነፋስ መውጫና ምንጭ ውኃ ሚካኤል ሲሉትም የእውቀት አድማሱ ናቸው። ከአናቱ ስጀምር ወደ ትምህርት ዓለም የመጣሁት ገና ለጋ ለለሁ ነው። የፊደል መምህራ ቀለመ ወርቅ ይባላሉ። አረጋዊ ሲቅ ነበሩ። ፊደል ስጀምር ጉበልነቴን አይተው 'ይህ ገና ለጋ ነው! ለምኖ መብላት፣ ቀለም መቀበል አይችልም። ለምን አመጣህብኝ?' ብለው ከአትቴ ጋር ጠብ ፈጠሩ። አንቱ ኧረ ይችላል? ትልቅ ነው? ብሎ በሐፍረት ፊቱን አዞረ። እንደ ምንም አሳምኖ ከፊደል ቤት ጥሎኝ ወደ ቤቱ ተመለሰ። በማልስቱ ሰኞ ዐቢይ ጾም ተጀመረ። መምህሩ እኔን ጨምሮ ከዐሥር ዓመት በታች አድሜ ጥላ ሥር ያለን ጉብላሊቶቹን ስብስበው 'እናንተ ገና በለጋ እድሜ ሥር ናችሁ። እስከ ዘጠኝ ሰዓት ለመጾም አትሞክሩ። ለጊዜው እስከ ስድስት ሰዓት ይበቃችኋል። ቀሪውን ጊዜ እኔ እጾምላችኋለሁ' አሉን። ደስ ብሎን ጉልበታቸውን ሳምናቸው። መልሰው ግንባራችንን ላሙን። በዚህ ተስማማን። ሊቁም ለራሳቸው እስከ ዘጠኝ ሰዓት ጹመው፣ የእኛን ፈንታ ደሞ የሦስት ሰዓት ጾም ይጨምራሉ። ዛሬ አድጌ ሳሰላስል ይህ ስብእናቸው የመምህሬን ትልቅነት ያስታውሰኛል። በትክክል እንቍ መምህር ነበሩ።" ታሪኩ ይህንን ብሎ የፊደል መምሩ ቀለመ ወርቅን አስታወሰ።

ሕፃናትን ስብስበው ፊደል ያስቆጥራሉ። እንዳለፉ ሊቃውንት እሳቸውም በሕሳቤ በኩል የታደሉ ባለሀብት አልነበሩም። ደመወዛቸው ደረቅ መሬት ናት። ደረቅ መሬት እየጫሩ፣ የሀገር ባለውለታ ሊቅ ነበሩ። ጠላያቸው ደግሞ የሚገርም። ቁጣ ብሎ ነገር አይነካካቸውም። ከዓመት ዓመት እንደምሰሶው ተተክለው ፈጣሪን ያገለግላሉ። በሀገሩ ዘንድ 'ድርብ ታቦት'

PDF Compressor Free Version

በመባል ይወደሳሉ። መንደርተኛው በሙሉ አክባሪያቸው ነበር። ቅዳሜ ቅዳሜ መጣፍ ዘርግተው ይመለከታሉ። በሰንበት ቀን የታመመ ይጠይቃሉ። የሞተ ይቀብራሉ። ለተማሪዎቻቸው ምሥጢረ ሥላሴን ያስተምራሉ። 'ኢትዮጵያ የምሥጢር ሀገር ናት። ተመርምሬ አትዘለቅም' እያሉ ሬት ለሬት በተነሰነሱ ተማሪዎቻቸው አእምሮ ውስጥ የሀገር ፍቅር በመርፌ ይሰፉ ነበር። ታሪኩ ይህንን ውስጥ ውስጡን ሲያነሳ ቆይቶ ቀጠለ።

"ከየኔታ ቀለመ -ወርቅ ንባብ ቤት ሳለን በአንድ ማዕድ ስምንት ሆነን እንበለፍ ነበር" አለ ታሪኩ ወደኋላ ተመልሶ።

ገሞራው ምርጥ ምርጥ ታሪኮቹን በውስጡ እየመዘገበ ዐይኖቹን እንደጨፈነ ማዳመጡን ቀጠለ።

"ከስምንቱ ተማሪዎች ዐራታችን ገና ጉበል ስለነበርን ከውሻ ጋር ታግለን ማሸነፍ ዐቅም አልነበረንም። ስለዚህ ዐራቱ ውሻ ሲከለክሉ ዐራታችን ደግሞ ረዳት ሆነን አኮፋዳችንን በቀበቶ ማንገቻ አዝለን፣ ወደመንደር ሂደን "በእንተ ስማ ለማርያም" እንላለን። በጊዜ ያበሰለ የበሰለ ድንችና እንጀራ ይሰጠናል። ያላበሰለ አላበሰልሁም ሲል፣ ጥሬ ይዘከሩን ብለን እንቆማለን። እናቶች ጥሬ ድንቹን በቁና አፍሰው ይዘከሩናል። ያን መስደን ገሚሱን በሸክላ ቀቅለን እንበላዋለን። የቀረውን ሽጠን ሐመልማ ዝያ በርበሬ እንሸምትበታለን። ከበርበሬ የተረፈውን ደግሞ እንሶላ በክንድ ተከንድቶ እንገዛበታለን። አንሶላዋን ለብሰን እንደጉንዳን እንተጋለን። ምሽት ምሽት "በእንተ ማርያም" እያልን ከአንዱ መንደር ወደ ሌላኛው መንደር ከአንዱ በራፍ ወደ ሌላው በራፍ ስንሸጋገር ጸሎተ

PDF Compressor Free Version

በመባል ይወደሳሉ። መንደርተኛው በሙሉ አክባሪያቸው ነበር። ቅዳሜ ቅዳሜ መጣፍ ዘርግተው ይመለከታሉ። በሰንበት ቀን የታመመ ይጠይቃሉ። የሞተ ይቀብራሉ። ለተማሪዎቻቸው ምሥጢረ ሥላሴን ያስተምራሉ። 'ኢትዮጵያ የምሥጢር ሀገር ናት። ተመርምሬ አትዘለቅም' እያሉ ሬት ለሬት በተነሰነሱ ተማሪዎቻቸው አእምሮ ውስጥ የሀገር ፍቅር በመርፌ ይሰፉ ነበር። ታሪኩ ይህንን ውስጥ ውስጡን ሲያነሳ ቆይቶ ቀጠለ።

"ከየኔታ ቀለመ -ወርቅ ንባብ ቤት ሳለን በአንድ ማዕድ ስምንት ሆነን እንበለፍ ነበር" አለ ታሪኩ ወደኋላ ተመልሶ።

ገሞራው ምርጥ ምርጥ ታሪኮቹን በውስጡ እየመዘገበ ዐይኖቹን እንደጨፈነ ማዳመጡን ቀጠለ።

"ከስምንቱ ተማሪዎች ዐራታችን ገና ጉበል ስለነበርን ከውሻ ጋር ታግለን ማሸነፍ ዐቅም አልነበረንም። ስለዚህ ዐራቱ ውሻ ሲከለክሉ ዐራታችን ደግሞ ረዳት ሆነን አኮፋዳችንን በቀበቶ ማንገቻ አዝለን፣ ወደመንደር ሂደን "በእንተ ስማ ለማርያም" እንላለን። በጊዜ ያበሰለ የበሰለ ድንችና እንጀራ ይሰጠናል። ያላበሰለ አላበሰልሁም ሲል፣ ጥሬ ይዘከሩን ብለን እንቆማለን። እናቶች ጥሬ ድንቹን በቁና አፍሰው ይዘከሩናል። ያን መስደን ገሚሱን በሸክላ ቀቅለን እንበላዋለን። የቀረውን ሽጠን ሐመልማ ዝያ በርበሬ እንሸምትበታለን። ከበርበሬ የተረፈውን ደግሞ እንሶላ በክንድ ተከንድቶ እንገዛበታለን። አንሶላዋን ለብሰን እንደጉንዳን እንተጋለን። ምሽት ምሽት "በእንተ ማርያም" እያልን ከአንዱ መንደር ወደ ሌላኛው መንደር ከአንዱ በራፍ ወደ ሌላው በራፍ ስንሸጋገር ጸሎተ

PDF Compressor Free Version

ማርያምን አናስቀድማለን። ይህ የተማሪ የግል ጸሎት ነው። መቼም ከመንደር ስንደርስ ዘው ብሎ መንደር መግባት የተከለከለ ነው። ከመንደሩ ስንደርስ "ጸሎተ ማርያምን" ጸልየን በጌታችን አምላክ ጸሎት በእቡነ ዘበሰማያት አሳርገን ወደ መንደር እንገባለን። የሕይወታችን ዋስትና ጸሎቱ ነው። ጸሎቱ ከደዌ፣ ከውሻ ጥርስና ከሰካራም ዱላ ይጠብቀናል። ወዲህም ስክርም ሆነ ሳይሰክር፣ መኖሪያ አመለካከት ካለው ሰው ይጠብቀናል። ምን አልባት በመንደሩ ኃይለኛ ውሻ ካለ መፍዘዝ መደንገዝ እንዳሆነን ይመስለኛል። በእርግጥ በጸሎቱ ተጠቅመንበታል። ጸሎቱ ያው የሱቃስ ወንጌል ነው። አመቤታችን የተናገረችው ትልቅ ጸሎት ነው። ይህንን ጸሎት አበው በአመቤታችን እድሜ ልክ ስልሣ ዐራት ጊዜ ይጸልዩት እንደ ነበር ከየኔታ አንደበት ከሰማንበት ቀን ጀምሮ፣ ዘወትር ወደ መንደር ስንሄድ እንጸልየው ነበር። እግዚአብሔር በጸሎቱ ከፈንጣጣና ከኩፍኝ በሽታዎች ጠብቆናል። ከሸፍታ ሳይቀር ጠብቆናል።

ከዜማ ቤት ወደ ቅኔ ቤት ነው ቀጥታ ያመራሁት። ቅኔን የጀመርክ'ትም ሆነ እስክ ቅኔ ዘራፍነት ደረጃ የደረስሁ ጎንደር ደብረ-ብርሃን ሥላሴ ነው። ደብረ ብርሃን ሥላሴ የቅኔ ጀማሪ ሆኜ ገባሁ። በቅኔ ቤቱ እንደ እኔ ልመና የሚጠላ ተማሪ አልነበረም። ጎደኞቼ ልመና እንሂድ ሲሉኝ እሺ ብዬ አብሬ እወጣለሁ። ከመጀመሪያው ቤት "በእንተ ስማ ለማርያም" ብዬ እጀምርና ወዲያኑው ከጎደኞቼ እደበቃለሁ። እነሱ እየለመኑ ከብልኮ ሰፈር ወደ አባጃሌ ተክለ ሃይማኖት ይወርዳሉ። ቅዳሜ ገቢያ ድረስ አልፈው እየለመኑ በቲርቱስ በኩል

PDF Compressor Free Version

አድርገው በቅዱስ ሩፋኤል ቤታቸ እየሰመኑ በአንገረብ ወንዝ ዙሪያ
ያለውን ዐርባዕቱ አንበሳ ቤተክርስቲያንን ወደቀኝ እየተጠ ወደ ደብረ
ብርሃን ሥላሴ ቅኔ ቤት ይመጣሉ። እኔ መዲያውኑ ወደ ቅኔ ቤቱ
ተመልሸ ግስ ሳጠና አመሸና ወደ ዕሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ
ለጎንደር እናቶች ውኃ በጀሪካ እሸከማለሁ። እነሱ ፒያሳ መርቅ ሲሸጡ
ውለው በጣም ስለሚደክማቸው ውኃ መቅዳት ይለለቻቸዋል። እኔ ሁለት
ሦስት ጊዜ ተመላልሸ ውኃ በጀሪካ ስቀዳላቸው የዕለት ምግብ እንጀራና
በርበሬ ይሠጡኛል። ለሌላ ጊዜ ደግሞ ኮቾሮ አድርቀው ይጠብቁኛል።
እንደልማዴ በጀሪካ ውኃ ሳጉዝ ሳጉዝ፣ አምሽቼ ደረቄን ኮቾሮ በለስፋዳ
አንጠልጥዬ ወደ ቅኔ ቤቱ ሙልት እያልሁ በቅኔው ገፋሁበት። ትንሽ
ቆይቼ በቅኔ በኩል እየበረታሁ ሄድኩ። በወርባ ዐራቱ ያሉ ሊቃውንት
በመሉ በየኩበረብኃሉ ቅኔውን ሰኔ እየሰጡኝ ወርባ ዐራቱን አድባራት
እየዞርሁ በቅኔ አረሰረስካቸው። ቢኋላ ግን ወርባ ዐራቱን አድባራት
እየተዘዋወርኩ ቅኔ መዝረፉን አቁሜ ከዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ
የደመራና የጥምቀት በአደባባይ ቅኔ መስጠት ጀመርኩ።" አለ ደማሙ
ሊቅ ታሪኩ።

"ቅኔ በጀመርህ በስንት ዓመት የቅኔ ዘራፊ ሆንህ?" አለ ቸሩ ቶማስ።

"ባሙቱ!" አለ ታሪኩ።

"እንዴት ቆናህ እኔ ባሙቴ ዋዜማ አንካ ሳልደርስ?" አለ ቸሩ ቶማስ። ወደቅኔ ዘረፋው ታሪኩ ስመጣ "ከምንጭ ውኃ" ጋር የተያያዘ ትልቅ ትዝታ አለኝ።" አለ ታሪኩ።

"ምን ትዝታ?" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

ዝቅኔ በኩል ብዙ አልደከምሁም ሲል ጀመረ ታሪኩ።

ዝቅኔ በኩል ብዙ አልደከምሁም። ዝም ብሎ ነው የተገለጠልኝ ማለት አትላለህ" አለ በድጋሜ።

"እንዴት ያለ ድካም ተገለጠልኝ ስትል?" ገሞራው ሰፍ ብሎ ጠየቀው።

"በእምነት የጠጣሁት ምንጭ ውኃ ነው እንዲህ ሊቅ ያደረገኝ ታሪኩ በአጭሩ መለሰ።

"የምን ምንጭ?" አለ ገሞራው።

"ነገሩማ ልጅ እያለሁ ነው። ልጅ እያለሁ ብዙ ብዙ ነገር እሞክር ነበር። ከሞከርኩት አንዱ የምንጭ ውኃ ሚካኤል ምንጭ ነው። ምንጩ ሲጠጡት እሸት እሸት የሚል ውኃ ነው። ላይ ጋይንት ዙር አምባ አሻጋሪ ይገኛል። ተወልጄም ያደኩት ከዚሁ ታሪካዊ አካባቢ ነው። እናም ልጅ እያለሁ አንድ ትኩስ ወሬ ሰማሁ። ደራ-መስቀል ሳለሁ ላይ ጋይንት ውስጥ "ምንጭ ውኃ" የሚባል ምንጭ አለ። የውኃው በሮች በግንድ ተረብርበዋል። ውኃዋ በጠፍጣፋ ድንጋይ ተገጥማለች። ሲከፍቷት ውኃዋ የጠራ ሰማይ ይመስላል። ሲጠጧት እሸት እሸት ትላለች። በዚህ በኩል የሚያልፍ ሰው ምንጯን የቅዱስ ያሬድ ጠበል አያለ ስፌ ታሪኳን ይናገራል። ይዘክራል።

ምንጯን ቅዱስ ያሬድ ከዙር አባ ተነሥቶ ወደሲሳየ-ዳውንት ሲያልፍ የጠጣት ምንጭ ናት። በዚህ ቦታ ላይ "አውነዘ ለመ. ማየ ሕይወት ዘትረ-ኩኩሕ ፈልፈለ-ነቅዕ ዘኢይነጽፍ" ብሎ ዘምሮባታል። ትርጉሙም የሕይወትን ውኃ ሰጣቸው፤ ከጭንጫ ላይ ማር አፈለቀላቸው። የማይነጥፍ ውኃ አፍልቆ አጠጣቸው" ማለት ነው። ደራሲው ይህንን

PDF Compressor Free Version

መዝሙር የዘመረው ወደሲሳየ-ዳንዉት ሲያልፍ ምንጭ ውኃ ላይ ቁጭ
ነበር። ዛሬ ድረስ ይህ ስፍራ ምንጭ ውኃ ሚካኤል ተብሎ ይታወቃል።
የሕይወት ውኃ መሆኑን ግን ተመራምሮ የደረሰበት ጠቢብ ያለም።
ወደፊት ግን ተመራማሪ ይጠበብባታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ምንጩን
በምሥራቅ በኩል ቤተ-ልሔም፣ በምዕራብ ጉና ተራራ፣ በደቡብ የጉላ
ገደባ፣ በሰሜን ሸየኖ ተራራ፣ የከበባት ምንጭ ናት። የቤተ-ልሔም
ሊቃውንት ወደ ሰዓሊ ገቢያ ሲወጡ ወደቤተ-ልሔም ሲወርዱ ውኃዉን
ተንጭተው፣ ማንባራቸውን ተቀብተው ያልፋሉ። በዚህ ጊዜ እድለኛ
ለሆነ ሰው ምሥጢር ይገለጽለታል ሲባል ሰማሁ። ለእኔም ትምህርቴን
ይገልጥልኛል። አድሌን ልምክር ብዬ ወደ ምንጭ ውኃ ሄድኩ። ከውኃዉ
ስጠጣ እሸት እሸት አለችኝ። ጥቂት ቆይቶ ሰማይ ብልጭ አለብኝ።
የቆምኩበት ጠፋብኝ። በነጋው ስነቃ አእምሮዬ ቀለም ለመቀበል ስል ሆኖ
አገኘሁት። ከዚያም ወደ ቤተ ልሔም መጓዝ ጀመርኩኝ። ቤተ-ልሔም
ልደርስ ጥቂት ሲቀረኝ የተማሪዎች ጎጆ ከሚዳ ላይ የሬሰሰ ዝንጀሮ
መስሎ ታየኝ። ሊቃውንቱ በቀለም ይፋለማሉ። ተማሪው ይጠይቃል።
መምህሩ ይመልሳሉ። ከዚህ ማዕረግ ለመድረስ ሰላም ለአ ብዬ ድጓውን
ጀመርኩ። በእምነቱ ላይ የምንጭ ውኃ ኃይል ተፈጠምሮልኝ ነው
መሰለኝ የቀለም ዘር አሳቆመኝ አለ። ድጓውን እንደ ምንጭ ውኃ ፉት
አልኩት። የረድም ዓመቱን ትምህርት በአጭር ጊዜ ጨረስኩ።" አለ
ታሪኩ ታሪኩን አየዘከዘከ።

"ምንጭ ዛሬም ድረስ አለች?" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

"እንዴታ! አለች እንጂ። ዛሬም አንዳንድ የአዲስ አበባ ሲቃውንት ከረጅም ጊዜ በኋላ ድጓው ሲጠፋባቸው፣ ወደዚች ምንጭ እየዘለቁ ይጠጣሉ ይባላል። እድሉ የሬዳው የጠፋው ይመስለኛል። የገደፈው ይመጣለታል። ሌላው ደክሞ ይመለሳል። ለእኔ ግን ቅኔን ጭምር የገለጠችልኝ ይመስለኛል። በወቅቱ ውኃዋን ስጠጣ ቅኔ የማወቅ ፍላጎቴ ከባድ ስለ ነበረ ቅኔ ስጀምር ወዲያው ነው እሳት የላሰ ባለቅኔ ለመሆን የበቃሁት። ከምንጭ ውኃ ጋር ይህንን የመሰለ ትዝታ አለኝ።" አለ ታሪኩ።

ከዚያም ቀጠለ።

"በእርግጥ ከዚያ ወዲህ ድጓውን ከስመ-ጥር ሊቃውንት በተደጋጋሚ ተምሬዋለሁ። ዐመሉን ጠንቅቄ አውቄዋለሁ። ከጓደኞቼ ጋር ከጋይንት ተነሥተን ወዲህ ወደ ጎጃም መጥተን ባሕር ዳር ጊዮርጊስ በድጋሜ ዜማ ጀመርን። በዚህ ጊዜ የባሕር ዳር ጊዮርጊሱ የድጓ መምህር ዳግም በእውቀት ፈጥረውኛል። ድምፄም በዜማ የታሸው ከዚሁ ዜማ ቤት ነው። መምህሩ በፍቅር ጆሮዬን ይዘው በቁንጥጫ ያልመዘምዙኛል። የፍቅራቸው መገለጫ ያ ነው። የባሕር ዳር ጊዮርጊሱ መምህረ-ድጓ ከሊቅ በላይ ሊቅ ናቸው። ዜማውን እንደሳቸው የያዙ ፍሬ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። ከዜማው ሁሉ ላቅ ያለ ትምህርት "አንቀጸ" የሚባል የዜማ ቀለም አለ። ዐመሉ ከባድ ነው። ዜማው በጣም ያደክማል። የባሕር ዳሩ መምህር ግን ከማንም ሊቅ በላይ አላምጠው በልተውታል። 'አንድ አንቀጽ ከጠፋኝ መኪና ይነዳብኝ' እስከማለት ደርሰው በራሳቸው ላይ የሞት ውርርድ ይወራረዳሉ። ውርርዳቸው ሲበዛ ሊቅነታቸውን እንጂ

PDF Compressor Free Version

ትዕዚታቸውን አይገልጥም። ሊቅነታቸውን አስተዚህ ድረስ ደርሰው ያምነበታል። ወዲህም እንደሌሎች መምህራን አይደሉም። ሌሎች ይዘነ ቢኖራቸው የተራቀቀ ድምፅ ላይኖራቸው ይችላል። የባሕር ዳር ጊዮርጊሱ መምህር ግን እኔን አነሳሱ! ድምፃቸው ድምፀ-መረዋ ነው። እንደ ሰልአሮድዮን ደስ እያላቸው የራሳቸውን ድምፅ በተመሰጠ እያዳመጡ ይጮኻሉ። ይዘታቸውም እንዲሁ ነው። ማንሴት ሲቆሙ ድምፃቸው እንደመረዋ ያገርራል።" ታሪኩ የልጅነቱ ዘመን ውል አሰበት። "እልአሮድዮን ደግሞ ምንድን ነው?" አለ ቶማስ።

"የወፍ ዝርያ ነው። ወፉ የራሱን ድምፅ ሲሰማ ራሱ ይደሰታል። በጣም ደስ ሲለው ብቻዉን እየዘመረ ሲበርር ሲበርር ቆይቶ ቀጥ ብሎ ይቁማል። ከዚያም መዘመሩን ይቀጥላል። ዝማሬውን ሲሰማ ምግብ እስክ መብው ይደርሳል። በዚህ ጊዜ ሰውነቱ ደክሞ ጠጉሩ በንኖ ይሞታል" አለ ታሪኩ ከጥንት ፈላስፎች መጽሐፍ ያነበበውን አያስታወሰ። የእኔ መምህርም የራሳቸው የሆነ የዜማ ስልት አላቸው። እንደ እል-አሮድዮን ደስ። ታዲያ ይህንን ሲያዜሙ በአንድ እጃቸው ጸናጽል እያቃጨሉ በሌላ እጃቸው የከበሮ ምት ለተማሪዎቻቸው ያስለምዳሉ። እኔም ከበሮ መቆርቆር የተማርኩት ከእግራቸው ሥር ቁጭ ብዬ ነው። መጀመሪያ የራሳቸውን ድምፅ በተመሰጠ ሲሰሙ ስናይ የአብነት ነገር ይመስለን ነበር። ነገር ግን የአብነት ጉዳይ አይደለም። ድምፀ-መልካም ስለነበሩ የራሳቸውን ድምፅ ዞር ብለው የሚያዳምጡት ቀሰሙ እየሳባቸው ነው። ቀስ ብሎ ሲገባኝ እንደ ወፉ በራሳቸው ድምፅ እየተማረኩ ነበር። በእርግጥ "ምንጭ ውኃ ይጠጡ አይጠሙ የተረጋገጠ

PDF Compressor Free Version

ነገር የለም። ወዲያው ብጥስ ግን ቤተ ልሔም ድንኳን ለማስመስከር ሲሄዱ እንደጠሉ አጥብቆ ያምን ነበር። እኔ አላመንኩም። የተፈጥሮ ጸጋቸው ነው የሚመስለኝ።" ተሰናብቷቸው ጋደም አለ። እንቅልፍ ግን ሊመጣለት አልቻለም። ሰለ ጎንደር ውኃ ሲያወጣ ሲያወርድ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከእንቅልፍ ጋር ተፋታ።

PDF Compressor Free Version

፳፯

ታሪኩ አንቅልፍ ባጣ በሦስተኛው ቀን ሊቁ ሩፋሰ የሊቅነት ክሔ አያስመ ወደ ቅኔ ቤቱ ዘለቁ። ከታሪኩ ጎጀ ፊት ለፊት ሲደርሱ ጥላቸው ከወደው። ቀና ሲል ሊቁ ከአጠገቡ ደርሰዋል። ብድግ ብሎ እ ነግ።

ሊቁም ሰላምታውን በትሕትና ተቀብለው እንዳበቁ "ቅኔ ቤቱ ሞል ብሏልሳ? ተማሪው ሁላ ወዴት ሄደ?" አሉ። "በያቅጣጫው ተበትኗል ወደ ዝያም ወደ ልመናም የሄደ ይመስለኛል።" አለ ታሪኩ "ሽጋ ነው!"

"አንተስ ጎዳይ የለኽም?"

"የዛሬ እቅዴ ግሰ መመልከትና ክሰንት በኋላ ደግሞ ወደ መንዝ ወርጄ ገሳጩን መታጠብ ነው።" አለ ታሪኩ።

"ደግ አድርገኻል። በል እንግዲያው ከኔ ጋር ትንሽ ቦር ዞር እንበል" ብለው ወደ ትልቁ ዋርካ አለፉ። ታሪኩ መጽሐፉን በዕልባት አስተካክሎ ተከተላቸው።

ቅኔ ቤቱን እየዞሩ ሳለ "ከለፈው ሳምንት መወድስህ ውስጥ ብዙ ኮርኒሪ ነገሮች ነበሩት። ለመሆኑ ወደዚህ ሀገር ለመማር ከመምጣትህ በፊት ስለ አባቱ ስለ ድንቁ የምታውቀው ነገር ይኖር ይሆን?" አሉ ሊቁ።

"አዎ! ከቅድመ አያቱ ጋር የተያያዘ ትንሽ ወሬ ሰምቼ ነበር" አለ ታሪኩ።

"ምን ነበር የሰማኸው?" አሉ በከበሬታቸው ከዋርካው ሥር የረገፉ ቅጠሎችን እየሰበሰቡ።

PDF Compressor Free Version

ጭሰም ቅድመ አያቱ ከአሰቃ ድንቱ ጋር በጎንደር ውስጥ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ተምረዋል። በጎንደር መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ሐዲስ ዲያን አጥንተዋል። ከቀለም ትስስር የዘለለ የምሥጢር ሰንሰለትም እንደነበራቸው ሰምቻለሁ። ወደ ርስም ያመጣኝም ያ ነው።" አለ ታሪኩ።

"ምግቸው ማን ይባል ነበር?"

"ኖላዊ"

"የሰማዕቱ ኖላዊ የልድ ልጅ ነኝ እያልህ ነው?" አሉ ሊቁ።

"ቀለም ቅድመ አያቱ ናቸው።"

"በዕረፍታቸው ጊዜ አባቱ ድንቁ ጎንደር ነበሩ። ስመሆኑ ከወዴት እንዳረፉ ታውቃለህ?" አሉ ሊቁ

"ከወዴት እንዳረፉ አላውቅም። ጎንደር እንደ ተቀበሩ ግን አውቃለሁ።" አለ ታሪኩ።

"ክብረ ልጄ! በትንሽ እድሜህ ብዙ ነገር ቀስመኻል!" አሉ ሊቁ ዋርካውን በደንብ እየተደገፉ።

"ሊቁ ያረፉት ጀርመን ሀገር ነው ሲሉ ጀመሩ። ያረፉት ጀርመን ሀገር ነው። ወደ ጀርመን ያመሩት ደሞ እንደ ዛሬ ዘበኑ ፈላሲ ሰንዋይ አልነበረም። ጀርመን የግእዝ አስተማሪ እንድትሰጣት ኢትዮጵያን በጠየቀችው መሠረት ብዙ ሊቃውንት ከየክፍለ-ሀገሩ ተጠሩ። አባቴ ድንቁም ከተጠሩት ሊቃውንት አንዱ ነበሩ። ሁለቱም አዲስ አበባ ደርሰው በተደረገው ምልመላ መስፈርቱን አሟልተው ተገኙ። የቀለም አባቴ ድንቁ በሆነ ምክንያት ጥሪውን ሳይቀበሉ ቀሩ። ኖላዊ ግን ጥሪውን አክብረው ጀርመን ሀገር ተሻገሩ። መሄዳቸው ቁርጥ ሲሆን በበቀደም

PDF Compressor Free Version

አንዴልኸው የሁለቱ ምሥጢራዊነት መገለጫ የሆነውን ለአባቱ አደራ ሰጥተዋቸው ሄዱ።" አለ ሊቁ ሩፊስ።

"ምን ነበር?" አለ ታሪኩ

ጥያቄውን ያልሰሙ መስሰው ንግግራቸውን ቀጠሉ።

"ጀርመን ገብተው ሀገራችንን ሰሌላው ክፍለ ዓለም አስተዋወቁ። ግእዝ ዋንኛ ክፎንኖነቱ በላይ አያሌ ምሥጢራዊ ነገሮችን አጭቶ እንደ ያዘ አስረዱ። መፈጨሻቸው ግን አላማረም።" ብለው በግንባራቸው ላይ ተቢፀተሰፋ ተነበበ።

"እንዴት? እንዴት?" አለ ታሪኩ።

"ናላዊ ዘንጀር እርግና ሲጫጫናቸው ሀገራቸው ገብተው ቀሪ ዘመናቸውን ሊያሳልፉ ሲዘጋጁ በገዛ ተማሪያቸው አጅ አለፉ።" ብለው እንባ በዐይናቸው ታቈረ። እንባታቸውን ወደ ጉልበታቸው ደገፍ አደረጉ። የታቀረው የእንባ ዘለላ በሰጋጋ አፍንጫቸው ላይ እየተንከባለለ ዱብ ዱብ አሰ። ኩልል ኩልል በሚለው የእንባቸው ጠብታ ውስጥ የንዴት መልክዐ ፊደል ተቀረፀ።

እንደገና እንባታቸውን ከጉልበታቸው ቀና አድርገው "በያንዳንዱ ሊቃውንት ሕይወት ውስጥ ስዉር ደባዎች እንደጠሳ ተራራ ተገድግደዋል። አያትህ የዚህ ደባ ሰለባ ናቸው። ሰውየው ሲፈጥራቸው የዋዛ ሰው አልበሩም። ጎንደር ውስጥ በዐርባ ዐራቱ አድባራት ውስጥ የሚመስላቸው ሊት አልነበረም። ጎንደር ሳሉ ጎንደርን በሊቃውንት አጥለቅልቀዋል። ጊላም ጀርመን ሂደው ግእዝ ቋንቋ ማስተማር ጀመሩ።

PDF Compressor Free Version

ከዚህ በኋላ ከሀገራቸው ገብተው ቀሪ ጊዜያቸውን ጎንደር ላይ ለማሳለፍ አስበው ነበር። ጠላት ቀደማቸው።"

"ምን ዐይነት ጠላት?" አለ ታሪኩ።

ዓለውንስ ቶሚ ይባላል። ቀጣፊ ጀርመናዊ ነው። ጀርመን እንደ ገቡ በደቂ መዝሙር ስም ተቆራኛቸው። ስለ ኢትዮጵያ ምሥጢራዊነት ብሎም ስለ ጎንደር ልዕልና እየነገሩ ግእዙን በሚገባ አስተማሩት። ክላውንስ ቶሚ ጎንደርን ለማጥናት ዱብ ዱብ ማለት ጀመረ። ከንፍ አስኪደቆጠቁጥ ድረስ ከአገራቸው ሥር ተወሽቆ ዐሥር ዓመት የግእዝ ቋንቋ አጠና። ጥናቱ ግን እንደ አንድ ደቀ-መዝሙር ለመልካም ነገር አልነበረም። የኢትዮጵያን ቤተ-መዛግብት ለመመገበር የከርሠ ምድሯን ምሥጢር አንጦርጦስ ድረስ ወርዶ ለመፈተሽ እንጂ። ይልቁንም የጎንደርን የሕይወት ውኃ ለማጥናት ዐሥር ዓመት ግእዝ ዐሥር ዓመት አማርኛ እንዲያውም የጎንደር ቅላጼ ያለው ጎንደርኛ የአማርኛ ዘይቤ ለማጥናት እድሜውን መሥዋዕት አድርጎል-ክላውንስ።

"ከዚያስ?" አለ ታሪኩ

"በግእዝ ቋንቋ እየበሰለ ሲመጣ ስሙን ከክላውንስ ወደ ዲልማን ቀየረ። በቀደመው የግእዝ ሊቅ በዲልማን ጀርመናዊ ስም ዲልማን ጀርመናዊ ተብሎ እንዲጠራ በጀርመን ፍርድ-ቤት ስሙን አስለወጠ። ዲልማን በሉኝ። በዲልማን ስም ጥሩኝ ብሎ አወጀ። እኔ እንኪን ክላውንስ ይሁዳ እያልሁ ነው የምጠራው።" ሊቁ ፋሬስ ገጻቸው ተለዋወጠ።

"ለምን የኔታ? ይሁዳ ድረስ ምን ወሰደዎት?" አለ ታሪኩ ፈገግ ብሎ።

PDF Compressor Free Version

"መምህሩን የገደለ፣ ሰብሉናውን የሸጠ፣ ጌታውን ያሰቀለ፣ ሰው ለሰው
ነው ክላውንስ ይሁዳ ያልሁት።"

"እንዲሁህ ይህ መሠሪ የግእዝ መምህር ሰመሆን የፈጀበት ጊዜ ስድስት
ዓመት ሲሆን በቂ ነገር እስኪያጠና ወደ ዐሥር ዓመት ዘለሰ። እግዚ
ውጪ የግል ሠራተኛ ተቀጥሮለት ልብስ አጣቢ ሞግዚት ተዘጋጅቶለት
ሙሉ ጊዜውን ቦግንበብ ብቻ ተጠቅሞ ግእዙን በክራል አወቀ። ልዲም
ሆነ ጠሚር የግእዝ ቃላትን እንዳሻው ለመተርጉም በደክመው ደግም
ፍሬ አፍርቷል። የስድስት ዓመት የግእዝ ተማሪ እደለ በቀላል ግ
የተጠመሩ የግእዝ መጻሕፍትን ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተርጉሞ ራሱንና
እግረ መንገዱን ግእዝን ለዓለም አስተዋውቋል። በመጽሐፉ ምረቃ ወቅት
በለጠው አጠር ደለ ንግግር የግእዝ ቋንቋን ያጠናው "የሐበሻ ታሪክ
ማርኮት" እንደሆነ በደፈናው ገልጦ ነበር።" አሉ ሊቁ አብረው የነበሩ
ያክል የታሪኩን ፍሰት ሳያዛቡ።

"እሺ? ዝዚያስ?" አለ ታሪኩ

"መጽሐፉ በተመረቀበት ወቅት የተሰብሳቢውን ሥነ ልቡና ለመማረክም
ግእዝ ቋንቋን ለማጥናት እንደ አብነት የወሰድኩት ሙሴ ሜንደንን
ነው። ሙሴ ሜንደን ፈረንሳዊ ነው። የፈረንሳይ ዜጋ እንደሆነ ለእናንተ
ለታሪክ ምሁራኑ አዲስ አይደለም። እንደኔ የሐበሻ ታሪክ የሐበሻ ባሕል፣
የሐበሻ ወኔ ማርኮት ኢትዮጵያ ንብቶ በእምዬ ምኒልክ መልካም ፈቃድ
አማርኛ እንዳጠና ተናገረ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ በመጽሐፉ ምረቃ ቀን
አብረው የነበሩ ይመስል።

"ሙሴ ሜንደን ማን ነው?" አለ ታሪኩ።

PDF Compressor Free Version

ሙሴ ሚንደን ኢትዮጵያ ውስጥ አማርኛና ግእዝ ተምሮ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ በፊደንሳይ የአማርኛና ግእዝ መምህር ሆኖ ግእዝን እያስተማረ ያለፈ የፈረንሳይ ዜጋ ነው። ከላውንስም ከሙሴ ሚንደን ቀሥዶ እኔም እንደዐቅሚ ግእዝ ማስተማር እችላለሁ ብሎ ዲስኩሩን ዘርቷል። በንግግሩ ወቅት ትንሽ የመዘላበድ ስሚት እንደታየበት ግንባሩ ላይ ትፍፍ ብለው የወረዱ የላብ ነጠብጣቦች ሐሳቦቹን ፍንትው አድርገውበት ነበር። ሀገሩ ጀርመን ግን "እልቦ ሊት እምቅድሚዘ ወኢ ምኮር እምድኅሬሁ" ብላ አጨብጫባ ተቀበለችው። ከግእዝ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የተረጎመው መጽሐፍም በያንዳንዱ የጀርመን ዜጋ በነፍስ ወከፍ በግድ እንዲሸጥ ተደረገ። በዚህም ሉቱፐር የሚያዳግት ቅጂ ተሸጠለታል። በወቅቱ መምህሩ የነበሩት ኢትዮጵያዊው ሊት ይሆን ሲያዩ በግእዝ የተጻፉ መጻሕፍት በዓለም ምን ያኽል ሙድ ዋጋ እንዳላቸው ተንገበገበው ጓዛቸውን ጠቅልለው መጽሐፎቻቸውን ሸክፍ ሸክፍ አድርገው ኢትዮጵያ ሊገቡ ትኬት በጨበጡበት ቀን ሬሳቸው ወደ ጎንደር መግባቱ የወቅቱ የዓለም እንቆቅልሽ ሆኖ ነበር። ውሉ የተወሳሰበ ልቃቂት! የጠቢባን ቅኔ! ከጊዜ በቀር ሊት የማይተረጉመው ውል አልባ አሚሚት! በእንባ ብቻ የሚዘከር! ለዘላለም የሚተረጎም የማይመስል ሕልም። መላ ጎንደርን በእንባ ያራጨ፣ የጎጃምን ሊቃውንት ያስቆጣ ጉዳይ ሆነ።" አሉ ሲቁ በልጅነት የተፈጠረውን የሐዘን ድባብ በአእምሯቸው እያሠሡ፡ ቀጥሎም ወደ ሀገራቸው ጠቅልለው ሊገቡ ሲጣደፉ ተደፋ። የዲልማን መጽሐፍ በተመረቀበት ምሽት በሰላም ቤታቸው ገብተው መኝታ ቤታቸውን ቆልፈው ሽልብ ብለው ሊነሡ እንደተዘጋጁ እስከወዲያኛው

PDF Compressor Free Version

አሸለቡ። ይህ እኩይ ክስተት ለጀርመን ሠርግና ምላሽ ለናንደር ግ
ሰቆቃ ነበር።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።
ታሪኩ የአየቱን ታሪክ ሲሰማ ከቆመበት ተንተዳንደ።
ሊቁም ትንሽ የአንባ ዘሰላ አንጠባጠቡ።
ታሪኩ የሊቃውንቱን ዕጣ-ፈንታ ወደ ራሱ እየተረጎመ የወደፊት ተስፋው
መጨላለም ጀመረ። እንደ ምንም ተጽናንቶ የቀሰም አያቱን የታሪክ
ፍጻሜ ናፈቀ።
"እሺ የኔታ ከዘያስ መጨረሻው ምን ሆነ?" አለ።
"ይህኮ መላ ጎንደሬ የሚያውቀው ምሥጢር ነው። አባትህ ነግሮህ
አያውቅም እንዴ?" አሉ ሊቁ።
"አባቴ ያረፈው ልጅ እያለሁ ነው። ሊሞት ትንሽ ሲቀረው ግን እንድ
ምሥጢር ሊነግረኝ ፈልጎ ነበር።"
"ምን ነበረ አሱ?" አሉ ሊቁ።
"እኔ በሥጋ ወልደኻለሁ። ዳግም መውለድ አስቤ ነበር። የዳግም ልደቱ
ምሥጢር ያለው ውኃው ውስጥ ነው። ከጥልቁ ባሕር ውስጥ ዳግም
ብወልድህ ለወደድኩ ሊል ፍርሐት ወረረኝ። እንደ ጨንቀኝ ሲረዳ
ወደፊት ዓላማህን እንጂ እኔን ተስፋ አታድርግ። ሰውና እንፍኬት ተሰባሪ
ነው። እኔ ደንዝዤ የቀረሁት የሞላዊ ሞት ተጽዕኖ ፈጥሮብኝ ነው።"
ብሎ ሐሳቡን ሳይፈጽምልኝ ወደወዲያኛው ዓለም ተሰናበተ።
አየንረመስሁ ስመጣ ነገሩ አሳሰበኝ። እናቴን ደጋግሜ ጠየቅኋት። እሱ
የሚያውቀው ብዙ ነበር። እሱ የሚያውቀውን እኔ እንዴት ላውቅ

PDF Compressor Free Version

አትሳለሁ? አለችኝ። ከዚያ ወዲያ ደግሚ ያ ጉንጭላ ማንሳቱ እናቴን ማሳቀቅ እንደሆነ ተረድቼ ተውሁት" አለ ታሪኩ።

ግሽን ግሽ! ሊንግርህ የፈለገው አሁን የጀመርሁልህን ተም ነገር ነበር። እሞ ልድ! ሰማዕቱ ባረፉበት ቀን ጎንደር ደም አልቅሳለች። ስማል የሚባል የሰቆቃ ንሙድ ታጥቃ አንብታለች። እንደ ወረደ ነገረኝ ካልህ ይሸውና" ብለው ጭራቸውን ወደ ተዋነደ ጥርስ ሽው አድርገው ቀበሉ።

"ይረፍታቸው ሲሰማ ዐርባ ዐራቱ የጎንደር አድባራት ሊቃውንት በነዘን ተመቱ። ልዕልቲ ጎንደር ዐራት ዐይናውን ሊት ተነጠቀች። በጥፍሯ ላይ ያለው ዕጣ ፈንታ በዐርባ ዐራቱ አድባራት ልክ የዐርባ ዐራት ቀናት የሐዘን ቀን ማወጅና ዐርባ ዐራት ዓመት በምድር ተሙጥ ከዐለት ላይ ነግሮ ታሪክ የሚናገር እንደ አቤል ደም የሚፈላ የደም እንባ ማልቀስ ብቻ ነበር። ያ ሆነ። እንባ አልቅሰን እኛ አነባን። በወቅቱ ሊቅ ዐዕቁ ያለአቡነ ፈቃድ ለዐርባ ዐራት ቀናት የሚቆይ ዐርባ ዐራት እግዚኦታ አወጁ። ሕዝቡ በጋራ እግዚኦ! እግዚኦ! እያለ የደም እንባ አፈሰሰ። ሊቃውንቱ በዜማ ሕዝቡ በሳግ እንባውን አወራረደ። ኪርያላይሶን ምድርን መላት። ይህ ቀን ለኢትዮጵያ እኩይ ቀን ነበር። ከሌሎች የፍሥሓ ቀናት እንደ አንዷ አልተቆጠረም። ከሌሎች የሐሴት ሰዓት እንደ አንዷ ሰዓታት ይቅርና የሰከንድ ሽራፊ ክብር ተነሣው። በላዔ-ሰብእ ቀን በላዔ-ሰብእ ሌሊት ሆነ። በላዔ-መጻሕፍት ኖላዊን የበላ በላዔ ሊቃውንት ቀን ተበሉ በጥቁር መዝገብ ተመዘገበ። በደቂቅና በልሒቅ

PDF Compressor Free Version

አንደበት ተረገመ። ኢትዮጵያ በሰቆቃ ውስጥ ወደቀች።" ብሎው ትካ
ፋታ መስዳ።

ታሪኩ ግሱን ወደ ውስጡ እየሸነሸነ በሚገባ ማዳመጡን ቀጠለ።
ሊቀም ክፋታ በኋላ በአዲስ መንፈስ ትረካቸውን አሸንደንዳት።
"ልቅሶው ከሰቆቃ በላይ ሊሆን የቻለም ለምን ነበር?" አለ ታሪኩ።
"ልቅሶውን መሪር ያደረገው የጎንደር ውኃ ጉዳይ ነው። ይህች ተአምረ
ውኃ በሲቋ በኩል ሰተመረጠ ሰምች ትሰጥ ነበር። ሲቋ ከጀርመን ወደ
ጎንደር ሲመለሱ ለብዙ ሰምች ውኃውን የማደል እቅድ ነበራቸው። ሊቅ
ዐዕቋን ጨምሮ ከውኃዋ ለመቋደስ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ወደ ሀገር
ቤት ሲመለሱ ላምንት ሲቀራቸው መላ ጎንደሬ በፍሥሓ ተመልቶ
ነበር። መኻል ላይ አረፉ ሲባል መላ ጎንደሬ ሰቆቃ በሰቆቃ ሆነ።" አሉ።
"እኔ የሰማሁት ቁብራቸው ሀጣም አፍሌቃጫቂ እንደ ነበር ነው።" አለ
ታሪኩ።

"የቁብሩ ጉዳይ በእርግጥ አጨቃጫቂ ነበር አሉ። ስለ ቁብራቸው
ጉዳይ በሲቃውንቱና በማኅበረ ጠቢባን መኻል የተነሣው ሐሳብ
ሲጠነክር አባቱ አለቃ ድንቁ በመካከል ሆነው አስታራቂ ነበሩ። በወቅቱ
ዐራት ያኽል አሳውንት ሐሳብ አቅርበው ተስማሙ። ነገር ግን ከቁብሩ
በስተጀርባ ያጨቃጨቀው ሌላ ምሥጢር ነው።" አሉ ሊቁ።
"ምን ነበር?" አለ ታሪኩ።
ሊቁ ፈገግ ብለው "በል በል ተነሥ ወደ ወንዝ ወርደህ በጊዜ ገላህን
ታጠብ። ለእንቅልፍ ጥሩ ነው።" ብለው ውልት አሉ። ታሪኩ እንዲያው
እኒህ ሰውዬ የምሥጢሩን በር አሻግረው አሳይተው ከፍተው የማያሰዩኝ

PDF Compressor Free Version

ሰሞንኮው? እያለ በጨዋታ ጠቀም አድርጎ በሳጨ። ሊቀ ኖላዊ ጀርመን ሀገር በጉብኝት ላይነሡ እንዲቀሩ የተደረገበት፣ ከቀበራቸውስ በስተጀርባ ያለው ምሥጢር ምን ይሆን? እያለ ያልነገሩትን ምሥጢር በሐሳብ እየመዘዘ ባለበት ፈዝዞ ቀረ። መሄዳቸው እንኳን ትዝ ያለው ቆይቶ ነው።

PDF Compressor Free Version

ሰኔ

ቅኔ ዘረፋ

ሊቁ በከዘራቸው እየተመረኰዙ ወደ ቅኔ ቤት እየመጡ ነው። ገሚ ሲያወርዱ ሲመጡ በቅኔ ቤቱ ውስጥ እንደጉንዳን የሚርመሰመሱ ተማሪዎች ወደ ማኅበር ቤቱ እየተራራጡ ገቡ። የተማሪዎች የመኝታ ቤት ሲቀ ግስ የሚገስሰብት፣ ቅኔ የሚዘርፉብት፣ ዘወትር የዕለቱን ታሪክ የሚተርክበት ቅዳሚ ቅዳሜ ደግሞ ወንጌል የሚሰበክበት ዳስ ነው። ዳሱ ከዕዕና ከጣር የተሠራ ሲሆን ከረምት በመጣ ቁጥር ጣር እየታጨደ ይከረከፋል። ዳሱ ሰቀላ ስለሆነ ብዙ ሣር ይጨርሳል። አገልግሎቱም ብዙ ነው። ሊቁ ፋራስ ቅኔውን የሚያወርዱት ግሱን የሚገስሱት ከማኅበር ቤት ስለ ሆነ ለማኅበር ቤቱ ታሳቅ እንክብካቤ ይደረግለታል። ሊቁ ፋራስ ቅኔ ሊዘርፉ ሲመጡ ተማሪዎች እየተጋፉ ወደ ማኅበር ቤት ገቡ፤ የተማሪዎቹ አለቃ ወደ መኝል ሄዶ ከጣሪት ፈልጎ ኩራዝ አብርቶ ሲመለስ ሊቁ ለማኅበር ቤት በር ሲደርሱ ያ ሁሉ ተማሪ ድምፁን አጥፍቶ ግርር ብሎ ተነሥቶ ተቀበላቸው። ሊቁ "አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ..." እያሉ ከዳ ወዳለው መንበረ ቅኔ ውጥተው ተሠየሙ። ያ ሁሉ ጠረ ሰማያት ተማሪ ምንም የኮሽታ ድምፅ ሳያሰማ ተቀመጠ።

ሊቁ ፋራስ ሁለት ሃብተ ግስገስሰው እንዳበቁ "ተቀበል ገሞራውሎ" አሉ።

ገሞራው በትሕትና እጅ ነሥቶ ለመቀበል ተዘጋጀ፤ ሊቁ ወደ ቅኔ ሃረጉ አሰፉ።

PDF Compressor Free Version

ሰራተኛ ምሥጢር ምሥጢረ እመ ንፄሉ ኩለሄ
ወሐ ትመርሕ መንገለ ሀለወት ቡሄ" አሉ ሊቁ።
ምራው ሊቁን አየተከተለ ያንን ቅኔ ደገመው። "መልሰው!" አሉ ሊቁ፣
ምራው እስከ ሦስት ጊዜ መላለሰው። በሦስተኛው ያ ሁሉ ተማሪ
ደምጹን ከፍ አድርጎ ያችን ቅኔ በየአፋ አላመጣት።
ሊቁ በዚህ መሠረት እስከ መወድስ ዘርፈው ሁሉንም ቅኔያቸውን
አየተረጎሙ እያበራሩ ከመወድስ ወደ መጀመሪያዋ ጉባኤ ቃና ወደ
ምትባለው አጭር ቅኔ ወደታች ወረዱ። ከመወድስ ተነሥተው ከጉባኤ
ቃና ሊደርሱ
ግሰተታ ምሥጢር ምሥጢረ እመ ንፄሉ ኩለሄ፤
ወሐ ትመርሕ መንገለ ሀለወት ቡሄ" አለ ገሞራው ቅኔዋን
ለማስተርጎም። ይቺ ቅኔ የእናንተን እውቀት ለመለካት የአእምሮ
ሚዛናችሁን ለመፈተሽ የተዘረፈች ቅኔ ናት። እስኪ እናንተ
ተመራመሩባት። ተከራከሩባት። ተጋጨባት። የቅኔውን ምሥጢር
መርምራችሁ ድረሱበት። ይቺን ቅኔ ተርጉሞና አርራቆ ለነገረኝ
በቅሎዬን እሸልመዋለሁ።" ብሎው ከቅኔ መንበራቸው አፈፍ ብለው
ተነሥተው ጉባኤውን በጸሎት አትመው ከዘራቸውን እየተደገፉ ወደ
ቤታቸው አመሩ።

PDF Compressor Free Version

፭፰

በጋታው ሊቀ ፋሪስ ሰማእኮማር ቅኔ ቤት ሲመጡ ከቅኔ ዘራፊዎች ቀድሞ ከሊቀ ሥር የተገኘው ገሞራው ነበር። በሙዳ የሚቆጠሩ የቅኔ ዘራፊዎች በናሪችውም ደቀ መዛሙርቶቻቸው በእውቀት ይበላለጣሉ። አንዳንዶች በስመ ዘራፊ ይጠሩ እንጅ እየቆጠሩ የሚቀኙ ናቸው። ቅኔያቸውም ቀላል ነው። የጥበብ ተሰጥዖ፣ የቅኔ ዘረፋ ስልት የሌላቸው ቁምር ናቸው።

ሊቁም ከታሪኩና ከገሞራው በቀር በብዙ ቅኔ ዘራፊዎቻቸው አቅም አይወራረዱም። ታሪኩ ግን ያው ግጨው ነው። መወድሱን አንሥቶ ይገጨዋል። ገሞራውም እንደስሙ የገሞራ እሳት ነው። ቅኔ ሲነግ ጩኸ ጩኸ ይለዋል። መዝረፍ ከጀመረ የያዘ አያቆመውም። ወዲህም ትጋቱ አይጣል ነው። ቀን ከሌሊት መጽሐፍ አይለየውም። ሌሊቱን በንባብ ተጠምዶ ያድራል። ጉባኤ ሲዘረጋ ደግሞ ሊቁን በክርክር ጠምዷቸው ይውላል። አንድ ቁንጽል ቅኔ አምጥቶ ለሰማ ሁሉ የሆነ ትርክት ይፈጥራል። እንኳን ያነበበውን የሰማውን ለመያዝ ችግር የለበትም። የአእምሮውን ብሩህነት የሚያውቁ ጓደኞቹ "ዘኢያገድፍ የሚባል ከሣቱም ሥጠር መድኃኒት አለው" እያሉ ይጠራጠሩታል። ደፍሮ የጠየቀው ግን ማንም የለም። ሊቅነቱ ከአቅም በላይ ስለ ሆነ ደፍሮ ዘኢያገድፍ አለህ? ወይስ የለህም ብሎ መኖር ያለ መኖሩን ያረጋገጠ የለም።

ገሞራው ግን ሊቀ ፋሪስ በሚዘርፉቸው ቅኔዎች አጥብቆ ይመሰጣል። "ከብሩ ለልብ ተመሥጦ ውእቱ፤ እያለ ይጠቃቅሳል። የአእምሮ ከብሩ

PDF Compressor Free Version

መመስጥ የቅድስና ዘበሩ ጽሙና ነው እንደማለት ነው። ከተለም በቀር ለራሱ ወሬ አንደበቱ አይከፈትም።

ይህ ሊት የሊቁ የፋሬስ ደቀ መዝሙር በመሆኑ የተለየ ፍሥሓ ይሰማዋል።

ሊቁ ፋሬስም ፋና ወጊ የቅኔ ሰው እንደሆነ ዓለም ይመሰክርላቸዋል። ክቡኔ በተሰጀርባም ከነገደ ሔት ሲወርድ ሲወራረድ የመጣውን ቅብዐ ጥበብ ተቀብተዋልም ይባላል። ባለ ቅኔው ተዋነይ ካስተማረበት ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ገዳም ቅኔ ማስተማር ከጀመሩ ብዙ ዓመታትን አስቆጥረዋል። በሊቃውንት የዝር ሐረግ ሲቆጠሩ ባሁኑ ጊዜ የተዋነይ የመጨረሻው መምህር ናቸው። ዘወትር ተዋነይ ከሚያስተምርበት ዋርካ ሥር ቡሔ ከሚባል ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ያስተምራሉ። ንባኤው አንድ ቀን አይታጠፍም። እንደ ሌሎች ከተማ ገብቼ ተቀዮሬ ሀብት ላብዛ፣ ቤት ልሥራ ማለት አያውቁም፤ የአበውን ፈለግ ተከትለው በኢትዮጵያ ለመጥፋት ከፍተኛ አደጋ ላይ የወደቀውን የግእዝ ቋንቋ ከመጠበቅ ጎን ለጎን የግእዙ ቅኔም እንዳይጠፋ ይለፋሉ። በቅኔ ይፈላሰፋሉ። ግእዝ በግእዝ ብቻ የተጠመሩ ውድ ውድ መጻሕፍት ባሉባት የሊቃውንት ሀገር የግእዝ ቋንቋ እየተዳከመ መምጣቱ ግርም ያደርጋቸዋል። በግእዝ ቋንቋ ብቻ ድርሰት ደርሶ ለትውልድ ትውልድ ማስተላለፍ ቢቀር እንኳን የግእዙን ቋንቋ ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ከእኔ ይጠበቃል ብለው ራሳቸውን ለወደዱት ነገር ሰውተዋል።

ከዚህ ባለፈ የሀገራዊ ምሥጢር ማእምር ቢሆኑም ከመናገር ግን ቁጥብ ናቸው። አልፎ አልፎ ውድ የሆኑ ምሥጢራትን በቅኔአቸው ውስጥ

PDF Compressor Free Version

ይዘራሉ። ጉናንት ማታ በዘረፋት ቅኔ የዘሩት ግን አሰካሁን በመወደስ
ከዘሯቸው ምሥጢራት ወጣ ያለ ነገር ነበር። በል ሲላቸው እንዲህ
ናቸው። ዐቢይ ዐቢይ ምሥጢራትን ወንጭፈው ምሥጢር ይደብቃሉ፤
ከማብራራት ይታቀባሉ። ምሥጢር መደበቅ ከቀደምት ሊቃውንት
የወረሱት ባሕላቸው ነው። በተለይ የጎንጅ ጽላሎ ሊቃውንት በዚህ ግብር
ይታማሉ። ምሁር ተመራምሮ ሊደርስበት የማይችል ቅኔ ዘርፈው
ምሥጢሩን ይደብቃሉ።

ሊቁ ፋሬስ "በሐተታ ምሥጢር ምሥጢረ አመ ንሄሱ ኩሰሄ
ቡሔ ትመርሕ መንገሰ ሀለወት ቡሂ" ብለው ዘርፈው ወደ ቤታቸው
ገቡ።

ገሞራው እንደተሰመደው ትርጉሙን ጠይቆ ለመረዳት ቢፈልግ
"መርምረህ ድረስበት" ብለው ገሰጹት። ተመራምሮ ለመድረስ ሌሊቱን
ያለ እንቅልፍ አነጋው። ትርጉሙን እንደነገሩ አወላገደው፤ ከዋናው
የምሥጢር ቁንጮ ለመድረስ ግን አልቻለም።

በተለይ "ቡሄ ወደቡሄ ታደርሳለች" የሚለው ስንኝ ምን ማለት እንደሆነ
አውጥቶ አውርዶ ሳይደርስበት ሌሊቱ ነጋ። ዐርብ መጣ።
ሊቁም እንደተሰመደው የዐርብ ማለዳ ሥራቸውን ለመሥራት ወደ ቅኔ
ቤቱ ሲገሰግሱ

"የኔታ!" አለ ገሞራው ሊቁ ንብሌ ሲመጡ አንዳና ጠብቆ።
"አቤት ልጅ"

PDF Compressor Free Version

ግንንትና ማጅራት የሚሉት መወድሶች በላይ ነው። ስሙ ባለ ሁለት ቤት ቅኔ ተብሎ ይጠራ እንጂ ሦስት ሙቶ መወድሶች እንካን ሊተካከሉት አይችሉም።" አለ ገሞራው።

ሌቱ በግርምት ፈገግ አሉ።

"መምሬ ይሙት!" አለ ገሞራው በቀለም አባቱ በራሳቸው በፋሬስ ስም እየማለ።

"ዝኩአ ጎቡአ ቅኔ ዘርፎ ሊቃውንትን ከተፈታተነው ከተዋነይ ቅኔ ጋር በወዳደር የአስም ቅኔ ይረቅቃል። የእርስም ቅኔ ጎቡአ ነው። ውሉ ውስብስብ ነው።" ገሞራው የተዋነይን ቅኔ በውስጡ እያሰላሰለ በሊቱ ፊት ተፈላሰፈ። ቀጥሎም "ተዋነይ ለዘላለሙ ተዋነይ ተዋነይ ተብሎ ስሙ በቅኔ ቤት ገንኖ የተረፈው

"ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ፤
ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ።"

ባለው ግሩም ቅኔ ነው። በእርግጥ ከዚህ የላቁ ቅኔዎች እንደነበሩም አውቃለሁ። ሌሎች በአደባባይ ተነግረው አያውቁም። ይኸኛው ቅኔ ግን ንባቡ በአደባባይ የተነገረ ሲሆን ምሥጢሩ ገዘፍ ብሎ ምሥጢር ነው።" አለ ገሞራው።

ሊቁ ፋሬስ የቀለም አባታቸው የተዋነይ ቅኔ ሲነግ ገጻቸው ፈካ። ከዚያም

"አዎ" አሉ ሐሳብ ለመጨመር።

"አዎ!" ባነሣሽው የተዋነይ ቅኔ ውስጥ "ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ። ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ" የሚሉት ቃላት በባለ ቅኔዎች ዘንድ ተጽዕኖ

PDF Compressor Free Version

ፈጥረዋል። የሊቃውንቱን ሊቅነት ተፈታትነዋል። በተዋነደ ቅኔ ውስጥ ፈጣሪ ፍጡር ተደርጎ ቀርቧል። ፍጡሩ ደግሞ ፈጣሪ መስሎ ተነግሯል። ይህ ላይ ላዩ ነው። ውስጡን ፈልቅቆ የተረጎመው ግን የለም። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች ይህንን ቅኔ አፍታትቼ እንድነግራቸው በተደጋጋሚ ደብዳቤ ጽፈውልኛል። ቤቴ ድረስ መጥተው የጠየቁኝም ቀላል አይደሉም። የዘመኑ ቀሲላን ሊቃውንት ይህንን ቅኔ ሲሰሙ በጪስ እንደታፈነች ጃርት ይጨነቃሉ። ጥይት እንደተተኮሰባት ሚዳቋ ጀሯቸው ጭው ይላል።" አሉ ሊቁ።

"እርስዎ ያን ጊዜ ሳይኖሩ እንዴት ሊረዱት ቻሉ?" አለ ገሞራው የጅል ጥያቄ!

ሊቁ ሳቅ አሉ።

"ባለ ቅኔስ ያን ጊዜ ኖረ አልኖረ ጉዳዩ አይደለም። በጊዜው ሳይኖር ከቅኔው ሐሳብ ተነሥቶ ቁጣ ቁጣ ነገሮችን ይፈታል። ቅኔውም በውስጡ ቁጣ ምሥጢር ይሏል። ቅኔ ነውና ቁባውን ፈትተን አየነው። ተስማማን። ቅኔ ነውና እንደቅኔነቱ 'አሜን' ብለን ተቀብለነዋል። የባለ ቅኔዎች አሸምሮ እስከ ጸባያት ደርሶ አዲስ ሐሳብ ማፍለቅ ስለሆነ ሥራው ቅኔውን እንደ ቅኔ ወስደን የነገረ መለኮት ተፋልሶ እንዳያመጣ አመስጥረን እናውቀዋለን። በእርግጥ ቅኔው ጸባያት ድረስ ገስግሶ ሂዶ ፈጣሪን መሳሸሙንም አላጣነውም። ፍጡር ፈጣሪን እንዴት ፈጠረ ተባለ? ይህንን ሰልበ ቢሰኙ እንናገርም። መርምረው ይድረሱበት። ነገር ግን ተዋነይን ስማድነት በቀር ቅኔውን አበታው መፋቅ አንችልም። ከወረቀት ፍቀን ፈቅፍቀን እናጥፋው ብንል እንኳ ከአእምሯችን ሊፋቅ

PDF Compressor Free Version

አይችልም። መሻል ናሳችን ላይ ጉብ ብሏል።" ብሰው ትልቱን ናላቸውን ጸሰ። ከዚያም "ቅኔዉ ዕትብታችን የተቆረጠበት አምባርት ማለት ነው። መሻል ሆዳችን ላይ እንደ ገመድ የተንመደደ አምባርት አለ። የዕትብታችን ምልክት ነው። አልተስማማንም ብለን የዕትብቱን ግንድ ቆርጠን መጣል አንደሌለብን ሁላችንም እናውቃለን።"

"አም" አለ ገሞራው።

"ይህንን ቅኔም ቆርጠን መጣል አንችልም። በሌሎች ዘንድ መሴ "ፈጣሪውን ፈጠረ" የሚለው ሐረግ ዛሬ ድረስ አፈጮሌቲ እንደሆነ ቀጥሏል። ባለፈው ቡተሞነይ ዙሪያ የተደረገ አንድ ትልቅ ጥናት ነበር። ነገርዬው ጥናት ከማለት ይልቅ ጉንጭ አልፋ ክርክር ቢባል ይቀላል። የክርክር እንጂ የጥናት ይዘት አልነበረውም። የሆነው ሆኖ ጥናቱ የተካሄደው የሃይማኖት ሊቃውንትንና የዘመናውያን ምሁራንን ማዕከል አድርጎ ነበር። ምሁራኑ ከዓለማውያን ተቋማት ሊቃውንቱ ከየንዳማቱ በመብራት ተለቅመው መጡ። ቀና ብዩ ሳጤናቸው ዘመናውያንምሁራኑ በፅጥፍ ናቸው። ብዛታቸው ግን የተዋነይን ቅኔ ለመርመር ያላቸውን ብቃት አይገልጥም።

"መሴ ፈጠረ ፈጣሪው"

የሚለውን ቅኔ ቀርቶ የሀገሬ ገበሬ በአሽሙር የሚናገረው ፈሊጣዊ ቅኔ እንኳን በደንብ የሚገባቸው ዐይነት አይመስሉም። በዘመናዊ አውቀት ዲግሪና ከዚያም በላይ መያ እንዳላቸው ስምቻለሁ። ዲግሪያቸውን አልነቀፍሁም። በዚህ አጋጣሚ ሀገሬ ኢትዮጵያ ምን ያኽል ዶክተሮች አንዳሷት ተረድቻለሁ። በአንጻሩ ደግሞ ቤተ-ክርስቲያናችን ምን ያኽል

PDF Compressor Free Version

የሲቃውንት ችግር እንደገጠማት አውቄአለሁ። ለምለሚ ብዕራችን እነደ በጋ ቅጠል መጠውለጓን አይቻለሁ። እናም እነሆ የዓለም ጠበብት ናቸው በተዋነይ ቅኔና ሥራ ላይ ምርምር ጀምረናል ያሉት። ትንሣኤያቸው ደስ ያሰኝ ነበር። ወደኋላ ሂደው የተዋነይንና የቀደሙ ሲቃውንት ሥራን ለመመርመር በመነሣሣታቸው እጅግ አመሰገንኋቸው። ነገር ግን ከተጠሩት ከፊሉ የግእዝ ቋንቋ መስማት አይችሉም። የእኔን እግር አጣቢ ደርቤን ታውቀው የለ? አዎ! ግልጥ ደርቤዎች ናቸው። ሊቅ ተብለው ሲጠሩ ሊቅ የሾንን መስሏቸው ጥሬውን አክብረው ከፀሬቱ ማዕዘን የመጡ ናቸው። መምጣት የሚገባቸው አረጋውያን ሲቃውንት ግን አልመጡም።" ብለው ከዘራቸውንወደ ትክሻቸው ሰቀሉ።

"ከዚያስ?" አለ ንሞራው

"ዘመናውያን ሲቃውንት ተነሥተው ቅኔው የፈጣሪን መለኮታዊ ሥልጣን ተጋፍቷል። ሙሴን ከፈጣሪ በላይ ፈጣሪ አድርጎ ስሎታል። መታረም አለበት ብለው ደመደሙ። ባለቅኔ ከተሰመደው የሃይማኖት ሐሳብ ያፈነገጠ በጥባቄ ሊቅ እንደሆነ እንኳ የደመነፍስ ያክል ግንዛቤ እንደሌላቸው ተረዳሁ። በዚያም ቅኔ ከሃይማኖታዊ ይዘት ወጥቶ ራሱን ችሎመቆም የሚችል ድርሰት መሆኑን ሳይረዱ ለጉባኤ በመሰለፋቸው ማፈር ነበረባቸው። ነገር ግን እውቀታቸው በስማ በለው እንጂ ማእዝ ተምረው ስላልሆነ ትችታቸው በክንቱ እንደሆነ ሲሰማኝ በእነሱ ፈንታ እኔ ራሴ አፈርሁ። እነሱ የሚሉትን ብለው ገለል እንዳሉ ተራው በየንዳማቱ ለመጡ ሲቃውንት ሆነ።

PDF Compressor Free Version

ከየገዳማቱ ተለቅመው የመጡ ሊቃውንት ግን ቅኔው የነገረ መለኮት እንጻልጣሰ ተናገሩ። ቅኔው ቅኔ እንጂ ፈጣሪን ከፍጡር መምህርን ከደቀመዝሙር የሚያበላልጥ ሐሳብ የለውም ብለው ክርክር አቀረቡ። እኒህ የጋን መብራቶች በቁጥር አናሣ ከመሆናቸው ሌላ ምሥጢሩን መጠበቅ እንጂ ሐሳባቸውን አፍታትተው የውስጣቸውን አውጥተው ያንኑ አቀላጥፈው የመናገር ስልቱ የሌላቸው የጋን መብራት ስለሆኑ ሐሳባቸው በአፈ ጮሌዎች ባዶ ካካታ ተዋጠ። አንዱ አፈ ጮሌ ተነሥቶ መድረኩን ያዘ። ከዚያም ወደ ጉባኤው ዞሮ "ቅኔው መታረም አለበት" ሲል ደነፋ። ከሥሩ የተኮለኮሉ ተከታዮቹ አጨበጨቡለት።

የፈረጠመ ክንዱን ወደ መሬት እየከነዳ

ይታረም! ሲል ድጋሚ ጮኸ።

ግብረ-አበሮቹ ተከተሉት።

ይታረም! ይታረም! ይታረም!"

ድምፃቸው ጣራ ወጣ።

ቅኔው መታረም እንዳለበት ውሳኔ ተላለፈ።

ሰውዬው ከመድረክ ሲወርድ አንድ አረጋዊ ሊቅ በሰው ተደግፈው ተነሡ።እንደምንም ተንገዳግደው ቆመና "አንተ ልጅ?" ሲሉ በትሕትና ተጣሩ። ወደመድረክ ወጥቶ ቅኔው እንዲታረም ያስጨበጨበው ሰውዬ "አቤት" ብሎ ተነሣ።

"ይታረም ማለትህን ወድጀዋለሁ። አም ይታረም!" ሲሉ ሰውዬው የደገፉኝ መስሎት አጨበጨበላቸው። ግብረ-አበሮቹ እሱን ተከትለው

PDF Compressor Free Version

አጨበጨቡ። ሊቀ ነደጓቸው። ሟቡጨባው ጋብ ሲል "በል! ልጀ! ሊቁ የእኔ ልጅ! ተነሣና

"ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ፣

ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ።" ያሰውን ቅኔ በሊላ ቃል ተክተህ አርመህ አሣየን።" ሲሉ ሰውዬው በላብ ተዘፈቀ።

"ሰውዬው እንኪን ቅኔውን በሊላ መተካት ቀርቶ የግእዝ ቋንቋ አይሰማም ነበር። ሰውዬው በላብ ሲዘፈቅ ተክታዮቹ አንገታቸውን ወደ መሬት ቀበሩ። እንዳጨበጨቡሉት አጨበጨቡበት።

"አረጋዊው ሊቅ ግን በዚህ አላበቁም። አባቶቻችን አክብረው የተቀበሉትን፣ እንዴት ከመሬት ተነሥተን ከመጽሐፍ አንፍቀዋለን? ከቁጥር እናወጣዋለን? እናውጣውስ ብንል መቼ ይወጣል? ከአእምሮ እንዴት በቀላሉ ይፋቃል? በዚያውም ላይ ሌሎች ወደ ሀገራቸው ቋንቋ ተርጉመውታል። እንዲያውም ውስጡ ላይ ምን ምሥጢር እንዳለበት እየመረመሩት እንደሆነ ሰምቻለሁ።" ብለው አስከበቃን ዘለፉን። ከዝምታ "በቀር በቂ ምላሽ አልነበረንም።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ወልደ-ድንቁ።

ንሮራው ዐይኖቹን ጨፍኖ ሲሰማ ቆይቶ "የዘመኑ ችግርም እኮ እሱ ነው! ከመጠምጠም መማር ይቅደም የሚለው ብሒል ከዚህ ጋር ይዛመዳል።" ብሎ ወደ ጥያቄው ተመለሰ።

"እኔም የፈራሁት ያ ሰሕተት በአርስም ቅኔ ላይ እንዳይደገም ነው።" ነገ ደግሞ አርስም "ቡሄ ትስሕብ መንገለ ሀለወት ቡሄ" ብለው የዘረፉት ቅኔ በነገው ትውልድ አርምት ሊጠብቀው ይችላል። መደራት

PDF Compressor Free Version

ይህ ቅኔ አጨቃጫቂ እንዳይሆን በአጭሩ ይቀጭ ባይ ነኝ። በእርግጥ ነገ ሳይመጣ ጭቅጭቁ ትናንት ተጀምሯል።" አሰ ገሞራው።

"እንዴት?" አሉ ሊቁ።

"ትናንት ማታ በዚህ ቅኔ ስንጨቃጨቅ ሁለቱ ዘራፊዎች ሊጋደሉ ነበር።"

"ማንና ማን ናቸው?" አሉ ሊቁ ቅኔ ዘራፊዎችን በውስጣቸው እያስታወሱ።

"አያ ጌዶርና አያ ዕዑብ!" አለ ገሞራው።

"ጌዶር ሷ፟ቴው?"

"አሞ ገለሚንጡ ጌዶር" አለ ገሞራው።

ጌዶር በቅኔ ቤታቸው ውስጥ የሚኖር አውደልዳይ ቢጤ ተማሪ ሲሆን የአንዱን የቅኔ ዘራፊ ስም ጠርቶ ከኔና ከእከሌ ማን በቅኔ ይልቃል? ሲል በቅኔ ቤቱ ያሉ ጀማሪ ተማሪዎችን ይጠይቃል። አንተ ትልቃለህ ካሉት የሦስት ቀን መንገድ ሂዶ ጠላ ሰምኖ ያመጣና ያንን ተማሪ ሳምንት ያጠጣዋል። የተጠያቂው መልስ በተቃራኒው ከሆነ ያ ተማሪ ፈረደበት አይቀጡ ቅጣት ይቀጣዋል። በዚህም የተነሣ አንድ ተማሪ በስለት ወግቷል።

ገሞራው ቀጠለ።

"የኔታ! እርስዎ አያውቁ እንደሆነ እንጂ አያ ጌዶር የጅብ ያኽል ጉልበት አለው። እግዚአብሔር እንደ-ጅብ ፈሪ አድርጎ ፈጥሮት እንጂ ከያዘ አይለቅም። ሲበዛ የጉልበት ሰው ነው። ለልመና ወደ መንደር ሂዶ እግዜር ይስጥህ ሲሉት ሴቶችን ያንቀጥጣል።

PDF Compressor Free Version

ያያታል።" ብሎ ሲመታው ሲመጣ አስቀድሞ ይፈነክተዋል። በሰሬር አለን የሚሉ ኮበሌዎች በሙሉ የጌዶርን በትር የደም በትር ሲሉ ይጠሯታል። ክቅኔው የበለጠ የጉልበት ተሰጥዎ አለው።" አለ ገሞራው። "ገለሚንጡ የሚለውን ቅጽል ደግሞ ማን ሰጠው? እኔ ዓይቱ ነር የምሰው" አሉ።

"ቶማስ ነው ገለሚንጡ ያለው። በቶማስ አገላለጽ ገለሚንጡ ማለት ሁሉን የሚገላምጥ አውደልዳይ፣ ደርሶና ደርሶ የተማረን ገላ በድንት መምተሪያ ስለት የሚገምጥ እንደማለት ነው።"

ሲቄ ፋሬስ በድርጊቱ ቢበሳጩም በቅጽል ስሙ ፈገግ ብለው "ታዲያ ትናንት ምን ሠራ እያልህ ነው? ወቸው ጉዴ?" አሉ።

"ትናንት ማታ ቅኔውን መርምሮ ለነገረኝ በቅሉዬን እሸልመዋለሁ ብለው ቅኔውን ሳያብራሩ ሲሄዱ በቅጸላ ላይ ጸቡ በረታ። ገለሚንጡና ዕፁብ አጥብቀው ተከራከሩ። ዕፁብ በክርክር ዘረረው። ጌዶር ቀስ ብሎ ወደ ጎጆው አመራ። እኔና ዕፁብ የተኛ መስሉን በቅኔው እየተከራከሩን ነበር። አጅሬ ገለሚንጡ እንደ አርጃኖ ጅራት የተድበለበለ ካራ ነጥቆ የእያ ዕፁብን ሆድ እቃ እዘረጥጣለሁ ብሎ ፎከረ። መኻል ገብቼ በመገላገልና የቅኔውን ምሥጢር በማፈላለግ ስዳክር አደርሁ።" አለ ገሞራው።

"እና ምን አርግ ነው የምትለኝ?" አሉ ሲቄ።

ይህን አጨቃጫቂ ቅኔ ተርጉመው እእምሯችንን ካላሳረፉ ቅኔ ዘራፊዎች የኔው ነው ትክክል? የኔው ነው ትክክል? በማለት ወደ ጦርነት ይገቡ

PDF Compressor Free Version

ይመስለኛል። በአንድ ነጠላ ትርጉም መላ ቅኔ ቤቱ ከሚበጠበጥ ትርጉሙን በታሰሩ ቢናገሩ ይሻል ይመስለኛል። ደግሞ የእርስዎ መወድሶችን ማበላለጥ ይከብዳል እንጂ የዛሬው ከወትሮው በጣር ነው። በምሰሉ አስረዳ ካሉኝ ከሚክኤልና ከገብርኤል ክንፍ የማናቸው ክንፍ ይረገፃል ተብሎ አይጠየቅም። ሁሉም ተመሳሳይ ናቸው። የእርስዎ ቅኔዎችም የማበላለጡ አይመስለኝም። ሁሉም ተመሳሳይ ምሥጢር አላቸው። ነገር ግን የትናንት ማታው የቅኔው ተዋቅሮ እስከ ወዲያኛው የሚተረጎም አይመስለኝም። ፊደል ከቀጠርኩበት ዕለት ጀምሮ እስከ ተቀኘሁበት ዕለት እንዲህ የረቀቀ ምሥጢር ሰምቼም አይቼም አላውቅም። እንደ ረቀቀ እያወቁ ትርጉሙን ነፈጉን። መርምራችሁ ይረዱበት ሲሉ የደቀ መዛሙርቱ አእምሮ ባኮ። የዘራፊዎች ሲትነት ተፈተነ።" አለ ገሞራው

"ለመሆኑ ቅኔውን ለመፍታት ሞክራችሁ ነበር?" አሉ ሊቁ ፋራስ በከዘራቸው ደገፍ ብለው ጎዳናቸውን ገታ አድርገው።

"አዎ ቅኔ ዘራፊዎች በጋራ ተሰባስበን ሌሊቱን ሰንፈኔቃጨት አደርን። የሸላ ፍሬ እንደሚለቅሙ የወፍ ጫጩት ስንጫጫ ሌሊቱ ነጋ።" አለ ገሞራው።

"ታዲያ ከጭቅጭቁ በኋላ ምን መፍትሔ ላይ ደረሳችሁ።" አሉ ሊቁ ፋራስ።

"ትርጉሙን እንደነገሩ ቆነጻጽለን የደረስንበት ይመስለኛል" አለ ገሞራው።

"እስኪ ምን ማለት ነው?" አሉ ሊቁ ግራ ጀሯቸውን ወደገሞራው ዘንበል አድርገው

PDF Compressor Free Version

ያው ግእዙ

"ዘሐተታ ምሥጢር ምሥጢረ እመ ንሄሉ ኩሉሄ

ቡሔ ትመርሕ መንገለ ትሔሉ ቡሄ" ነው አለ ገሞራው።

"ትርጉሙስ?" አሉ ሲቄ።

"ምሥጢር ሰጠየቀ ለተጋ በቃሉ።

ቡሔ ወደ ቡሔ ትመራለች አሉ" የሚል ግጥም እንዳለው ጫፍ ጫፉን የደረስንበት ይመስለኛል።" አለ ገሞራው።

"እሱህ ነው! ዝገዝ ዝገዝ የኔ ሊቅ!" አሉ ተስታ:ችው። ሲቄ ተስታ:ችእንጂ ተማሪያቸውን በፊቱ "ሲቅ" ብለው ከሚያመሰግኑ ቢሞቱ ይሻላቸው ነበር።

ወዲያውም

"ታዲያ ምኑ ቀረ?" አሉ።

"የቀረውማ ምሥጢሩ ነው። እኛ በአግድም የተለምነው ነጠላ ትርጉም ነው። ከዋናው የጥበብ ጫፍ ላይ አልደረስንም። እንደዐሰት የጠጠረብን "ቡሄ ወደ ቡሄ ትመራለች አሉ" የሚለው ምሥጢር ነው። እኔና ጓደኞቼ ስለቡሔ የጠለቀ እውቀት የለንም። ቡሄን የምናውቀው በዘልማድ ነው። የደብረ ታቦር ቀን "ቡሄ በሉ ቡሄ መጣ" ሲባል እንሰማን። ዛሬ ግን በዐሉ ደብረ-ታቦር አይደለም። ደብረታቦር ካልሆነ ቡሄን ምን አመጣው? ብሰን በቅኔው ተጋጨ ባሉት መሠረት ተጋጨን። በዚህ ጊዜ ደካማው ሲቅ ዕፁብ ጢጢቱ ጌዶርን በክርክር ሰቅዘ ይዞ ላብ በላብ አረገው። ጌዶር ግጭቱን የጦር ዐውደ-ማ አደረገው። ዱልዱም የድንች መምተሪያ ስለት መዝዘ ለመውጋት ተገሰገሰ።" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

ሊቁ ክብተር ብለው "ወዲህ ና" ብለው ዋናውን መንገድ ትተው ወደጫካው ገቡ። ገሞራው ጫካውን እየጣሰ ተከተላቸው። ጥቂት እልፍ እንዳሉ ከጫካው ውስጥ የወደቀ ዐይናማ ድንጋይ ላይ ወጥተው ገብ አሉ።

ገሞራው ከዐይናማው ድንጋይ ሥር ተወሸቀ።

ሊቁ በከዘራቸው ዐሰቱን ጣር ጣር እያደረጉ ሊያስላስሉ ጥቂት ቆይተው

"ቡሄ ወደ ቡሄ ትመራለች አሉ" የምትለዋን ግጥም በአዲስ ዜማ እንደማስረቅረቅ አድርገው፤ ቡሄ ማለት" አሉ ገሞራው በንቂሐ ልቡና እንዲከታተላቸው ፈልገው።

"ቡሄ ማለት ከጣቱ ምሥጢር ማለት ነው። ለሀገራችን ሊቅ ለሊቀ-ነቢያት ተዋነይ ዘጎንጅ "ሄጠር" የምትባል ጠንራ ብር የምታኸል ድቡልቡል ድንጋይ ነበረችው። የተከፈለችው ቡሄ ድንጋይ ተብሎ ከሚጠራው የብርሃን ድንጋይ ነው። ጥበቡ ቡሄ ከሚል ድንጋይ ጋር ተዛምዶ አለው፡ ሊቁ በዘመኑ ከዚህ ብርሃናዊ ድንጋይ ላይ ቁሞ ሲል ነቡኣ ምሥጢር ከፊቱ እየመጣ ይረገረግለታል፤ ይህ ጥበብ ከፈጣሪ ለኢትዮጵያ ብቻ የተሰጠ ሲሆን ምንጩ ቡሄ ድንጋይ ነው። ስመ ጋኔን ነገረ-ደብተራ ወይም ድግምት መተትና ከጠልሰም ጋር የተያያዘ ነገር የለበትም።" አሉ ሊቁ በሚያምር ድምፃቸው።

ወዲያው ገሞራው በንቂሐ ልቡና ሲከታተላቸው ተመልክተው ንግግራቸውን ወደ ግእዝ ለወጡ።

PDF Compressor Free Version

"መአልበ ውስቱቱ እመኒ አስማት መእመኒ ስመጋኒን ዳዕሙ ተፈጥረ በንተ ርእሰ አዳም ወደኢቲ ገነት ኢትዮጵያ ይእቲ እንተ ወገትዋ ስድስቱ አፍላጋት በአንጻረ ስድስቱ አክናፈ-ዋርካ ዘሊተ ነበልባል ተዋነይ ኮኑ ምሥጢራት።" አሉ ሰመስማት በሚስብ ድምፃቸው።

ከአማርኛ ወደ ግእዝ ቋንቋ መስመጣቸው ግእዙ ከአማርኛው የዘለለ ጉልበት እንዲሰጠው አስበው እንደሆነ ለተሞራው ቀድሞ ነበር የነገሩ። ትርጉሙ ግን ምንም ለውጥ አልነበረውም፤ ይህ ጌጤር ከአሰማትም ሆነ ከድግምት ጋር አንዳች ተዛምዶ የለውም። ዑሄ ድንጋይ ስሚባል ብርሃናዊ ድንጋይ የተከፈለ ከኅቱ ምሥጢር ድንጋይ ነው። ይህ ድንጋይ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ከኢትዮጵያም ስስድስት ዐቃ ብቻ ይገኛል። እነሀም የስድስቱ የተዋነይ ዋርካ አክናፎች ምሳሌዎች ናቸው።" የሚል ክሡት የሆነ ቃል እንደሆነ ግእዙን ወደአማርኛ ቋንቋ ተረተረው።

ሲቱ ፋሬስ ወዲያውኑ ግእዙን ትተው ወደ አማርኛው ተመለሱ። በግእዝ የተናገሩት አስበውበት ሳይሆን ዘወትር ከአማርኛ ግእዝ ስለሚቀናቸው ጭምር ነው።

ዑሄ ለነፎች እንደሚሉት አስማት ወይም ድግምትም አይደለም። በገነት ለመጀመሪያው አዳም የተሠጠ የጥበብ ድንጋይ ነው፤ አዳም ዑሄ በሚባል ድንጋይ አማካይነት የተለወሩ ነገሮች ሁሉ ተገልለጠው ይታዩት ነበር። አጋንንትም ሆነ መላእክት ከአዳም መሰወር አይችሉም ነበር። መላእክት ለሙዳሴ ሊቃነ መላእክት ለትዳሴ ሲፈልጉት በዚህ ድንጋይ የደወል ድምፅ ያሰሙት ነበር። አዳምም ከመላእክት ጋር ለሙዳሴ

PDF Compressor Free Version

ከነዋኩበት ጋር ለዝማሬ ተሰልፎ ፈጣሪውን እያመሰገነ በንስት ጥቂት ዓመት ኖረ። በዚህ የቀናው ክይሲ በዕዕ ትጠል ጣለው። በዚህ ጊዜ ቡሄ ተሰወረበት አትብሳ ያለውን ሲበላ እወቅበት! ተፈላሰፍበት! ተብሎ የተለጠው ቡሄ ከእጁ አሞሸለኮ ተሰወረ።" አሱ ሊቁ ፋሬስ።

ሊቁ ይህንን ተናግረው ከዐይኑማው ዐለት ላይ ተነሥተው "እየተንሳደዱ ገባህ?" አለ።

"ትንሽ ትንሽ እንደገባኝ ቡሄ የምትባል ብርሃናዊ ድንጋይ ለአዳም እንደነበረችው ነው። ሌላው አልገባኝም።" አለ ገሞራው የተናገሩት ግራ አጋብቶት።

"አዎ እንዲህ ዐይነቱ ረቂቅ ምሥጢር ለጆሮ በጣም የራቀ ነው። አዳም የሞት ፍሬ በልቶ በዕዕ መውደቁ በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ቁጥር አንድ ጀምሮ ተጽፏል። ቡሄ በሚባል የጥበብ ድንጋይ ላይ መለኮታዊ ፍልስፍና ይፈላሰፍ እንደነበረ ግን አልተጻፈም። በሌላም የድርሳን መጽሐፍ የተጻፈው ኃጢአቱ ሩካም በሚባል ድንጋይ በሰይጣን እጅ ተጽፎ ባሕር ውስጥ መጣሉና ጎላ በዳግማይ አዳም በክርስቶስ ጥምቀት መደምሰሱ ነው። ውስጠ ምሥጢሩ ግን በድንጋይ ምክንያት ኃጢአት ወደ ልቡ እንደገባ ኃጢአቱ በድንጋይ ላይ መጻፉን ያስረዳል። በድንጋይ ላይ መለኮታዊ ፍልስፍና እንደተጻፈ ማስተማር በሀገራችን እንግዳ ትምህርት ነው። ሙሴም በቶራ መጽሐፉ አልከተበውም። በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ በግልጥ የተጻፈው የሞት ፍሬ በልቶ መሰሳቱ ብቻ ስለሆነ የንገረ መለኩቱ አስተምሮ በዚህ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው። እኛም ይህንን ይዘን እንማራለን። እናስተምራለን።

PDF Compressor Free Version

የቡሄ ምሥጢር የሚመስደው ለምን የአዳም የሞት ዕዳ ሩኅም በሚባል ድንጋይ ላይ ተቀረፀ ለሚለው ጥያቄ የተሠጠ መልስ ነው። አያልሁት ያለ ግልፆ ይመስለኛል።" አሉ ጥቂት ተናግረው እግረ መንገዳቸውን የገሞራውን ከሕሉት አየለኩ።

"አልገባኝም?" ሄትኖዋ ቡሄ ለሄትኖዋ መሪ ናት ማለት ነው?" አለ ገሞራው ከሊቁ ሐሳብ ወጥቶ።

"እሱ ነው ያልገባህ?" አሉ ሊቁ ኮስተር ብለው በደንብ እንዳልገባው አይተው።

"አም።" አለ ገሞራው አሱም እንደ ሊቁ ኮስተር ብሉ። በእርስዎ እንደነገርኩህ "ቡሄ" ድንጋይ ሲሆን ከሌሉች አእባን የተለየ ምሥጢራዊ ድንጋይ ነው። ለምሳሌ ከዚህ ደምሮ ዒሄ ተብለው የሚጠሩ የድንጋይ ዐይነቶች ተራራውን ወረውታል። ስሙን እንጂ ምሥጢሩን ግን አልወረሱም። አግልግሎታቸውም ከፍ ሲል ለኪነ-ሕንጻ ዝት ሲል ደሞ ለጉልቻ ብቻ ነው።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ድንቁ የቆመበትን ጥፍጥፍ ድንጋይ በከዘራቸው አየቀወሩ።

ከዚያም "ቡሄ ግን በብዙ ይለያል። አዲስ ጎጆ ወጭዎች ለጉልቻ የሚጠቀመበት ተራ ድንጋይ አይደለም። ምሥጢራዊ ድንጋይ ነው። ማዕድንነት ካላቸው የድንጋይ ዘሮች ጋር ሲመደብ አይችልም። ቀደም ብዙ እንዳልሁት ማንኛውም ሰው ከዚህ ድንጋይ ላይ ቁጭ ሲል ጉሁ ምሥጢር ከፊቱ እየመጣ ይረገረግለታል። ይህ ጥበብ ከፈጣሪ ለሰዎች ልጆች የተሰጠ ምሥጢር ነው። በተለይ ኢትዮጵያ አጀጋን ወደአግዚአብሔር ዘርግታ የተቀበለችው ድንቅ ምሥጢር ሲሆን ምንጩ

PDF Compressor Free Version

ቡሔ ድንጋይ ይባላል። ስመ ጋኔን ነገራደብተራ ወይም ድግምት አይደለም። ከመፀኑትና ከጠልሰም ጋር የተያያዘ ነገር የለበትም።

በሥነ ፍጥረት ታሪክ ለመጀመሪያው ሰው ለአዳምይህ ቡሄ ድንጋይ ተሰጥቶታል። የተሰጠው ግን እግዚአብሔር መልካም አድርጎ የፈጠራቸውን እንዲያይበት ብቻ ነበር። ሰይጣን መጥቶ የሞታን ፍሬ እንዲበላ ሲነግረው ድንጋዩ ተሰወረበት። ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ጠፋበት።

ኋላ የአዳም ልጅ ክርስቶስ ለአዳም ዘርመድኃኒት ሆኖ ወደዓለም እንደመጣ በደብረ ታቦር ወጥቶ በዚህ ቡሄ በሚባል ብርሃናዊ ድንጋይ ላይ ቆሞ ብርሃነ መለኮቱን ገለጠ። ከዚያ ወዲህ ቡሄ የተባለ ድንጋይ ላይ ለቆመ ወይም ለተቀመጠ ምሥጢር ይገለጥለት ጀመር። ጌታችን ድጋሜ ባርኮና ገልጦ ሰጠን። ቡሄን እንደ ገና ገለጠልን። ሩሐም የተባለውን የሞት ድንጋይ ከነደብዳቤ አቅልጦ አጠፋው።

ዛሬ በደብረ ታቦር በዓል ሲመጣ ተራራ ላይ ወጥተን " ቡሄ በሉ ቡሄ መጣ" እያልን የምናዜመው ያንን ክርስቶስ ቡሄ ደንጋይ ላይ ሆኖ ብርሃነ-መለኮቱን መግለጡን ለመዘከር ነው። የጅራፉ ብልጭታ ደግሞ የብርሃኑን ፍንጣቂ ይነግረናል። ዋናው ምሥጢር ከዚህ ላይ ነው።" አሉ ሊቁ ወደገሞራው በአጭፍ ከዘራቸው እያመለከቱ።

ገሞራው ዐይኖቹን ጨፍኖ ተከታተላቸው።

አጭር ከዘራቸውን ተደግፈው ቀጠሉ።

"ይኸንን ምሥጢር የሚያውቀው ተዋነይ "ከቅኔው ውስጥ ቡሄ የሚባል የቅኔ ዜማ ልክ አኖረ። የዛሬ ዘመን ደብተራ ባልተለመደ ቃል ዜማ

PDF Compressor Free Version

ልኩን ቢሄ እያለ ሲጠራው አሰማለሁ። ዋና ስሙና ምሥጢሩን ነግ
በሐ አንጂ ቢሄ አይደለም።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ድንቁ።
ለጥቀውም "ተዋነይም ሆነ ሌሎች ከተዋነይ ወዲህ የነበሩ ሊቃውንት
በሁሐ ድንጋይ ተጠቅመውበታል" ብለው አጭር ከዘራቸውን ወደህዋ
ከፍ አረጓት።
ገሞራው የሰማውን በማመንና ባለማመን ማዕበል ሲገፋ ቆይቶ
"እና ቡሄ ከዚህ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ውስጥ አለ እያሉኝ?" ነው አለ።
ብዙ አታስወሽቱኝ! እንደዘመኑ ትውልድ ጠልፈህ ለመሮጥ እንጂ በቀ
አውቀት ለማግኘት የመጣህ አትመስለኝም። የቅኔውን የምስክር ወረቀት
ከሆነ ፍላጎትህ አሁኑኑ በማጎተም አትሜ አሰጥኻለሁ። ዛሬ የምስክር
ወረቀት እየሰበሰቡ ይሆንን አውቃለሁ ያንን ተምሬለሁ እያሉ ማውራት
ቀላል ነው። ከባዱ ነገር የተናገሩትን ሆኖ መገኘትና በተግባር መገለጥ
ነው። የትምህርት ቤቱን በር ሳይሳለሙ የምስክር ወረቀት እየገዙ
የሚሰበሰቡ ብዛታቸው ጨምሯል። ነገር ግን ገዝ ብሎ ሳይማሩ ወረቀት
መሰብሰብ ዝሙት ነው።" ሊቁ ፋሬስ በክራል አዲሱን ትውልዱ ነቀፋ።
"አሯ! የኔታ? አመጣጤ ለመማር ነው። የምስክር ወረቀት ፍለጋ
አይደለም። ልሙጥ ወረቀትና ልሙጥ ጭንቅላት ተሸክሜ ጉራ መንፋት
አልፈልግም። ጠራ ያለ ሊቀ ሊቃውንት መሆን ነው የምፈልገው።
ወደፊት ዐራት ዐይና ሊቅ እንኳን ብሆን ለስም አልኖርም።" አለ
ገሞራው።
"እንደሱ ነው የኔ ልጅ! እውቀት የሚፈልግ ተማሪ ሲመጣ እናቱ
ከመቃብር አምልጣ እንደመጣች አቆጥረዋለሁ።

PDF Compressor Free Version

ጀሆን ታኽል የመማር ፍላጎት ካለህ አብረን እንዘልቃለን።" አሉ።
እናም "ሁሌ ድንጋይ ኢትዮጵያ አፈር ውስጥ መኖሩን አምኔ ልቀበል?"
አለ ገሞራው።
የገባህ መስሎኝ እኮ ነው?
ቡሄ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል እንዳለ ይታመናል። በጎንጅ ደብረ-ጥበብ
መኖሩን እኔ ራሴ ..." የኔውን ተወውና አባታችን ተዋንይ "ቡሄ ላይ
ቁጭ ብሎ መወድስ ቅኔ ይዘርፍ ነበር። ወደቡሔ የሚወጣው ግን
ዘወትር አይደለም። ከዓመት አንድ ቀን የደብረ ታቦር ዕለት ብቻ ነው።
ቅድም ያነሣኸውን ቅኔ የዘረፈውም በደብረ ታቦር በዓል "ቡሔ ድንጋይ"
ላይ ቁጭ ብሎ ነበር" እስኪ ቅኔውን ከሥር ጀምረህ አምጣው።" አሉ
ሊቁ ፋሬስ።
"ዋሌትኛውን?" አለ ገሞራው። "ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ" ያሰውን ቅኔ
ከሥር ጀምረኽ ታውቀዋለህ? ወይስ ጫፉን ብቻ ነው?" አሉ ሊቁ።
አሯህእንደኑት ሰለሉኝ? ከሥሩ አመጣዋለሁ አንጂ ብሎ ወደኖቹን ጨፍኖ
አመጣው።
"የአምን ወደኀኒ ኩሉ ዓለም በዘፈጠረ ለሊሁ።
ብዙኃን እለ አምኑ ይስግዱ ቅድሜሁ።
ነጽሮተ ዝኒ ነገር ከመ እስራኤል ይፍርሑ።
ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ።
ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ።" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

ሊቱ ፋሬስ የተሞነይን ቅኔ ሲያብራሩለት አስበው ተውት፣ ወደ ቤቱ ማብራራያ ገቡ። በራሳቸው ቅኔ ውስጥ የተቋጠረውን መፍታት ጀመሩ።

"አቡሀ ልጀ! ወደውስጥ ሲዘልቁ ጥልት ምሥጢር አይጠፋም። ችግራችን የአባቶቻችንን ሥራ ኋላ ቀር ብለን ንቀን ጠቅጥቀን በድንዙርን መኖራችን ላይ ነው። በዕውር ድንብሩ መመራታችን ነው። ተውልዱ የአባቶቹን አፈር መርምሮ ካንድ ነገር ሰመድረስ ሲጓጓው ወደ ባዕዳን ያንጋጥጣል። የራሱን አባዶች ሚርተኛ፣ አስማታም፣ አያለ ስው ይሰጣል። ከአባቶቹ እውቀት፣ ጥሪት መቋጠር ሲጣው ተንጋሎ ይተፋል እንጂ ነገሩማ እንዲህ ነው።

"ቡሄ ለሰው ልጅት ከፈጣሪ የተሰጠ ጥበባዊና ብርሃናዊ ድንጋይ ነው። የመጀመሪያዎች ፍጥረቶች በዚህ ድንጋይ መለኮታዊ ሥልጣኑን በጥበብ ተመራምረን እንደርሳለን ብሰው አሰቡ። ከሰዙት ሳይደርሱ ምድረ ፋይድ ገቡ። ገነት ብቻዋን ቀረች። ሞት ወደዓለም ገባ። አንድዬም በደላቸውን ሩካም በሚባል ድንጋይ ጽፎ ከገነት አስወጣቸው። ዓለማዊ ጥበቡን ደሞ ቡሔ በሚባል ድንጋይ ቀርፆ ሰጣቸው። ዛሬ ዘመናውያን ሊታወኑት በምርምር ደረስንበት እያሉ የሚያላዝኑት ከዚች ጥበብ ከሰናፍጭ ቅንጣቢዋን ሊቀምሱ ነው። አባቶቻችን ግን ቀድም ብለው ደርሰውበት ነበር። "ቡሄ ወደ ቡሄ ትሰባለች" ያልሁት ይህን ነው። "ታዲያ ድንጋዩ ካለ ጥበቡ ከወዴት ገባ?" አለ ገሞራው ሲፈራ ሲቸር። "ከወዴት ይሄዳል? አለ አንጂ" አሉ ሊቁ ::

PDF Compressor Free Version

ንሙች የኢትዮጵያን ክርሠ ምድር እንደፋር የማያርሱት ሰምን ይመስልኻል? ያንን ፍሊጋኮ ነው፣ ታዲያ የፍልፈለ አፈር ወደ ሀገራቸው ለልኩ ነውን? ሀገራቸውን ትተው ወደሀገራችን የመኑት ደብረ ጻሞ ያህም ገብተው ለመጽደቅ ነው ብለህ ከሆነ "ጓዲኽ ናፅት" አሉ። ገና ያልበሰለ ቀጣ ነህ ማለታቸው ነው።

ትናንትና ቅኔውን በዚህ ክ፡፫ ነገር መዘረፍ የፈለግኩት በኢትዮጵያ መኖሩን ለመግለጥና ምን አልባት ከዚህ ሁሉ ወፈ ሰማይ ተማሪዎቼ አንቱ የዘህ ምሥጢር አዋቂ እንደሆነ ለመገመት ነበር።" ብለው ወደጓኡ ለመሄድ ተነሡ። ገሞራው ፈገዘ ቀረ።

PDF Compressor Free Version

፳፱

ዐርብ ጌታ ፍጥረታትን ፈጥሮ የፈጸመበት ቀን ሲሆን በሊቁ ፋሬስ ቅኔ ቤት ግን በሳምንት በሳምንት የቅኔ ዘርፍ ይፈጠርበታል። ሊቁ ፋሬስ የቅኔ ዘራፊዎች ቅኔ ዘርፈው እንዲነግሩ በጉባኤ ተሰየሙ። ገሞራው ለሊቁም አስቸጋሪ ተማሪ ከሆነ ሰንብቷል። ከልጅነቱ ጀምሮ የሚያውቃቸውን ትውፊትም ሆነ ባሕላዊ ወጥጉን በቅኔ ዐይነ ይመለከታቸዋል። ሊቁ ፋሬስ አንዳንድ ቀን በመወድሱ ሲበሽቁ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሰምና ወርቁ ሲስቁ ይውላሉ። ብሽቀታቸው ገሞራው ከአሳቸው ላቅ ብሎ በሊቃውንቱ ዘንድ እንደ አንድ ልዩ ክስተት መታየቱ ነው። ፍሥሓቸው ደሞ ገሞራው የባጡንም የቆጡንም በቅኔው ውስጥ እያመጣ ስለሚያስደስታቸው ነው። በዛሬው ጉባኤም አዲስ ምሥጢር እንደያዘ ገጹ ይናገራል። ሊቁ እንደተለመደው "ይመሐረን ወይሴሐለነ ለሊቃውንት የገለጸ አምላክ ለእኛም ቅኔውን አንባቡ ጋር ይግለጽልኝ" ብሎ አንድ አቡን ዘበሰማያት ደግመው

"በል አያ ገሞራው?" አሉ ካበርታቸውን እያስተካከሉ።

ገሞራው እንደ ልማዱ ተሸለጠ። ዐይኖቹ ተስለመለሙ።

መጀመሪያ እንደ አውራ በሬ አግሣ። ጠዲሀም መንጎራደድ ጀመረ። ሲንጎራደድ የሊቁ ዐይን ኦብር መንጎራደድ ጀመረ። ለስፍታ ያኽል ተንጎራድዶ ሰውነቱ በቅኔ እሳትነት መፍላት ሲጀምር፣

ተንሥእ ጴጥሮስ ዘኢትዮጵያ ሰማዕት፤
አምጣነ ባዕዳን ሆክዋ ለሀገርከ ሠናይት"

PDF Compressor Free Version

ለሰ ገሞራው እንደ ልማዱ። ቅኔዉን ተክትሎ አንገቱ ላይ ያለው ሥር ሲወጠር ከናፍሮቹ ሲረግቡ ሰተመለከተው ተፈጥሮና ቅኔ ድጋሜ እንደ ፈጠራት ያሳብቃል። ተፈጥሮ የቅኔ ለው አድርጋ ስትፈጥረው ቅኔ ደግሞ የሌለ ውበት ትደራበታለች። ሲመራመር ሲውል መልኩ ከሰማይ የወረደ መልአክ መስሎ ይውሳል። ምርምር ሲርቀው ደግሞ ፊቱ በረዶ እንደ መታው ማሽላ ዱው ብሎ ውበቱ ጠፍቶ ገጹ የተጠበሰ ጉበት ይመስላል። ዝዘኑና ፍሥሓዉ የተለከ ናቸው። ቅኔ ሲመጣለት ድርሰት ሲገለጥለት እንደ ናርዶስ ያሸበርቃል። መወድስ ሲሰወርበት እንደ ፅፀ ዘንቱ ኂ ብሎ ይከሰማል።

ሲቀ ፋሬስ በዚህ ቅኔው ውስዮ አዲስ ምሥጢር ማፈላለግ ጀመሩ። ገሞራው የወረወረው ሁሉ ምሥጢር እንደሆነ ያውቃሉ። በተለይ የኢትዮጵያው ሰማዕት አቡነ ጴጥሮስ በቅኔም ሆነ በታሪክ ሲወሱ በሲቀ ፋሬስ ዐይን የእንባ ጅረት ይቀዳል።

ሲቀ ፋሬስ የገሞራውን ቅኔ በጉጉት መጠበቃቸው ወድያው አያደለም። ተገድደው ነው። ገሞራው በአብነትትምህርት ውስዮ ያልዳሰሰውምንም ውስጠ-ምሥጢር እንደሌለ በቅኔው ውስዮ ሲመለከቱ ሰንበትበት ብለዋል። ከቅኔ ቤት ሕግ ወጣ ያለ ጠባይ ያለው መወድስ መፍጠሩንም ተረድተዋል። ገሞራው በአብዛኛው ጊዜ በጸድቃን በስማዕታት ክብር ከሚዘርፋቸው ቅኔዎች በተጨማሪ ከእኒህ ታሪክች ወጣ ያለ ሀገራዊ ፍልስፍና ተጠናውቶታል። ቅኔዎቹ እንደ ክፍለ ዮሐንስ ዘትንደር ቅኔ ሰፍልስፍና ሰባሕልና ለሊነ-ጥበብ ቀረብ ያሉ እንደ ሆኑ አፍ አውጥተው መናገር ጀምረዋል። ሲቀ ፋሬስም በዚህ ሁኔታ ግራ መጋባት ቢጀምሩም

PDF Compressor Free Version

በግድ እየተቀበሉት ነው። ሁለት ሦስት ቀን ግን በትኔው ምሥጢር ዳሳ
ቀረሽ ጠብ ውስጥ ገብተው ነበር። ጸብ ውስጥ ያስገባቸው ከተለመደው
ወጣ ያለ ምርምር ይዞ ብቅ ይልና በሊቁ ፊት ይንበተበቃል ወጣቱ ባሉ
ቅኔ ገሞራው። ሊቁ ከተለመደው የቅኔ ሕግ ሲያልፍ፡ "አይልም ይላሉ።
ወይም "አንለውም ሲሉ ራሳቸውን አንቱ ብለው ይጠራሉ። ገሞራው
አመክንዮ እየጠቀሰ ይከራከራቸዋል። ሊቁ ይረታሉ። ሊረቱ ክብራቸውን
የተጻፈረ እየመሰላቸው ቱሎ ቱሎ ቱግ ይሉ ነበር። እየቆዩ ግን
እየለመዱት መጡ። የቅኔውን አመሳጥሮ ለመረዳት እንጂ የሊቁን
የእውቀት አድማስ ለመለለል እንዳልሆነ ሲረዱ በእውቀቱ ላይ
የሚያውቁትን ምሥጢር እያነሱ መከራከር ጀመሩ። እንዲያውም እየቆዩ
ተማሪዎቻቸውን ሲመርቁ፣

"ቅኔ ከሚመስል ግጥም።

በረዙት ከሚመስል መርገም ራሳችሁን አድኑ ሲሉ መምከር ጀመሩ።
"ቤት የሚመታ ግጥም ሁሉ ቅኔ አይደለም። ንግግር ሁሉ ስብከት
አይደለም። ቅኔ ከቀሲሳን ልቦና የሚደገኝ ፍልስፍና ነው። ስብከትም
አቃል አዋቂዎች የራቀ የሕይወት ክፋይ ነው።" ብለው ማስተማር
ጀምረዋል።

ገሞራው እንደበጥባጭ ቅኔ ዘራፊዎች እየተንጎራደደ ቅኔውን
አደጋገመው ቦጋለ "በል እስኪ ፍታው?" አለ ሲቱ ባለ ቅኔውን
እየተመለከቱ።

ገሞራው

PDF Compressor Free Version

"..ተንሥኤ ጴጥሮስ ዘኢትዮጵያ ሰማዕት
አምላኔ ባዕዳን ሆነዋ ለሀገርከ ሠናይት።"

ብሎ ያመሰጣን ቅኔ ወደ አማርኛ ሲተረጉም እንዲህ ነበር ያለው።

"..ያሞት ሐዋርያ የጦቢያ ሰማዕት፣
ባዕዳን ሀገርህን እንዳይወጠጡጧት፣
ተንሥልን ጴጥሮስ አትሙት በኔ ሞት፣
ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ቀንሶበው ለመብላት.."

አለ ገሞራው ግእዙን ወደ አማርኛ እየተረጎመ።

ሊቁ ፋሬስ የመርጨረሻዋን የግጥም ሐረግ መዘነው ለመሆኑ "የሕይወት ዛፍ በኢትዮጵያ ምድር መኖሯን ታቅናለህ?" አሉ። ማመንም አለማመንም ይከብድ ይመስለኛል። በግሌ ወራው ለምን እንደሚወራ ለማወቅ የኢትዮጵያን ሽለቆዎች በከፊል አዳርሻቸዋለሁ። አሁንም ገና አግራ ያልደረስበት፣ የምጠረጥረው ስፍራ አለ ወደእሱ እሄዳለሁ።" አለ ገሞራው።

"እሷን ለማግኘት ነው?" አሉ ሊቁ።

"አዎ"

"ለመሆኑ እስካሁን ከሀገራችን ክፍል በሄት በሄት ዙረኻል?" አሉ ሲቄ። በትክክል ርሳቸው የሚያውቁትን ያውቅ ይሆን ብለው ተጠራጥረው።

"ቀሩኝ የምላቸውና የምጠረጥራቸው ሽለቆዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው።" ብሎ በሕሊናው ትኩረት ሰጥቶ የዞረባቸውን ሽለቆዎች ማሰላሰል ጀመረ። ወዲያውኑ ግን የወጣ የወረደባቸው ሽለቆዎች ትዝ አሉት። አስቀድሞ የመረደው ዐባይ ሽለቆ ነበር፣ የዐባይ ሽለቆ ከሰሜናዊ የሀገራችን ክፍል

PDF Compressor Free Version

ጀምሮ እስከ-ጥቁር ዐባይ የሚደርስ ቢሆንም ቅሉ ገሞራው ግን በጎ
ጽዮንና በደጀን መሻል የሕይወት ፍሬን የሚያውቁ ሊቅ እንዳሉ በመሬ
ሰምቶ የተንከራተተባቸው ሽለቆች አንድ ባንድ መጡለት።
"ለምሳሌ ጎሠሣ የጀመርኩት በዐባይ ሸለቆ ነው። ከማውቀው ሀገር
ልጀምር ብዬ በደጀን በኩል ወርጀ በጎሐ-ጽዮንና በደጀን በኩል ባለው
የዐባይ ሸለቆ ሐሠሣዬን ጀመርሁ።" አለ ገሞራው።
"ለምን አሉን አስቀደምህ?" አሉ ሊቁ ለምክንያት ይመቸኝ ብለው።
"እንደሚታወቀው ዐባይ ሸለቆ በደጀንና በጎሐ-ጽዮን አድባራት ተከበ
ይኖራል። በቅርብ ቀን የተሠራው የዐባይ ጠመዝማዛ መንገድ በውስጡ
ገቡኦ ምሥጢር አርግዞ ከፊት ለፊቱ ተንጥፏል። ከጎሐ ጽዮን እስከ
ሕዳሴው ድልድይ የተሠራው መንገድ መፈረካከስ የጀመረው ገና
ተሠርቶ ላይመረቅ ነበር። ከዐባይ ወዲያ ማዶ ከደጀን እስከ ዐባይ ያለው
መሥመር በግንባታ ላይ እያለ ከጎሐ ጽዮን ወዲህ ማዶ ያለው
መሰነጣጠቅ ጀመረ። ነፍጭ ይህንን መንገድ ለመሥራት ረጅም ጊዜ
እንደማይፈጅባቸው ግልጽ ነው። ይህን ያኽል እንደ ዐመተ-ፍዳ
እድሜዉን ያስረዘመበት ምሥጢር ከጀርባው ሌላ ውስጠ-ወይራ
እንዳለው ገምቼ ነው።" አለ ገሞራዉ።
ሊቁ በአንክሮ ቀና አሉ።
ገሞራዉ በትሕትና እንገቱን ወደ መሬት ዘንበል አድርጎ ቀጠለ።
"እኒህ ባዕዳን በተለያዩ የሥራ ዘርፍ በመጡ ቁጥር የኢትዮጵያን
ምሥጢርና ጥበብ ለመቧጠጥ የማይፈነቅሉት ትክል ድንጋይ እንደሌለ
ዝንተ-ዓለም ይወራል። እኒም በውስጡ ጣሊያኖች ላይቀር ጠባቂ

PDF Compressor Free Version

መልአክ መስለው የሚያነፈንፋት ምሥጢር አንዳስ ስለሰማው ጉዞዉ ወደዚያው ሆነ። በተለይ ጣሊያኖች ድሮ በጦርነት ሲጠቁ ዛሬ ደግሞ በልማት ስም በዐባይ ሽለቆ ውስጥ የሕይወትን ፍሬ ለመረከብ ጉንዳን እንደሚፈልግ ገመሬ ዝንጀሮ ድንጋይ ይፈነቅላሉ ይባላል። እንግዲህ ድሮ አባቶቻችን በቶፋና በጋን የቀበሩትን ወርቅ ዝር። ከዚያ ሚጥጠው ከወሰዱት ወርቅ ጀርባ ላይ ደግሞ አንዳንድ ምሥጢራት እንደተጻፋበት የታወቀ ነው። ያንን ጽሑፍ ከወርቁ ጀርባ ወደወረቀት አውርደው ጽፈው ወደ ሀገራችን መጥተው በአሐሱ መሪነት የሀገራችንን ከርሠ-ምድር እንደሚበረቅሱ ሀገር ያውቃል። በዚህ ሰንድ እየተመሩ ወርቁና ብሩን አንጉዘው ከጨረሱ ወዲህ ደግሞ የመዉረሻውን ነሠሣ እየሠሩ ይመስለኛል። ማዕድናቱ ተማጠው ሲያልቁ የሕይወትን ፍሬ ማደን ጀምረዋል። የኢደኑ መጀመሪያ ደግሞ የዐባይ ሽለቆ እንደሆነ የሚገምቱ ጠቢባን አሉ። መቼም ማዕድኑን ተቀራምተው በልተውታል። ከሕይወት ፍሬ በቀር ሁሉንም ነገር መሸልቀው መስደውታል ይባላል። የቀረቻቸው የዛፏ ፍሬ ብቻ ናት የሚሉም ሰዎች ገጥመውኛል።" አለ ገሞራው።

"በዚያ መኖሯን ማን ነገራቸው" አሉ ሲቄ።

"ከወርቁ ጀርባ ላይ ከተጻፉ ጥቃቅን ፊደላት በተጨማሪ በእንግሊዞች ቦርነት ጊዜ ከተዘረፉት አያሌ መጻሕፍት ውስጥ መጽሐፈ አእጋረ ፀሐይ የሚባለው ጥራዝ አንዱ ነው።

በዚያ መጽሐፍ ውስጥ "አፍዮን ወሪደ መንገለ ቆላ ወበህየ ትረክብ ዐቢየ ፈለገ ወበውስተ ውእቱ ፈለግ ትረክቦ ለፅፀ ሕይወት፣ ፈጥነህ ወደ ሽለቆው ውረድ። ወርደህም ዝም አትበል። ሽለቆውን አሥሥ። በሽለቆው

PDF Compressor Free Version

ከርሠ ምድር ምሥጢሩን ታገኝዋለህ።" የሚል ንባብ አለ። ያንን መሠረት አድርገው "ፊለግ ዐቢይ ተባለ ግዮን ነው" ብለው ምድረ ፈረንጅ ሁሉ ዐባይን እንደተከተለ እድሜውን ጨረሰው። እስካሁን ግን የሕይወትን ዛፍ ቀርቶ መዓዛዋን ያሸተተ ሳሊያናዊ ጠቢብ አልተገኘም። በእርግጥ አፅጋረ-ፀሐይ የተባለው የመጽሐፉ ዋናው ጥራዝም በሠገራችን ስለማይገኝ በእኛም ዘንድ ምሥጢሩ እስከዛሬ ገና ለጥናት አልቀረበም።

"ታዲያ ይህ በሌለበት ለምን ደከምህ?" አሉ ሲቄ።

"በእርግጥ ወደ ሥፍራው ስሄድ ሌላ ተልካሻ ምክንያትም ነበረኝ" አለ ገሞራው።

"ምን ነበር?" አሉ ሲቄ ደስ በሚል ድምፃቸው።

"ዝሰሚ ስሚ እንደ ስማሁት ዕው ከዐባይ ድልድዮች በአንዱ ሥር አንዲት ይገመታል። በብሰይ በሳሊያን ጊዜ የተሠሩ ድልድዮች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። በቅርቡ በሕዳሴው ድልድይ የተተካው የጥንቱ በሳሊያን የተሠራው አሮጌ ድልድይ የንሠሣዬን ከፍተኛ ድርሻ ይይዛል።" ገሞራው ጉድ ፈለፈለ።

"ለምን?" አሉ ሲቄ።

"ቀድሞኑ ድልድዩ የተሠራው ለዚህ ምሥጢር እንደሆነ የኢትዮጵያን ምሥጢር ጠንቅቀው የሚያውቁ ሊቃውንት ያውቃሉ። ድልድዩ ክልታጣው በታ ከጥንቅሩ ውስጥ የተጠነቀረው ለዚህ ጉዳይ ታስቦ ነው ይባላል። ጃንሆይም ሆኑ ጓድ መንግሥቱ በድልድዩ ስም የሕይወትን ፍሬ በወታደር ለማስጠበቅ የተጠበቡበት ለዚህ ዐቢይ ምሥጢር ይመስለኛል። ወዲህም ሣሊያንም ይህን ድልድይ ከታላቁ ኑረብታ ሥር

PDF Compressor Free Version

ወደዱ የወሸቀው ወድዶ አይደለም። በእረፋሽስት ዘመቻ ወቅት በላይ ዘለቀ ከዚህ ውስጥ በዕፀ መሰውር እየተሰወረ እንደ ወጋው ዐውቆ እንደምንም የበላይ ዘለቀን ጥበብ ተጠቅሞ ድጋሜ ኢትዮጵያን ወግቶ የሮምን ልዕልና በአደባባይ ለመስበክ ነበር። መቼም ጣሊያን ከዐባይ ሽለቆ ውስጥ ድልድይ ለመሥራት የወሰነው ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ብቻ እንዳልነበረ ግልጥ ነው፤ ሕዝቡን ድልድይ እየሠራሁ ነው ብሎ አታሎ ፍሬዋን ለመጠቀም ነበር። ሕልሙ ቅዠት ሆነበት። የሀገሬ ጠቢባን ጥበባቸውን ተጠቅመው ሕልሙን እንደጉም አተነኑት። ምሥጢሩን ጋረዱበት። በሌላ ጊዜ ንጉሡ ያንን ድልድይ ሲሳበኙ ምሥጢሩ ተነገራቸው። ንጉሡም የጠቢባኑን እውቀት ለመፈተን ይህን እንዲያጠኑ ጠቢባኑን እየላኩ አንድ በአንድ አስፈትሸውት ነበር። ሊያገኙት ግን አልቻሉም። እየቆዩ ይህንን ምሥጢር ለማግኘት በላይ ዘለቀን በድብቅ ቢለምኑት ፊት ነሣቸው። ተናደው ስቅላት ፈረዱበት።" አለ ገሞራው።

ሊቁ እንባቸው ዱብ ዱብ ማለት ጀመረ። ልማዳቸው ነው። በበላይ ዘለቀ ስቅላት ደም ያነባሉ። ስለ ዐጤ ቴዎድሮስ ሞት እኻር ያፈሰሱ። የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስን በመትረጊስ መደብደብ ሲያስቡ ታመው ይሰነብታሉ። በተለይ አንድ ጊዜ አዲስ አበባ ዘልቀው ሲመለሱ የአቡነ ጴጥሮስን ሐውልት ከነመትረጊሱ ባዩ ሰሞን ታመው ነበር። ከዚያም እንባቸውን እንደምንም ለመቆጣጠር ሞክረው ሲያቅታቸው ከኪሳቸው መሐረባቸውን አውጥተው ዐይናቸውንና አፍንጫቸውን በመሐረባቸው እየጠረጉ "ወይ ይች ዓለም! ወይ ይች ኢትዮጵያ! ስንቱን ጀግና በላችው!" ብለው ተደነቁ።

PDF Compressor Free Version

ገሞራው ግን የሊቁን የአንባ ጠቢታና አንክሮ ከመጤፍ ሳያቆጥር በቅኔው ስላመጣው ጉዳይ ማብራራት ቀጠለ።

"የሆነው ሆኖ የሕይወት ዛፍ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በዐታው እንዳለ በወግ አዋቂዎች ዘንድ ይነገራል። እኔም ቦታዋ ድረስ ደርሼ ነበር። በወቅቱ አንድ ሐረ የሚባሉ በሕይወት ዛፍ የሚጠቀሙ ሊቅ አንተው ስምቼ በአግራ አዘገምሁ። ስደርስ ጋራው በሠራዊት ተከቧል። ከዚይህ አይቀር ብዬ ወደአንድ ወታደር ጠጋ ብዬስለ ሰውየው መኖርና አለመኖር ጠየቅሁኝ። ወታደሩ ግን በጎ ምላሽ አልሰጠኝም። ወደዚህ ምን አመጣህ? አንተ አሸባሪ ብሎ አፈጠጠብኝ። "የእግዜር አገልጋይ ዲያቆን ነኝ" ከዚህ ከሩፋኤል ገዳም ውስጥ የሚኖሩ አባት እንዳሉ ሰምቼ ልጠይቅህ ፈልጌ ነበር አልሁት። ወታደሩ መታወቂያዬን ተቀብሎ በሞንቅ አንብቦ የቋጠረውን ግንባሩን ፈታ አደረገው። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ እንደገና ቋጠረው። አያይዞ ግን ሰውዬው ለስመ ከዚህ አሉ ይባላል እንጂ የሚኖሩት ሌላ ቦታ ነው። ወደ ሽለቆው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ብቅ ይላሉ አለኝ።" አለ ገሞራው

"ሰውዬው ማን ነበሩ?" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ዮተለየ ስምና ሀገር የላቸውም። ሀገራቸው ኢትዮጵያ የጥበብ ስማቸው ደግሞ ሐረ ይባላል። እንደሚባለው በዚህ ሽለቆ ውስጥ መኖር ከጀመሩ ብዙ ዓመታት አልፈቸዋል። ሐረ ከሰማይ ብር ያወርዳሉ። ንዋይ ከሰማይ ያዘንማሉ ይባላል። ወዲህም በጥበብ ተጠቅመው በደመና ይጫናሉ የሚል መላ-ምትም አለ። በቅኔ በክል ግን የተመሰከራለቸው ሊቅ ናቸው። ቅኔ ዘረፋ ከጀመሩ ሰማይ ምድሩ ይጠባቸዋል።

PDF Compressor Free Version

እንዲያውም ሲሞቱ ተሰላችውን ለኢትዮጵያ ሲቃውንት አወርስዋለሁ ሲሉ ተናዘዋል አሉ።" ገሞራው ለማመን የሚከብድ ምሥጢር መሰለ። "እንዴት? እንዴት?" አሉ ሊቁ።

"እንደ ስውዱው አገላለጽ ከሆነ ዕለተ ሞቱ ሲቀርብ ዐባይ አወርዳለሁ። አማሮቼን በዐባይ ውኃ እታጠባለሁ። ለሳምንት ብቻ ውኃውን ለጠጣ ምሥጢር ይከሰትለታል። ያን ጊዜ ወንዙ በጥበብ ይሞላል። በዚያ ለምንት ግዮንን ለጠጣ ቀርቶ በዋና ሲሻገር ገላዉን ለነካው ሁሉ ምሥጢርና ጥበብ ይገለጥለታል ሲሉ ያወራሉ። ጊዜ ገጥሞት ከጠበሉ የተነነጨ ፍጡር መልአክ ሞትን አውግዞ ለሰባት መቶ ዓመት ያክል በሕይወት የመኖር መብት ይሰጠዋልም ብለዋል።" ካለ በኋላ ታዲያ ምን "ያደርጋል? መንግሥት እስክ ዝግንትላቸው ወርሶ የቁም እስረኛ አድርጓቸዋል። በወታደር ተከብበው እንደሚኖሩ ተረድቻለሁ። ሆኖም ተስፋ አልቆረጥሁም እንደ ምንም ለአንድ ጊዜ ባገኛቸው ብዬ አንዳንድ ምሥጢራዊ ስጦታዎችን አዘጋጅቼ ነበር የሄድሁት።" አለ ገሞራው።

ሊቁ ፋሬስ ይህንን ታሪክ በጽሞና ሲያዳምጡ ቆይተው

"እሱን ሐተታ ተውና በቅኔው ውስጥ፤

ተነሥልን ጴጥሮስ አትሙት በኔ ሞት።

የሞት ሐዋርያ የጦቢያ ሰማዕት

ባዕዳን ሀገርህን እንዳይቦጠቡጧት

የሕወይትን ፍሬ አሥሠው ለማግኜት።" ያለውን የቅኔ ክፍል ብቻ አብራራው አሉ።

ገሞራው ቀጠለ።

PDF Compressor Free Version

አቡነ ጴጥሮስ ለሀገራቸው ሲሉ ሞትን ፊት ለፊት የተጋፈጡ አቡን ናቸው። ከዚያ ወዲህ ኢትዮጵያ እሳቸውን ያኽል አቡን ሳታገኝ ከዚህ ደረሰን። በዚህ ዘመን አቡነ ጴጥሮስ ቢኖሩ አለዚያም አቡነን በሰማዕትነትም ሆነ ሕገዘቡን በትክክል የሚያስተምር መንግሥትን የሚገስጽ ተተኪ አቡን ቢገኝ ሀገር የሚበረቅሱ ዕፀ-ሕይወትን የሚያሥሙ መቼ በመኻል ገብተው ይከፋፍሉን ነበር። ለዚህ ነው "ተነሥልን ጴጥሮስን የምዘምረው።" አለ ገሞራው።

"የሆነው ሆኖ ቅኔው ሸጋ ነው። ሕዋያንንም መታንንም እንዲሁም የጠቢባን ሕይወት ይዳስሳል። ለዛሬ ጉባኤም ይመጥናል። ስለዚህ ሌላ በል። ቅኔውን ተቀበያለሁ።" አሉ ሊቁ።

ገሞራው እጅ ነሥቶ ለመሄድ ሲዘጋጅ ና ወዲህ ብለው ከፊታቸው ቁጭ አድርገው።

"ወደ ፊት ይህን መሰል ቅኔ ይትርብህ። ዐይን ውስጥ ትገባለህ። ሲጀመር የሕይወት ዛፍ ነገር ሀገራዊ ምሥጢር ነው። ቢገኝ እንኂን ክፉ መዘዝ አለው። ወደ ሀገራዊ ምሥጢር ዘው ብለህ አትግባ። ዘመኑ ክፉ ነው። እድሜህ ያጥራል። ሖረን አታንሣ" ብለው ከመከሩት በኋላ "በል ሰላም ሁን" ብለው ስለ ጠቢቡ ሖረ ጥቂት አሰላሰሉ። ከጎንደር መደወያ ሽሉቆ ምን መሰደው?። ችግር ገጥሞት ይሆን?" እያሉ የዕለቱን ጉባኤ ፈጽመው ቤታቸውገቡ።

PDF Compressor Free Version

ጠቢቡ ሖረና ሲት ዕፅቱ ከአንገረብ ወደ ቤታቸው እንደ ተመለሱ ሲቱ ሲት ዕፅቱ ደስ የምትል ሽሮ መሠራት ጀመሩ። ብረት ድስቷን ጥደው በቀኝ እጃቸው መጽሐፍ እያነበቡ በግራ እጃቸው ሽሮዋን አያማሰሉ ያንን ጉዳይ ያወቡ ያወርዱ ጀመር። ከአንገረብ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ሁሉቱ ጠቢባን በዝምታ ነበር። አሁን ግን ሲቅ ዕፅቱ ዝምታውን ሰበሩት።

"ጉልበቱ እየደከመ አንደበቱ እየተሳሰረ ስለመጣ ይህንን መጽሐፍ ልቀበረው አስቤ ነበር። ስለመጣህ የሐሽማሎች ጥበብ በአንተ እጅ ይቆይ ዘንድ ፈጣሪ ፈቅዷል ማለት ነው።" አሉ ሲቅ ዕፅቱ።

"መቼ ውኃዋ ተገኘች ብለው ነው?" አሉ ጠቢቡ ሖረ በቀቢፀ ተስፋ።

"እኔ ውኃዋን ላልጠጣ ልጠራ እችላለሁ። አንተ ግን ገና አጉልበት ነህ። ወጥተህ ወርደህ የ" ከመ ታእምር"ን ቀመር እየቀመርህ ከሰሜን ጎንደር ጀምሮ ያሉ አንቅዕትን ማሠሡን ማፋበት። ዝርዝራቸው እነሆ ብሎው ከመጽሐፉ ላይ በቅደም ተከተል የተቀመጡ የጎንደርን ምንጮች ተራ በተራ ማንበቡን ቀጠሉ። ቀሃ አንገረብ መገጭ ማይ ዳግም ፈጨፈጭ የልደታ ውኃ... ወዘተርፈ።

እኒህ ሁሉ ውኃዎች የጎንደር ትሩፋቶች ናቸው። እኒህ ዛሬ ላይ በዐይን የሚታዩ ሲሆኑ ወደ ውስጥ ተቀፍረው የተቀበሩት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው። ዝርዝራቸው እነሆ፦

PDF Compressor Free Version

አሳምንት ሦስት ያለዚያም ሁለት ቀን ብቻ ነበር። ትሕርምት ያበዙ ጀመር። ኋላም መጽሐፉን አንበብው እንደጨረሱ አርምሞ ያዙ። አሰው ጋር የሚነጋገሩት በጽሑፍ ብቻ ነበር። ያውም አንዳንድ አስፈላጊ ነገር ብቻ ሲሆን ነው። በቀር ቀሪ ዘመናቸውን ያሳለፉት አቡሻክር በመመርመር፣ በአርምሞና በጽሙና ብቻ ነው።

ወደ መጽሐፉ ስመጣ ዛሬም ቢሆን ይህንን መናጢ አቡሻክር ለማንበብ በፀራቱ ማእዘን ያሉ ሊቃውንት ልባቸው እንደቆመ ነው። በእርግጥ ከትርብ ጊዜ ወዲህ ከሌተ-መጂሕፍት እንዳይወጣ የተከለከለ ይመስለኛል። በተለይ ከመስዕ በሚወጡ ሦስት ነፋሳት አማካይነት በደመና መሄድን ስለሚናገር...::" ገሞራው ምሥጢር ሊያመልጠው ሲል አፉን ያዘ። ታሪኩ መስማቱን ቀጥሏል።

ቸሩ ቶማስን ግን እንቅልፍ እልም አድርጎ ወስዶታል።

ገሞራው ግድግዳውን ደገፍ ብሎ በማብራራት ንፋብት።

"እናም ተክለ እግዚአ ቀን ቀን ተራ ሰው መስለው ቁልቋል ሰቁልቋል ሊዘዋወሩ ይውላሉ። ወደ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ አቡሻክራቸውን አውጥተው ይፈላሰፋሉ። መጽሐፉን ሲያነቡ ይቆዩና ዐይናቸውን ቀና አድርገው ጨረቃ ላይ ያፈጣሉ። ተመልሰው ወደመጽሐፉ ያቀረቅራሉ። ሰው ሲመጣባቸው ደግሞ እንቅልፍ ላይ ያሉ ለመምሰል ዐይኖቻቸውን ያስለመልማሉ። አላፊ አግዳሚው የተኙ መስሎት መነኩሴው በቁመ ያንቀላፋል ብሏቸው ያልፋል። ሊቀንታቸውን የሚደብቁት በዚህ መሰልነባሬ ነበር። አሁን ላይ ሁኜ ሳስበው እንዲህ ደፋ ቀና እያሉ ዐይናቸውን አንድ ጊዜ ከጨረቃ፣ ሌላ ጊዜ ከመጽሐፉ ላይ እያፈራረቁ

PDF Compressor Free Version

አንጸሪያ ዮርዳኖስ ሾላዩ..." እኒህ ወንዞች ቅድመ ፋሽስት ወረራ በጎንደር ክተማ ይፈስሱ ነበር። በወረራው ወቅት ግን ጣሊያን ወደ ውስጥ አስጠግቸው። የሕይወት ውኃ ከእኒህ በአንዱ ውስጥ ልትኖር ስለምትችል ጎሠሣው ከርሠ ምድርን ጭምር ያካትታል። ያም ሆኖ የሕይወት ውኃ ዐባይ በጣና ላይ እንደሚሄድ በእሷ ላይ ደግሞ ሌሎች ውኃዎች ይሄዱባታል እንጂ እሷ በውኃዎች ላይ አትሄድም። ዐባይ በጣና ላይ መሄዱ ሌሎች አንቅፅት በሕይወት ውኃ ላይ እንደሚሄዱ ያስረዳል። የዚች ምሥጢረኛ ውኃ መክስት ደግሞ ይህ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ከውኃዎች ላይ ሲወድቅ የሕይወት ውኃ በውስጡ ካለች ባሕሩ ይነዳል። ያን ጊዜ የሕይወት ውኃ በመጽሐፉ አማካይነት እጃችን ውስጥ ትገባለች። ያን ጊዜ ሐሽማል ሆነህ ጠቢባንን በሕይወት ትቀላቀላለህ" አሉ ሊቅ ዐፅቁ ::

"የሐሽማል ትርጉም ግን ምንድን ነው?" አሉ ጠቢቡ ሐረ::

"ትርጉሙን መጽሐፉ በትክክል ሥራውን ሲሠራ የሕይወት ውኃ ስትገኝ እንግርኻለሁ" ብለው ሽሮዋን ወደማማሰል ገቡ::

ሽሮዋ ትንተክተካለች:: ብረት ድስቷ በጢስ ታፍናለች:: ሊቅ ዐፅቁ ክቅኔ ትምህርት ቤት ጀምሮ ራሳቸው ወጥ ፍልቅ እያረጉ ራሳቸውን ሲረዱ ስለሚኖሩ ወጣቸው ከመልካም ሴት ወጥ ትጣፍጣለች:: ችግሩ ግን ወጥ ሠርቶ መብላት ደመኛቸው ነው:: ሽጋ ወጥ መሥራት እየቻሉ ዘወትር ጥሬ ሽንብራ ሲቆረጥሙ ይኖራሉ:: ሰውነታቸው በጣም ሲጐዳ ብቻ ከወር አንድ ቀን ሽሮ ወጥ ይሠራሉ:: በሰሞኑ ግን ጠቢቡ ሐረን በእንግድነት ለመቀበል ሽሮ በመሥራት ተጠምደዋል:: ጠጅም ቤታቸው

PDF Compressor Free Version

ውበት በሁለት መርሙስ ይታያል። ሊቅ በፅፁ መጽሀፍት ሆኖም እንደሆነ ይረዳሉ። እንዲሁም መጽ የማይመስ ሰው ቀለም ይናገራል በለው አያምኑም። ቫርዋን ሠርተው እንደጨረሱ መሳፍ ያማረ የነሳም እንቆራ አቀር። ከሦስት ቀን በፊት ከቀልድባ መደ ንገደር የመጡ ሥነሴ ለወረስት የሰሚቸው ላቢ ነው። ላቢ የሚባለውን የነሳም እንቆራ ከተመሰት በኋላ ሁሉቱ መደ የግል እሱታቸው ገቡ። ምሥጢረኛው መጽሐፍ ቢታቸውን በብርሃን መሰቀታል። ሁሉቱ ምንም ከራዝ ላይፈልጉ በመጽሐፉ ቀያይ ብርሃን ብራሳ መጽሐፋቸውን ዘርገተው ለሆዝ ይጀልፉ ጀመር። ሐሸማል በመብራትነት አያገለግላቸው ነበር። ይቅድቀን ፈጨሰግ በመንገቡ ዘርገጾታል። የጨቲቱ ውስጣዊ ክፍል በሌሳት የተያያዘች ትመስላለች።

PDF Compressor Free Version

ሰባት

ከቅኔ ዘረፋ መልስ ገሞራው ወደ መንደር ብቅ ብሎ በአንተ ማርያም እያለ ሦስት አኩፋዳ እንጀራ ለመነ። ከልመና መልስ በቆሎ በቆሎውን ከእንጀራው ውስጥ መረጥ መረጥ አድርጎ ትኩስ ቆሎ ቆላ። ከእንጀራው ጋር የተቀላቀለውን ሽንብራና ጓያ መርጦ በብረት ድስት ቢቀቅለው አንድ ቁና ንፍሮ ወጣው። ወደ ማታ ቸሩ ቶማስን ጨምሮ የቅኔ ዘራፊዎችን ብቻ መረጥ መረጥ አድርጎ ወደ ቤቱ ጠራቸው።

ቅኔ ዘራፊዎች ወደ ጎጆው እንደ ገቡ ስለ ነፍሰ ጉር ስለ ተክለ እግዚእ እያሰ ንፍሮ ማደል ጀመረ። ከዚያም ከመንደር ለምኖ ካመጣው ቅራሪ ቢጤ ጠላ እየቀዳ ጨመረላቸው። ራት በልተው ቅራሪ እየጠጡ ሳለ ገሞራው ስለ ድግሱ ማብራራት ጀመረ።

"ዛሬ የአቡሻክሩ ሊቅ ያረፉበት ዕለት ነው። ዲማ ጊዮርጊስ ሳለሁ እኔን ጨምሮ ሌሎችንም መርሐ ዕዉር ያስተማሩን ሊቅ በዛሬዋ ዕለት ነበር ያረፉት" አለ ገሞራው በዐይኑ እንባ ሞልቶ።

"ተክለ እግዚእ ማናቸው?" አለ ዓይኗው ጌዶር። በደንብ ቅኔ ዘራፊ ባይሆንም ራሱን እንደ ቅኔ ዘራፊ ስለሚቆጥር አብሮ ተጠርቶ መጥቶ ነበር።

ገሞራው ጌዶርን ቢንቀውም ከመመለስ ግን አልተቆጠበም።

"የኔታ ተክለ እግዚእ ወሎ ካፈራቻቸው ሊቃውንት አንዱ ሊቅ ነበሩ።" ሲል አመጣው-ገሞራው።

"ሊቁ የአቡሻክር ሊቅ ሲሆኑ የታወቁ መናኝ ጭምር ነበሩ። ከወሎ ወደ ጎጃም መንነው ግብአተ መሬታቸው የተፈጸመው ዲማ ጊዮርጊስ ውስጥ

PDF Compressor Free Version

ነበር። እኔም ጊዜ ጎንቻን ቢያርፉ ዲማ ጊዮርጊስ የመጻሕፍት ትርጓሜ በመማር ላይ ነበርኩ።" አለ ገሞራው በትዝታ ፈረስ ወደ ዲማ ጊዮርጊስ ሰሜሮ።

"መቼም ዲማን የማያውቅ የቂስ ተማሪ ያለ አይመስለኝም። ለምን ቢሉ? ዲማ-ጊዮርጊስ ማሕፀነ-ለምለም ገዳም ናት። መጻሕፍት ሁሉ ከእሳ ይወለዳሉ። በዲማ ቤተ መዛግብት የሌለ መጽሐፍ የለም። መጽሐፈ አዳርን ጨምሮ ሌሎች ብርቅዬ የጥበብ መጻሕፍት አሉ። በተለይ አቡሻክሩ ግሩም ነው። "ከመ ታእምር" የሚለው ቃል ያለበት የኖበቡ አቡሻክር ያለው ዲማ ጊዮርጊስ ብቻ ይመስለኛል። በሌላ ቦታ ያለው አቡሻክር ደግሞ የራሱን ቀመር ይዞ ይሄዳል። እንደምታውቁት የአቡሻክር መንገዱ የተለያየ ነው። የዲማው በተለይ ከመታእምር የሚለውን ቀመር ይጽፋል። ይህንን ቀመር በትክክል ለቀመረው ክልደቱ እስከሞቱ እድሉን ያውቃል..." ብሎ ሊቀጥል ሲል ምሥጢር አሳካኝ ጌዶር አብሮ መኖሩ ትዝ አለው። ወደ ተክለ እግዚእ ታሪክ ተመልሶ መተረክ ጀመረ።

"እናም ድሮ የ ከመ ታእምርን ምሥጢር ለማወቅ ሊቃውንት ወደ ዲማ ጊዮርጊስ ሂደው መጽሐፍ በማንበብ፣ ምሥጢር በማደላደል፣ ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር። የአቡሻክሩ ሊቅም ወደ ዲማ ጊዮርጊስ የመራት የጥንቱ አቡሻክር ከዚያ መኖሩን ሰምተው እንደሆነ በራሳቸው እንደበት ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አቡሻክሩ በዲማ ጊዮርጊስ ውስጥ በተጠቀለለ ብራና ተጽፎ ይገኛል። አቡሻክሩ ከግዘፈቱ እኩል ጠባዩ ረቂቅ ነው። ማንም መርምሮ በቀላሉ ሊረዳው አይችልም። ሊትነትን

PDF Compressor Free Version

ይፈታተናል። ጀግና ያውቃል። አቡሻክሩ በቀመር ሲተነትን የአንድን ሰው ዕጣ ፈንታ ከልደቱ እስከሞቱ ድረስ ጎልጉሎ ይናገራል። እድልን ቀልጭ አድርጎ ያሳያል። "ከመ ታእምር ዘንተ ከመ ታእምሮ" እያለ ጥበብ ቀመስ ቀመር ያስተምራል። ቀመሩን ላወቀ ደግሞ እድል ፈንታውን በቀላሉ ያውቃል። የሞቱን ዕለት ሳይቀር ቀመሩ ይጠቁማል። ያም ሆኖ ቅኑ አቡሻክሩ ቀላፊ-መልአክ ጭምር ይመስለኛል። አቡሻክር ተምረው ከተማ ለከተማ "አወቅሁልሽ" እያሉ ጠበር እየጣሉ የሚያጭበረብሩ ብቅ ሲሉ ፈጥኖ ይቀስፋቸዋል። በአጭሩ ትምህርቱ የመናኒ ትምህርት እንጂ የአጭበርባሪ ትምህርት አይደለም። ማጭበርበር አያስተምርም። ከሌላው መንጠቅን ያወግዛል። በእውነተኛው መንገድ ግን እውነተኛው ሀብት የሚገኝበትን ያመለክታል። ቀመሩ ጠበር እየጣሉ የሚቆጥሩት ሳይሆን በቅጽበት ተአምር ማሳየት የሚችል ነው። እኔም በጥቂቱ ፈትሸዋለሁ።" አለ ገሞራው።

ገሞራው በቀመሩ መሠረት አንድ ነገር ብቻ ተጠቅሞበታል። ይቺን ተአምር ማወቅ የቻለው ደግሞ በዐሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር። በዚህ ቀመር ከተጠቀመ ወዲህ ወደምናኔ ሕይወት አዘነበለ። ውስጠ ሰብእናው አልም ያለ መናኒና ተመራማሪ እየሆነ መጣ። የዓለም ገባዘንኬ ከአፍንጫው እጅግ ቅርብ መሆኑን ሲያይ ከዓለም ገባዘንኬ እየሸሸ ሄደ። ከሰው መነሻል ቁኖ ብሎ ጠባዩ ከሰው እየተለየ በሐሳብ እየነጎደ አስመሪረው። ዲማ ጊርጊስ ላለ የቅርብ ጓደኞቹ ሳይቀር አቡሻክሩ መፍዘዝ መደንገዝ እንደሆነው አስከመገመት ደርሰው ነበር።

PDF Compressor Free Version

"ከመ ታእምር ዘንተ" ከሚለው ቀመር በአንዱ ቀመር የፈዘዘ የመሰላቸው ጓደኞቹ ወደዚህ ውስጥ በመግባቱ ይናደዳሉ። አፍ አውጥተው እንዳይዘልፉት ዘለፋና ውዳሴ ኢምንቱ ናቸው። ለዘለፋው ቀዘቃዛ ውኃ ነው። ንዴት ብሎ ነገር አይነካካውም። ሰውዳሌም እንዲሁ አይጓንፃም ነው።

ባቢቱው ጌዶር የሚወድደውን ቅራሪ ስላገኘ ገሞራውን መስማት ክቋመ ቆይቷል። ቅራሪውን በጉንጩና በጉንጩ እያማታ ወደውስጡ ያንቆረቁረዋል።

ገሞራው ግን ቀጥሏል።

"የአቡሻክሩ ሊቅ መናኙ ተክለ-እግዚአ ወደዲማ ጊዮርጊስ በአማራ ሳይንት የተሻገሩት ይህንን "ከመ ታእምር ዘንተ ከመ ታእምር ዘንተ" እያለ ከምሥጢር ወደምሥጢር የሚመራውን መጽሐፈ-አቡሻክር ሰመመርመር ነበር። መጽሐፉን "ቀሊላን ደብተሮች" ጠጠር እየጣሉ ሲያሟርቱበት፣ ጠቢባን ሊቃውንት ግን የሰማይና የምድሩን ምሥጢር ይፈላሰቆበታል። አንዱ መናኝና ፍልሰፍ ደግሞ ተክለ እግዚአ ዘወሎ ነበሩ። ዲማ ጊዮርጊስ መጡ። በእንግድነታቸው የመጽሐፍ ተማሪዎች ተቀበልናቸው። ሰነባብተው አቡሻክር ለማንበብ እንደመጡ ለገዳሙ መምህር ገለጡ። ምሥጢር እንዳያወጡ ቃል ገብተው መጽሐፉ ከቤተ-መዛግብት ወጪ ሆኖ ተሰጣቸው። ከቤተ-መጻሕፍት በር ላይ ቁጭ ብለው ለዓመታት ያኸል በጽሙና መረመሩት። ቀመሩ በአያሌው እየተረዳቸው ሲሄድ ሰውነታቸው እያለቀ ውስጣቸው እየረቀቀ ሄደ። እንደሲባጎ ገመድ ቀጠኑ። ሥጋቸው አልቆ በአንጥታቸው ሄዱ። እኽል የሚቀምሱት

PDF Compressor Free Version

መግለጫቸው ቀመረ ዉሕረቃን ለመመርመር ይመስለኛል። መጽሐፉ የዉሕረቃን ከፊል ብርሃንና ግማሽ ጽልመት ይነግራቸዋል። መጽሐፉ የነገራቸውን ለማረጋገጥ መደጨረቃ ዐይናቸውን ይልካሉ። ከመቀመጫቸው ብድግ ቁጭ ብድግ ቁጭ ያሰኛቸዋል። ምሥጢራዊ ምርምር እንዲህ ብድግ ቁጭ፣ ብድግ ቁጭ፣ ሲያደርጋቸው ያበዱ ይመስላሉ። ዘወትር ይህንን በመሰለ ምርምር ያመሹና ዉሕረቃ በደንብ ወንግ ስትል መጽሐፉን አጥፈው ወደእቃ ቤቱ መልሰው ወደጎጇቸው ገብተው ለጸሎት ይሰለፋሉ። ደግሞ ትዝ ይለኛል። በደብሩ ጥድ ሥር ቁጭ ብዬ ወንጌል ሳጠና ቀስ ብለው ከበዓታቸቸው ወጥተው ያጨበጭቡልኛል። ቀና ስል "-ና- ወዲህ" በሚል ዐይነት እሻቸውን ያወናጭፋሉ። ጣቶቻቸው ቀጫጭን ሲሆኑ እንደፋና ያበራሉ። መዓዛቸው እንደናርዶስ ጠረን ያውዳል። የጣታቸው አዕቅ ግን ለምፅ በለምፅ ነው። ስግደት ስለሚያዘወትሩ ቡግ ብሎ ቁስሎ ቍስሉ ተመልሶ ስለደረቀ ለምፁ ብቻ ለምልክት ቀርቷል።

"ዘወትር ና ወዲህ" ሲሉኝ እየተንቀጠቀጥሁ እሄዳለሁ። ከቤታቸው በር ስደርስ ድንጋይ ላይ አረፍ እንድል ያመለክቱኛል። በጣም እፈራለሁ።" አለ ገሞራው።

"ለምን ትፈራለህ?" አለ ጌዶር በፍርሐት በኩል ጓድ ያገኘሁ መስሎት።

"ፍርሐቴ ዕለተ-ሞቴን ይነግሩኛል ከሚል የመነጨ ነበር። አቡሻክር የተማረ ሊቅ የሌላውን የእድሜ ጣራም ያውቃል። የመሞትም ሆነ ብዙ ዘመናት የመኖሩን ዕጣ ፈንታ እንደሚያውቅ ቀደም ብዬ አውቃለሁ። ገና አቡጊዳ ስቆጥር ወሬው ደርሶኛል። ከየኔታ ለበቅ ለጥቆ የማውቀው

PDF Compressor Free Version

ነገር ቢኖር አሰኑ ነው። ይህን ስለማውቅ አቡሻክር የተማረ ሊት ሲፈ
እኖር ነበር። በእርግጥ እንደመሲሴ ያስፍራኝ ሞቱ ብቻ አይደለም። ከሞን
ቀድሞ የጎሊና ሞት አለ። ጎሊናው የሞተ ሰው ባይሞትም በድን ነው።
እኔን ያሰፈራኝ ቀዳሚው የሕሊና ሞት ነበር። በል! አትልፋ? በቅርብ ቀን
መልአከ-ሞት ይጎበኝኻል" ቢሉኝ ተስፋ አቀርጣለሁ። ከቅኔና ከመጽሐፍ
ትምህርቱ እናጠባለሁ ከሚል የሕጻንነት አእምሮ የመነጨ ነበር
ፍርሐቴ።

እግዚአብሔር ይመስገን! አለ ገሞራው ዐይኖቹን ወደሰማይ ወንጭፎ።
እግዚአብሔር ይመስገን ያንን ሳይሉኝ ተሰያየኑ። የራሳቸውን የሞት
ዜናም ሆነ ያለፈውን እጣ ፈንታቸውን ሲያረዱኝ የእኔን እጣ ፈንታ
ደበቁኝ።" ገሞራው ትንሽ ትክዝ አለ።

"እንዴት የራሳቸውን ዕጣ ፈንታ ነገሩኝ ማለት? ምን ማለት ነው?" አለ
ታሪኩ ቅራረዋን ምንም ሳይቀምስ በተመስጦ ሲሰማ ቆይቶ።

"ነገሩ ወዲህ ነው" ሲል ቀጠለ ገሞራው።

"ነገሩ ወዲህ ነው። አንድ ቀን መጽሐፍ ስመለከት እንደልማዳቸው
ጠሩኝ። ሄድሁ። ከዚህ ዓለም የምለይበት ጊዜዬ ደርሷል። ቀኑ ደግሞ
ወር በገባ በሃያ ዘጠኝ ቀን ነው። በቀትር ሰዓት የቅዳሴ ደወል ሲደወል
እሞታለሁ" የሚል ጽሑፍ በብጣቂ ወረቀት አቀብለውኝ ዘልለው
ቤታቸው ገቡ። አንብቤ ስጨርስ ሰቅሰቅ ብዬ አለቀስሁ። ያስለቀሰኝ
ሞታቸው ብቻ አይደለም።

PDF Compressor Free Version

ሊቶ ሊምቱ ለኮሳሙሩ አማር መቃብር መሙረዱ ጭምር ውልል ብሉ-
ታይቶኝ ነው።" ብሎ ዐይኖቹን ግልጥልጥ አርጎ ወደ ንደኞቹ
ወረወራቸው።

ታሪኩ በተመሥጦ ሲሰማ ቆይቶ ዐይቹን ወደ ቅራሪው ወረወረ።
ሄር አጁን ሰድዶ በሞርማ ከቀረበለት ቅራሪ በጎይል ተጎነጨ።
ገሞራውም በደም የተሠረቡ ዐይኖቹን ገርበብ አድርጎ ዝም ሲል ሲቁ
ሳይገርም ሊቅ ናቸው። የሊቃውንቱ ጎበብ በቀላሉ ተንግሮ አያልቅም።
አሁን ይህን ማን-ወንዱ ነው አሜን ብሎ የሚቀበለው" አሰ ታሪኩ።
"እውነት ነው ታሪኩ ሲሰሙት ተአምር ይመስላል። ያፈላል፣
ያደነግላል። ነገር ግን መፍዘዝ መደንግዘ ለደይደለም። ተአምርም
አይደለም። በዐይኖቹ ያየሁት የአባቱ ታሪክ ነው።" ኅሰ ገምራው።
ፍጻሜው ምን ላይ ደረሰ?" አለ ገራገሩ ቶማስ አእንቅልፉ ባንኖ።
ዐይኖቹ በእንቅልፍ አብጠው የበለለ የሾላ ፍሬ መስለዋል።
ገሞራው ቀሪውን ታሪክ ለመግለጽ ከኤርታሌ ጉድጓድ እንደሚፈናጠር
እሳት የሚንቀለቀሉ ዐይኖቹን ሰመመን ውስጥ ከተታቸው። ዐይኖቹን
ሰመመን ውስጥ ጥሎ ተአምር የሚመስሉ ነገሮችን ማብራራት የዘውትር
ልማዱ ነው። የሰውን ስሜት የሚነኩ ነገሮችን ሲያብራራ ዐይኖቹን
ያስለመልማቸዋል። በሽፋሽፍት ይደብቃቸዋል። ሰመመን ውስጥ
ይጥላቸዋል። ቅኔ ሲዘርፍ ደግሞ የበለጠ ሰመመን ውስጥ ይወድቃል።
ሁለመናው ሰመመን ውስጥ ሆኖ ቅኔውን ሲያንጎደጉደው የቀለም ዘር
ጠብ አትለውም። ያንን ገመድ የሚያክል መወድስ ወደፊት ይስበዋል።
ወደ ኋላ ይጎትተዋል። ወደ ሰመመን ዓለም ሲገባ ታዳሚውን ሰመመን

PDF Compressor Free Version

ውስጥ ይጥላል። እሱ ታሞ ሌላውን ያሳምማል። በቅኔ ኑበደ ሌላውን ያሳብዳል።

"ዕረፍቱ ደርሷል" ሲሉ ሸፈው የሰጡኝን ወረቀት ወደ መጽሐፌ መልሼ ወደ ቁልቋሉ ጫካ ገባሁ። የቁልቋሉን እሾህ እየረገጥሁ ወደ ውስጥ ዘልቄ አንድ ሙሉ ቀን በግንባሬ ተደፍቼ ስነፈርቅ ዋልሁ። በዚች ቅጽበት ያረፉ መስሉኝ ነበር። ወደማታ ቤታቸው ሄጀ አጨበጨብኩ። ብሩህ ገጻቸውን አስቀድመው ብቅ ሲሉ ማመን ተሳነኝ። ረጅም ናዝራዊ ጸጉራቸውን ሽቅብ እየቀለበሱ ሲመጡ ከመታብር የወጡ መስሉኝ አንደ መግደላዊቷ ማርያም ከጉልበታቸው ወደቅሁ። ለትሕትና ያንስ ወደ ኋላ ተስፈነጠሩ። ከእግራቸው ጫማ ላይ ሊያርፉ የነበሩ ስናፍሮቼ ፀፈር ነፈሱ። ድንጋይ ነከሱ። በእጃቸው ደረቱን ደግፈው ሲያስነሱኝ አንዳች ነገር ተሰማኝ። እጃቸው መቁሰል። በመቀቱ ውስጥ መልካም መዓዛ አወደኝ። ከመሬት ሲያነሱኝ እንደመርዶ የከበደኝ ትካዜ ከሳቤ ተገፈፈ። ከዚያኑ ቅጽበት ጀምሮ ማልቀስ አቆምሁ። እንዲያውም ከዚህ መጣ ያሳልሁት ፍሥሓ ወረረኝ። ወደ ቤታቸው መግስንሱን ግን ወደ ወዲያኛው ዓለም እስኪሄዱ አላቆምሁም ነበር። ወር በገባ በሃያ ዘጠኝ ቀን ቤታቸውን አንኳኳለሁ። የተቀደደ ቀሚስ፣ ያለቀ አቡጀዲ፣ ደርበው ብቅ ይላሉ። የምለው ነገር ይጠፋብኛል። እጅ ነሥቼ በውስጤ አለመሞታቸውን አረጋግጬ እመለሳለሁ። ደግሞ ወደ ማታ በደኅና መዋላቸውን ለማረጋገጥ እሄዳለሁ። እንደማለዳው አጨበጭባለሁ። የተቀደደ ቀሚስና ያለቀ አቡጀዲ ደግልለው ይወጣሉ። ገጻቸውን አጥብቄ አመለከታቸዋለሁ።

PDF Compressor Free Version

አሳቸውን ይነግሩ ዘንድ መቅኑን ይሰጡኛል። ያንን ለመቅመስ አረፍ እላለሁ። የሞቱ መስሎኝ አፈን ደም ደም ይለዋል። ጸጉሩ የሚባለው የገዳሙ ምግብ እንደ አዝን ጥሬ ይተናነቀኛል። ሁኔታዬ ገብቷቸው ማየ-ኑግ የሚባል የኑግ ጭልቃ በዋርማ ይዘው ድጋሜ ብቅ ይላሉ። የምግቡ ማወራረጃ መሆኑ ነው። እጅ ነሥቼ አቀበላቸዋለሁ። በዚህ መልኩ ወር በገባ በሃያ ዘጠኝ ቀን ስመላለስ አራት ዓመት አለፈኝ። እየቆየሁ ስሄድ ግን የዋሹኝ መሰለኝ። መመላለሴን ግን አላቆምሁም። እሳቸውም አልከለከሉኝም። መጨረሻቸው ሲደርስ ትንቢታቸው ሲፈጸም በዐይኔ ዐይቼ ሟ ብዬ አሰቀስሁ።" አለ ገሞራው ያንን ያለፈውን ትካዜ በምናቡ እያመጣ።

ታሪኩና ቶማስ ሕልም የሚያወራ ቢመስላቸውም ገሞራው የሚሳሳለት ሕይወቱን ለእንዲህ ዐይነት ነገር አሳልፎ እንደሚሰጥ ስለማያውቁ ልባቸውን ከፍተው መስማማታቸውን ቀጠሉ።

ገሞራውም ቀጠለ።

"ዐያችሁ ወንድሞቼ! ለካ የአቡሻክሩ ሊቅ ትንቢት ሐሰት አልነበረም። ምትሐት አልተቀላቀለበትም። አነጋገራቸው የነቢያት ትንቢት ብቻ አልነበረም። በአቡሻክር ቀመር ተሰልቶ የተገኘ ጥበብ ጭምር እንጂ። ያሉት አልቀረም። ዕረፍታቸው ሲደርስ ወርኑ የግንቦት ወር፣ ዕሉቱ ሐሙስ ነበር። በዚች ቀን ማለዳ እንደልማዴ ሂጀ አጨበጨብኩላቸው። መልስ ግን አልነበረም። ዘው ብዬ ወደ ቤታቸው ገባሁ። ቤታቸው ዝንተ-ዓለም ሲኖሩ አይዘጋም ነበር። ክፍት ውሎ ክፍት ያድራል እንጂ። ወደ በዓታቸው ስገባ ራስ ፍልጠት ስትጠዘጥዛቸው ደረስሁ።

PDF Compressor Free Version

ጥንቸል ምቱት ነበረችባቸው። ራሳቸው "ሐዳጊት" እያሉ በቅጽል ሙ
ይጠሯታል። ምክንያተ-ሞት ትሆናለች ብዬ ግን ጠርጥሬ አላውቅም
ነበር። ነገር ግን መታበር አመረደቻቸው። ራስ ፍልጠት ሲጠዘጥቸው
ራሳቸውን በሻሽ ደግልሰው ጋደም እንዳሉ እንቅልፍ አሸለባቸው። የሞት
መስሎኝ ተሉ ቶሎ አዳበሳቸው ጀመር። ሙቀት አልተሰያቸውም።
አፍንጫቸው የሕይወት እስትንፋስ ይተነፍላል። ሰዓቱ ወደ አምስት
ሰዓት ሲጠጋ ሞታቸው እየተረጋገጠ መምጣት ጀመረ። በደናቸውን
ገለጥለጥ አርገው "የቀትር ደወል ተደወለ?" ሲሉ ጠየቁኝ። ከዐራት
ዓመት በፊት "በቀትር ጊዜ የቅዳሴ ደወል ሲደወል አርፋለሁ" ብለው
በጣቂቂ ወረቀት ጽፈው የሰጡኝ ታወሰኝ። ሰቅሰቅ ብዬ አለቀስሁ።
"በቀትር የቅዳሴ ደወል ተደወለ ማለት ምን ማለት ነው?" አለ ቸሩ
ቶማስ።

"የቀትር ደወል ማለት ከቀኑ ስድስት ሰዓት ግድም በቀትር ለቅዳሴ
የሚመታ መረዋ በለው። በገዳም ሥርዓት መሠረት ስድስት ሰዓት
ሲመላ የቀትር ደወል ይደወላል። ካህናት ለቅዳሴ ይሰበሰባሉ። የዛሬው
ደወል ግን ባይደወል ወደድሁ። ደወሉ በቀር መልአከ ሞትም የማቀር
መሰሉ ተሰማኝ። ያ ግን አልሆነም። ቀትሩ ነባልባሉን አስቀድሞ ብቅ
አለ። ደወሉ ተደወለ። የአቡሻክሩ ሊቅ የቀትር ደወል ሲደወል ነፍሱ
ታርጋለች ሲሉ ዳግም ትንቢት ተናገሩ። ስድስት ሰዓት ደርሶ በቀትርጊዜ
የቅዳሴ ደወል ሲደወል ነፍስና ሥጋቸው ተለያዩ።" ገሞራው ትክዝ
አንገቱን ደፋ።

PDF Compressor Free Version

ገሞራው በሞቂቱ ቢዕን ከሰደዩ ተመራማሪ ሊቅ አቡሻክሩን ቀጽሏል። መርሐ እውሩን አሂዷል። ሌላም ሌላም ምሥጢር ተሰሚል።

"ቆይማ! ዓይ?አንድ ጥያቄ አለኝ?" አለ ታሪኩ በተደሞ ሲሰማ ቆይቶ። ምን ነበር?" አለ ገሞራው ወደ ታሪኩ ሁለቱን ጀሮዎቹን ዘንበል ዘንበል አድርጎ።

"እንደኛው ጥያቄ አቡሻክርን ያኽል ውቅያኖስ የሆነ ትምህርት ተምረው እንደማስተማር ለምን መነሱ? ዓለም በቃኝ ለምን ገቡ? በሰማይ ቤት መክሊቱን የቀበረ ባሪያ ተብለው አይጠየቁምን?" አለ ታሪኩ።

"ጥያቄው ሸጋ ነው" አለ ገሞራው

"ቅድመ ምናኔ የአቡሻክር ጉባኤ ዘርግተው አንዳንድ አእምሯቸው ክት ጭንቅላታቸው ክፍት የሆኑ ደቀመዛሙርትን ብቻ መራርጠው ያስተምሩ ነበር። ሲያስተምሩ "የዘመነ ሰው ፈተና ሆነባቸው። በዓታቸው ድረስ እየሄደ የጸሎት ጊዜ አሳጣቸው። መጣኒው ዘፋኝ፣ሙዚቃዬ የአድማጭ ጆሮ አጣ። አድማጭ እንዲያገኝ ምን ሳድርግ ማለት ጀመረ። ሯጩ፣ እግሬ እየሰነፈ አስቸገረኝ። እንደ አሣሒል ቀሲል ሰኮና ይትከሉልኝ ማለት አመጣ። የቆሎ ተማሪውም አልቀረ። ተምሬ ሰጪርስ አቡን መሆንአፈልጋለሁ በዚህ በኩል ይርዱኝ እያለ ጨቀጨቃቸው። ወደ መጨረሻው ግድም ደግሞ ባለ-ሥልጣናት ጭምር የሥልጣናቸው ልዕልና ሰማየ-ሰማያት እንዲሰቀልላቸው በማዕረግ ላይ ማዕረግ እንዲጨመርላቸው ሊቁ መላ እንዲፈጥሩላቸው ዕረፍት ነሳቸው። ስግብግቡ ባለሀብት ደግሞ በሀብት ላይ ሀብት በፎቅ ላይ ፎቅ

PDF Compressor Free Version

መቀጣጠል የምችለው በየትኛው የሥራ ዘርፍ ብሰለጥ፡ ነውን እደሰ ይጨቀጭቃቸው ያዘ።

የአቡሻክሩ ሊቅ ግን እኔ መምህር አንጻ ጠንቋይ አደደለሁም። የእስሌ ሀብቱ ንንድ፣ የእስሌ አጣ ፈንታ ንብርና ነው እያልሁ ጠጠር የምጥል ሚርቶኛ አደደለሁም ብለው እንቅፀን ተናገሩ። የአቡሻክሩን ምሥጢር ሰጠሩ። የቀመሩን ምሥጢር ጠበቁ። የእኛው ሰው ለወሬ ምን ይማነዋል? የቅጠል ቀዳዳ ያክል መግቢያ ካገኘ የሣመል ሳዓስፈያ እስኪሆን ያሰፋዋል። የሰማው ሳልሰማው እያወራ የአቡሻክሩ መምህር ጉባኤ የሰንብንበት መጠራቀሚያ ሆነ። ደላሎችም በስማቸው መነገድ ጀመሩ። ክብብ የሚቆጥሩ የአቡሻክር ሊቅ ተፈጠሩ ተብሎ ከሀገር ሀገር ተወራባቸው። ደላሎች ከተማ ቁጭ ብለው ሕዝብ እየሰበሰቡ መኪና እየተክራዩ ወደ ሊቁ እየላኩ ከሀብት ቁንጮ ላይ ወጥተው ፈጥ አሉ። በሕገዙ ዘንድ የሊቁ ማዕረግ ከሊቅነት ወደ ጠንቋይነት ዝቅ ሊል ምንም አልቀረውም። የአቡሻክሩ ሊቅ ይህንን መከራ ሰዓመታት ታግሰው ተጋደሉ። ተጋድሎው ከገመቱት በላይ ከባድ ፈተናሲሆን ስማቸውን ለውጠው፣ አስኪማ መላእክት ተቀዳጅተው፣ እንደ ጌታችን የእሾህ ጉንጉን በራሳቸው ችንክረው ቀራንዮ ላይ ተሰቀሉ። ዓለም ለምኔ ብለው ጉባኤያቸውን ፈትተው ሀገራቸውን ትተው መነኑ። መንነውም ብቻ አላበቁም። እስከወዲያው ቃል ላይጠሣቸው አርምሞ ያዙ።" አለ ገሞራው።

"እግዚኦ! አርምሞው እንዲት አስቻላቸው አየ? ቀለሙ ፈንቅሏቸው ላይወጣ መቅረቱ አርምሞ ሊይዙ።" ታሪክ ተደመመ።

PDF Compressor Free Version

"ምን ያድርጉ ብለህ ነው!? ጥበብ እየነገሩት ጥንቆላ ከሚፈልግ ትውልድ ለመራቅ መፍትሄው አርያምም ብቻ ነው። የዘመኑ ሰው እንደሰይጣን በሄዱበት ገዳም በመነኑበት ሜካ እየገባ ሲያሚርትባቸው እስከ ዕለተ ሞታቸው ቃል ላይተነፍሱ አርምሞ ያዙ። በዚህ ዘመን የአቡሻክር ሊቃውንት እየጠፉ የሄዱበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። አባቶቻችን የአቡሻክር ጉባኤ ዘርግተው አቡሻክር መንገር ሲጀምሩ እንደጠንቋይ ይቆጠራሉ። ወይም ተማሪዎቻቸው አቡሻክሩን በደንብ ተምረው ለመንፈሳዊ ነገር ማዋል ሲገባቸው የ"ከመ ታእምር"ን ቀመር ተጠቅመው ከመንፈሳዊ ወደ ዓለማዊ ነገር ይሰባሉ። ንዋይ ሲማርካቸው ወደጥንቁልና ይዘምታሉ። የአቡሻክር ሊቃውንት ይህን ሚርት አጥብቀው ስለሚጠሉ ከማስተማር ታቅበው፣ ገዳም ገብተው፣ ራሳቸውን ይደብቃሉ። ለራሳቸው ኖረው ለራሳቸው ብቻ ያልፋሉ። የነገውን ባናውቅም ዛሬ ላይ የአቡሻክር ትምህርት በኢትዮጵያ እየተመናመነ የመጣው ሊቃውንቱ ራሳቸውን በመደበቃቸው ነው። ተምረው እንዳልተማሩ አርምሞ ይዘው አፋቸው ሳይናገር ምላሳቸው እንደ ተቋጠረ ምሥጢር ሳይተርፉን ወደ መቃብር ይወርዳሉ። ፍልስፍናቸው ከሥጋቸው ጋር ይቀበራል። ጥበባቸውን መጫ ይውጠዋል። የሆነው ሆኖ የዛሬው የነፍስ ይማር ለእሳቸው ነው። "ክሉ ነፍስ ይማር በሉ!" አለ። "ነፍስ ይማር! ነፍስ ይማር!" ብለው ዝም አሉ። ንሮራው በድቅድቁ ጨለማ ፊሪው ጌዶርን ቤቱ ድረስ ሸኝቶ ተመልሶ የቅራሪዋን ቅምጫና ወደ ውጪ አውጥቶ ወደ ቆጥ አልጋው ወጣ። ታሪኩና ቶማስ ባሉበት እንቅልፍ ጣላቸው። ሌሊቱ የጨለማ በርኖስ ደርቦ ነበር።

PDF Compressor Free Version

ሽፍን

ኮቅኔ ገዘ። ሊቁ ዘወትር ከሰኞ እስከ ዐርብ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ተነሥተው ጸሎት ያደርሳሉ። የዘወትሩን ጸሎት እንደ ጨረሱ ጥቂት ሽልብ ይላሉ። ከጸሎት በኋላ ሽልብ ሲሉ አልፎ አልፎ ራእይ ያያሉ። ይህ ከጸሎት በኋላ የሚመጣው ራእይ ቅዠት መሰል የሐሞታት ሕልም አይደለም። በጸሎት የተገለጠ አማናዊ ሕልም ነው። ቅኔ ሲዘርፉ ሲፈልጉ ግን ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ይነሣሉ። በቀር ሌሊቱ መነጋጋት ሲጀምር ጸሎታቸውን በአቡነ ዘበሰማያት ዐሥረው ቀጥታ ወደ ቅኔቤት ገብተው የዕለቱን ታሪክ ይተርጎሙ። ሲተርኩ ድምፃቸው ዜማ ባለው ቅላጼ ይስረገረጋል። በዕለቱ የሚውሰውን ታሪክ አስቀድመው "በዛሬው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በድንግል ማርያም ማሕፀን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት የተወለደበት ዕለት ነው..::" ብለው ጀምረው ሪዙሙን ታሪክ እንደ አቡነ ዘበሰማያት ሰተት አድርገው ተርከው ሲጨርሱ "በሉ ፀሐይ ሳይቀትር አእምሯችሁ በፀሐይ ሙቀት ሳይበተን ወደቅኔ ሙጠራ ሂዱ" ብለው አዳዲስ የቅኔ ጀማሪዎችን ወደ ጸሩ ያስዚያም ጽሞና ቦታ ፊልገው ቅኔ እንዲቆጥሩ ያሳስባሉ።

ተማሪዎችም ትእዛዛቸውን አክብረው ቃለ-ሕይወት ያሰማልን ብለው ወደየጫካው ለቅኔ ቆጠራ ይበተናሉ። የተማሪዎች የቅኔ ቁጠራ ስልቱ ልዩ ልዩ ነው። ብሉ ተማሪ ከጓደኛው ጋር ቁጭ ብሎ እያወራ በልቡ ቅኔ ይቁጥራል። ልበ-ቢሱ ተማሪ ምንም ድምፅ ከማይሰማበት ቦታ ተደብቆ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣

PDF Compressor Free Version

"ጎዷ ንዓ ወላዲተ አምላክ መርዓት" እያሰ ቅኔ ካልቆጠረ ብልጭ አይልለትም። ሰንፋ ተማሪ ደግሞ በሳኒ ተኝቶ ካልሆነ በቀር ሕሊናው ለቅኔ አይሰበሰብም። ሊቁ ፋሪስ ግን ተኝቶ ቅኔ መቁጠር የሰንፍና ምልክት ስለሆነ ሲወጡ ሲወርዱ ወዲያ ወዲህ ሲሉ እየቆጠሩ አእምሯቸውን በእውቀት እንዲያበለጽግ ለተማሪዎቻቸው ሳይመክሩ ሳይዘክሩ ውለው አድረው አያውቁም።

በዛሬው ዐርብ ታሪኩ ስሜት ውስጥ ከገባ ቆይቷል። የቅኔ ዘረፋው ወኔ ተቀሰቅሰበት መሬቱን በእግሩ ሲጭር ይታያል። ታሪኩ ቅኔ ለመንገር ሲቆም መሬቱን በእግሩ አውራ ጣት የመሳር ልምድ አለው። ይህንን የሚያደርገው አስቦ አይደለም። በልቡናው ምሥጢር ሲጭር በእግሩ አውራ ጣት ደግሞ መሬት ይጭራል። የሌላውን ሊቅ የቅኔ ምሥጢር በመንጠቅም የታወቀው። ጎንደር አካባቢ ተወልዶ በጎንደር አድባራት እየዞረ ተምሯል። ጎንደር ቅኔ ተመርቶ ጎጃም ደግሞ ልዩ የቅኔ መንገድ ለመቀጸል ነበር የመጣው። ጎጃም ተመርቶ ጎንደር፣ ጎንደር ተመርቶ ጎጃም፤ ትግራይ ተመርቶ፣ ዋድላ ደላንታ፣ ዋድላ ተምሮ ትግራይ፣ ሸዋ ተምሮ ቦሩ ሜዳ፣ ቦሩ ሜዳ ተምሮ አዲስ ዓለም እየተዘዋወሩ የተለያዩ የቅኔ መንገዶችን መቅሰም የተለመደ የቅኔ ሊቃውንት ባሕል ነው። ታሪኩም ጎንደር ተምሮ ጎጃም ከተሻገረ ገና አንድ ዓመት ቢሆነውም ለቅኔው ዘረፋ ግን አዲስ አይደለም። ደረጃውም ሰባት ዓመት በጎንዮ ቅኔ ቤት ከቆዩ ቅኔ ዘራፊዎች እኩል ሆኗል።

"እስኪ በል ልጄ?" አሉ ሊቁ ፋሪስ ታሪኩን እየታኙ።

ታሪኩ በእግሩ አውራ ጣት አፈሩን እየገፋ ቀጠለ።

PDF Compressor Free Version

"ሀገረ ሊቃውንት ቀደምት መሠረተ-ዜማ ጎንደር።
ጽሑፍ ስምኪ በዘማየ ሕይወት ምሥጢር።" አለ ጎንደር ከሚለው ሰንጎ
ላይ 'ር 'ን ከረር አድርጎ።

ሊቁ ፋሬስ መቋንጥጥ ጀመሩ። ያቋነጠነጣቸው የሕይወት ውኃ
ምሥጢር ነበር። ገና ታሪኩ "በሕይወት ውኃ ምሥጢር" የሚል ቃል
ከአንደበቱ ሲያወጣ ሊቁ ውስጣቸው ተንካ። እናም ተቋነጠጡ። የጎንደር
ውኃ ሰትነሣ የቀለም መምህራቸው ድንቁ ትዝ አሏቸው። ዛሬ ላይ
ጊዜው ቢርቅም ድንቁ ጎንደር ተሻግረው ሃያ ዓመት ተምረው
ተመልሰዋል። ጎንደር ሳሉም ይቺን የሕይወት ውኃ ለብዙ ዘመናት
ሲያሥሙ ነበር። እንደ ጀምስ ብሩስ ብዙ ደክመዋል። ወዲህም ጎንደር
በእውቀት የተወለዱባት ሀገር ናት። ዳግም ልደታቸው ጎንደር ውስጥ
ነው። በሥጋ ጎጃም ይወለዱ እንጂ በእውቀት የተወለዱት ከጎንደር እና
ከጎጃም ወፈር ነው።

"ምን ማለት ነው ቅኔው?" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

ታሪኩ ቅኔውን ማብራራት ቀጠለ።

"..የዐራራይ የዜማ የሊቃውንት ሀገር፤
የምሥጢር እመቤት ሰላም ለኪ ጎንደር
ስምሽ የተጻፈው በሕይወት ውኃ ሥር.."

ብሎ ጎንጅ ደብረ-ጥበብ ሰማይ ሥር የተቀበረውን ዐይኑን አንሥቶ
ወደጎንደር ወረወረው።

"ይበል! ነው ኧረ ይበል!" አሰይ ልጂ!" አሉ ሊቁ። እንዲለሌ የተረገረገው
ወፈ ሰማያት ተማሪ ለታሪኩ አጨበጨቡ።

PDF Compressor Free Version

ከዚያም
"እስኪ በደንብ አብራራው። የቅኔ ተዋቅሮው ሲላም ጭብጥ ያለው ይመስለኛል። ወዲህም የቅኔው ሰምና ወርቅ ውስጤን አልነካውም። እስኪ በደንብ አብራራው።" አሉ ሲቄ ፋራስ።

ምሥጢሩ አልነካኝም ማለታቸው ክልባቸው እንዳልነበር ውስጣቸው አያነገራቸው። ሲቄ እንዲህ ናቸው። ዐቢይ ምሥጢር ማስወጣት ሲፈልጉ ምሥጢሩ ውስጤን አልነካኝም ይላሉ። ያን ጊዜ አያ ተማሪ የኔታን ያስረዳሁ እየመሰለው የውስጡን ይዘክዝክል። የምሥጢር ስልቻውን ይፈታል።

"ደግሞ ጎንደር ጎንደርን አትመልከት። መቼም የተወለዱበት ሀገር ደጉ ቀርቶ ክፋው ይናፍቃል። ከዕትብታችን ጋር የተቀበረ አንዳች ምሥጢር ላይኖረው አይቀርም። ዕትብታችንን መሬት ውስጥ ሲቀብሩ የበታውን ፍቅር ደግሞ በልባችን ውስጥ ይቀብሩታል መሰለኝ። ትዝታው ከሞት በኋላም የሚለቅ አይመስለኝም። እኔም ጉብል ሳለሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅኔ-ቤት የሄድሁት ጎንደር ነበር። ጎንደር ሁኜ እንዲህ እንዳንኑ ማዶ ማዶውን እያየሁ ጎጃም ናፈቀኝና ሰቅሰቅ ብዬ አለቀስሁ። ጓደኞቼ ሂደው ለመምህሬ ነገሯቸው። ለበቅ ቆርጠው ልቤ እስኪጠፋ ገረፉኝ። በሳንባ ጠለፋ ጅራፍ ሳንባዬ ከጉረሮዬ እስኪላጠቅ ጠበጠቡኝ። ያን ጊዜ የጎጃም ናፍቆት በአፈል ቀነሰልኝ። እኔ ግን እንደ መምህሬ ለበቅ ቆርጬ ተማሪ ዝርፌ አላውቅም። አግባብም አይደለም። ተማሪ ሲያጠፋ አንድ መጽሐፍ ጠቅሼ ያንን አንብቦ መጥቶ ለጓደኞቹ እንዲያብራራ የሚል ቅጣት

PDF Compressor Free Version

አስቀድማለሁ። ወዲህም የቻልኩትን ያክል አመክራለሁ። የማስቀድመው ምክር ነው።" አሉ ሊቁ።

ታሪኩ ጀሮ ሰጣቸው።

ሊቁ በአጭሩ ምክራቸውን ቀጠሉ።

"አንተ እሳት ነህ። ነበልባል ነህ.. የእሳት ዘመን ደግሞ የትምህርት ጊዜ ነው። የእውቀትና የክሕሎት ወቅት ነው.. ወጣትነቱን በራሱ ጊዜ ያባከነ ሰው ራሱን በገመድ ሰቅሎ እንዳጠፋ ይቆጠራል። በወጣትነት ዘመን ዝንባሌን መከተል መልካም ነገር ነው። እግዚአብሔር በአርዐያ የቀረጸው ፍጡር ለራሱ ብቻ የተሰጠው ዝንባሌ አለው። ያንን ዝንባሌ በትምህርት በፈጠራ ማዳበር የባለቤቱን ትግሐት ይጠይቃል። ነገር ግን ያንን ወርቃማ ዘመን እንደ ዘበት ማሳለፍ መጨረሻውም ፀፀት ነው።

ለሰው ዘር በሙሉ ዐራት የእድሜ ክፍሎች አሉት። እነሀም ዘመነ-ነፋስ፣ዘመነ እሳት፣ዘመነ መሬትና ዘመነ ማይ ናቸው።

ከዐራቱ አንዱ ዘመነ እሳት የወጣነት ዘመን ነው። አቡሻክራችን ቆጥሮ ሰፍሮ ቀምሮ እንዳኖረው በእሳት ዘመን የሰውን ልጅ ፍትወት አጥብቆ ይቃወመዋል። ያን የእሳነት ጠባይ ድል አድርጎ የእሳትነት ዘመኑን በሚገባ የተጠቀመ ሰው ዘላለም ንጉሥ ነው፤ ዛሬ ላይ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ሆነው የቆሙ ሊቃውንት በወጣትነት ዘመናቸው በአብነት ትምህርት ቤት የተራቡና የተጠሙ ናቸው።" ብለው ጥቂት ፋታ ወሰደው ቀጠሉ።

"በእርግጥ ውቢቱ ጎንደር ትናፍቃለች። ከውጪ ሲወጡ ቀርቶ ከውስጧ ሳሉም ዘወትር አዲስ ናት። እንዲያውም አንዳንድ መጻሕፍት 'ገነት

PDF Compressor Free Version

ምድራዊት የዓለም እናቷ ናት ሲሉ ይጽፋሉ። እኔ ደግሞ ጎንት ማለት ጎንደር ናት ብዬ አመስጥሬ አተረጓመዋለሁ። ከታሪክ ምሁራን ጋር እከራከራለሁ። ለምን መሰለህ? ጎንት ማዕከለ-ምድር ናት። ጎንት መልካም መዓዛ አላት። ጎንት ፍሬዋ የበረከት ፍሬ ነው። ከርሠ-ምድሯ በሕይወት ውኃ የተሞላ ነው። ጎንደርም እንዲህ ዐይነት መልክዐ-ምድር ናት። ሊጀመር ጎንት በሰባት ተራሮች ተከልላለች። ጎንደርም ሰባት ተራሮች የተጋረዱላት ውብ ሀገር ናት። ደግሞ ዓመት ዓመት ቀለም ይፈሰባታል። ወዲህም ጎንደር ለኢትዮጵያ ማዕከል እንደ ሆነች ይታመናል። ማዕከላዊነቷ ግን የመልክዐ-ምድር አቀማመጥ አይደለም። የአእምሮ ነው። የእውቀት ነው። ከዐጤ ፋሲል እስከ ዐጤ ቴምድሮስ ሊቃውንቱ ቤተመንግሥቱን የሙጥኝ ብለው ጎንደርን በእውቀት አበልጽገዋታል። አያሌ ድርሳናት የተደረሱት ጎንደር ውስጥ ነው። ከርሠ ምድሯስ ቢሆን? እ..? እ...?" የሕይወት ውኃ ምሥጢር ከዚያ ሁላ ወፈ ሰማይ ተማሪ መኳል ሊያመልጣቸው ሲል ዝም አሉ።

"ቦል ወደ ቅኔው ተመለስ!" አሉ ሊቁ።

ታሪኩም ትንታኔውን ከሊቁ አፍ ነጥቆ በቅኔው ጭብጥ መራቀቁን ቀጠለ። አሁን እንዳሉት ጎንደር በተለያዩ ጎብረ ምሥጢር የተዘጎረጎረች ከተማ ናት። ከዐጤ ፋሲለደስ ማጎተም ስንነሣ የዐጤው የግል ማጎተም ብቻ የብዙ ምሥጢራት ባለቤት ነው። ከማጎተሙ ላይ በጉልህ የተቀረፁት ፊደላት፤

"ዝ ማጎተም ዘዐጤ ፋሲል ሃሌ ሉያ።

PDF Compressor Free Version

ኮከብ "ማኅተሙ ኮከብ ብሩህ ዘኢትዮጵያ" የሚል ፊደል ተቀርፆበታል። ይህ ማኅተም በአንድ ጥንታዊ ገዳም ውስጥ አለ። ማኅተሙ ማታ ማታ ብርሃን ይፈነዋቃል። ጀምበር ብቅ ስትል ይደበዝዛል። ገዳማውያኑ ከትርስነት ጎን ለጎን ማኅተሙ አንዳች ምሥጢር እንዳለው ሲያውቁ ከጠላት ለማራቅ መሬት ውስጥ ቀብረውት ይኖራል። ይህንን ማኅተም ከሁሉም ልዩና ምሥጢራዊ የሚያደርገው ግን ከውኃ ውስጥ ሲጥሉት ውኃ ያደርቃል። ከየብስ ላይ ሲያስቀምጡት ምንጭ ያፈልቃል። ይህ ውድ ነገር የተገኘው ከእኛዋ ጎንደር እንጂ የጥበብ አማልክት ልዩ ተፈጥሮን እንደሰጧት በሚነገርላት በግሪክ አይደለም። "የምሥጢር እመቤት ስል በቅኔ የገለጥሁት የዚህን ጉደኛ ማኅተም ባለቤት ጎንደርን ነው።" አለ ታሪኩ።

"እሺ" አሉ ሊቁ።

"ወዲህም "ማኅተሙ ኮከብ ብሩህ ዘኢትዮጵያ" ማለቱ ለጊዜው የአጥቢያው ኮከብ ፋሲል ሲሆን፣ ወደ ፊት ደግሞ አንግዳ ምሥጢር መኖሩን ይጠቁመናል። የማኅተሙ ይቆይና ዛሬ ላይ ዓለም የሚያውቀውን ብቻ ላውራ።" ብሎ ቀጠለ።

"ዐጤ ፋሲል ባይኖር የዛሬዋን ጎንደር ማን ዞር ብሎ ያያት ነበር? የፋሲል ቤተ መንግሥት ባይኖር ታሪክ ከወደዬት ያርፍ ነበር? ጎንደርኮ! እንደሌሎች መልክዐ-ምድር ብቻ አይደለችም። ምሥጢራት የተጠመሩባት የታሪክ ሰሌዳ ጭምር ናት። ከአይታ የተሰወረ እብነ-በረድ ያለባት ምድራዊት ብራና ጭምር ናት። እንዲያውም ሊቅ ዐፅቋን ጨምሮ ብዙ ሊቃውንት ጎንደርን ጥቅል ብራና አድርገው ይስሏታል። ይኸውና ብራና

PDF Compressor Free Version

የሙ ነገር ሰንድ ነው። ብዙ ነገሮች መሬት ወርደው ከመስፈራቸው ቀድመው በብራና ላይ ይቀመጣሉ። ብራና ላይ ተፈትሸው መሬት ላይ ዝራዊ ይሆናሉ። ብራና ላይ ካላማሩ መሬት ላይም አይሠምሩም። ማናቸውም ጥበብ ያለው ብራና ላይ እንደሆነ አሙን ነው። ሲቃውንቱ ጎንደርንኖ በብ ብራና ማለታቸው ከዚህ ተነሥተው ነው። ብራና ላይ የሠፈሩ ሁሉ ከጎንደር መልክዐ-ምድር ላይ ሰፍረዋል። የጎዛራና የፋሲል ቤተ-መንግሥት ብራና ላይ በምስል ሲኖሩ ጎንደር ላይ ደግሞ መሬት ላይ ተቀምጠው ታሪክ ይናገራሉ። የጎንደርን ክብር ይገልጣሉ። ደርቡሾች ከሁሉ አስቀድመው ጎንደርን ስመደምሰስ የቋመጡትም ለዚህ ነበር ይባላል። ጎንደር ከጠፋች ኢትዮጵያ ምስል ሆና ትቀራለች የሚል እኩይ ጉልስፍና ነበራቸው። ወዲህም ጎንደር የእግዚአብሔር ቤት ናት። ለዚህ ነው "ሰላም ለኪ ጎንደር" ብዬ በቅኔዬ እንደ ቅዱስ ታቦት የውዳሴ አምን ያቀረብኩላት አለ።" ታሪኩ።

ከዚያም

"እንዲያውም በቅርቡ አንገረብ ወንዝ ዳር አንድ አረጋዊ መኖር ጀምረው ነበር። አንገረብ ወንዝ ዳር ቁመው፤

"ዝ ማኅተም ዘዐጤ ፋሲል ሃሌ ሉያ።

ክብብ ብሩህ ዘኢትዮጵያ።" እያሉ ይለፈልፋሉ። ከእኔ በቀር መላ ጎንደር ከአቁብ አልጣሩቸውም። እኔም አንዳንድ ጊዜ ሲቅ ዐፅቁ ይሄን ቃል ሲናገሩት እሰማቸው ስለነበረ ነው። ሌላ ጊዜ ደግሞ "ሰላም ለኪ ጎንደር" እያሉ በመስቀል ምልክት ያማትባሉ። እኔም "ሰላም ለኪ ጎንደር" ስል በቅኔ የገለጥሁት ያ ቃል ገርሞኝ ነው።" አለ ታሪኩ።

PDF Compressor Free Version

"ልጅ ጥሩ ብለኻል። በእውነት የምልህ ነገ ተነገ ወዲያ ታላቁን ባለሻኒ
ክፍለ ዮሐንስ ዘጎንደርን እንደምትተካ ጥርጥር የለኝም። የእኔ የተሰጥ
አባት ድንቁ ጎንደር ሲኖሩ ጎንደር ምን ትመስል እንደነበር ሲተርኩልኝ
ብትሰማ ደሞ ቀሰ በቀሰ ማበድ ይከጅልህ ነበር..." ካሉ በኋላ ተጨሱ...
"አባቱ ድንቁ ከጎጃም ወደ ጎንደር ሲሄዱ ጎንደር ምድረ-በዳ ሆኖ
ለበቀቻቸዉ። በወቅቱ ፋሽስት እንገር እንደነፋው እንዘላ ይፈነጭባት
ነበር። በጣሊያን ቦንብ፣ በባንዳዎች ሴራ፣ ምድረ በዳም ሆና ነበር። ወርቃ
ወራቱ አድባራት በፋጫካ ተወርረው ነበር። ሁሉም ፍልሰልሰ ብሎ
ምስቅልቅሉ ወጥቶ ነበር። ጃን ሆይ ከስደት ተመልሰው ዘፋናቸውን
ተረክበው ጥቂት ቆይተው ጎንደርን ለመጐብኘት ሲመጡ አንዲት ሴት
ሰምልክት ከዐበቅ የለሽ በር ተገናኙ። በጸረ ፋሽስት ጦርነት የኖረው
አርበኛ ሁላ እየመጣ ከሴትዋ ቤት ደጅ ይጠናል። አርበኛው ሁላ
ንጉሡን ደጅ ሊጠና የሚበላው ስንቅ አልነበረውም። አማራጩ ዱቄት
ጭኖ መምጣት ነበረና ከገጠር ዱቄት ጭኖ ይመጣል። አንድ ሴት
ስትገኝ አርበኛው ይሸማታል። እድል የሰጠው ሚስት ያረጋታል። ዱቄት
ጭኖ መጥቶ ያገኛት ስለሆነ ስመ-ም የዱቄት ባል ይባላል። እሷም
የዱቄት ሚስት ትባላለች፤ ያንን ዱቄት እየጋገረች ትሰጠዋለች። ዱቄት
አልቆ ያ ሰው ዱቄት ለማምጣት ወደ ገጠር ሲሄድ ሌላው ገብቶ ሚስት
አድርጎት ይቆያል። አንዳንድ ሴቶች እንዲህ እያሉ ይናሩ ነበር። እናም
ያች ሴት ዐበቅ የለሽ በር ላይ ጠጅ እየጣለች ጠላ እየጠመቀች
የሚመጣውን ዐርበኛ ሁሉ ታስተናግድ ነበር። በሥራዋ እየከበረች
ስትሄድ ሌሎች ሴቶች ተመቅኒተው አንድ በርሜል የጣሊያን ብር ቀብራ

PDF Compressor Free Version

አስተርታለች ብለው ከሻንሆይ ፊት ሰፍርድ አቀረቧት። ሻንሆይ ግን መርምረው ነፃ ነሽ አሏት። ከዚህ ክሰ ነፃ ስትወጣ ጠላቶቿ አየቀዩ ወሞተንቱ ገፋበት። የጠጁን አንዐላ ከምትደፋበት ሰፍራ ዐይጡንና ታሩሱን በወጥመድ ይዘው እባቡን ገድለው አንቡላው ላይ ይደፋባታል። ዝያተኛው በሙሉ ሰካ ዐይጥ ነው የምታጠጣን እያለ አልጠጣም አለ። ሴቲቱ ጠፎ መጣሉን ተታ አንድ ጀግና አግብታ የቤት እመቤት ሆና ቀጠለች። ጎንደርም እየቆየች የጫካ ተራዋን እየተሳጨች እየለማች ፄደች። አርበኛውም ከፊሉ ሹመት ተሰጠው። እንደ እየዐትሙ አውራጃ ፓሼ፣ ወረዳ አስተዳደሪ፣ ምክትልና ሻንበል እየሆነ ተሾመ። በትራ መንግሥት ይጨቡጣል ተብሎ የተገመተው ደግሞ ባልሠራው አበሳ፣ ባላደረገው በደል በሐሰት እየተከሰሰ በገመድ ተሰቀለ፣ በዱላ ተደበደበ። አስገድዶ የሚመጣው ደግሞ ደኛች አርአያ ይባል ነበር። መድኃኔዓለም የሚባል ዱላ ነበረው ይላሉ። በዚያ እየወቃ ያመጣዋል። ራስ አምሩ ተቀብሎ "ስማል" በሚባል ገመድ እያነቀ ይጥለዋል። በወቅቱ የተገጠመ የአንኮርጕሮና የቀቢፀ ተስፋ ግጥም እንደነበረ ድንቁ ነግረውኛል።" ብለው ዐይናቸውን ጨፈኑ። ወዲያውኑ ግጥሙ ሲመጣላቸው ዐይናቸውን ቦግ አድርገው ቀጠሉ።

"አወይ! መከራችን አበሳችን መጣ፤
አምሩ በገመድ አርአያ በቁምጣ።" እያለ ሕዝቡ እያሰቀሰ በአርአያ ዱላ፤ በአምሩ ገመድ ተንጠልጥሎ ይሞት ነበር ሲሉ አባቴ ድንቁ ትዝታቸውን ያወሩ ነበር።" አሉ ሊቱ ከቀለም አባታቸው የለመኑትን ታሪክ ወደ ልጅነት ዘመናቸው ተመልሰው ቃል በቃል እያስታወሱ።

PDF Compressor Free Version

ከዚያም አንባቸው እንደ መስክረም ነጠብጣብ ጀደድ እያስ እየወረደ ቀጠሉ።

"መምህሬ ድንቁ እንዳሉት በወቅቱ በዱር በገደል እየወደቁ ሳህር እየተጋደሉ ሀገር ጠብቀው ያቆዩ ጀግኖች እንደ ጃርት በውጥመድ ገብተው በገመድ ታንቀው አሸለቡ። በተቃራኒው ባንዳዎች ተሸመሩ። ሀገር የሸጡት ወንድማቸውን የገደሉት በያሉበት ተፈልገው በሚሬ ተሸመሩ። በአንገታቸው ኒሻን አጠለቁ። በጀግኖች አንገት ገመድ፣ በጅሎች አንገት ኒሻን ተገደገደ። ፈሪ ለእናቱ ደፋር ለሞቱ ነውና ከጣሊያን ጋር የተዋጉ ደፋሮች እንደጌታ ያለ-አበሳቸው ተሰቀሉ። ፈሪዎች እንደበርካን ተሸመሩ። ይህ ሚሬ ያናደዳቸው አርበኞች አርሰን እንበላሰን ብለው ጎፈሬያቸውን ተላጭተው ወደአርሻ ተመለሱ። ሞቱም ሹመቱም ቀረባቸው። ጎንደር ከመልካም ገጽታዋ ጎን ለጎን እንዲህ ያለ አሰ-ይ ሚሬ የተፈራረቀበት የሊቃውንት ሀገር ጭምር ናት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እኔም በደንብ አውቃታለሁ። ጎንደር የጀግኖች ሀገር ናት። የጎበዞች አድባር ናት። ዝቅ ብለህ ደረሰኔ ዝለቅማ! የጀግኖች ታሪክ አፍ አውጥቶ ይመስክራል። በእርግጥ የቀለም አባቱ ድንቁ እንዳሉት ድሮ ጎንደርን ጨምሮ መላ ጠቢያ ከሥልጣኔ በኩል ጎላ ቀር ነበረች። ይኸውም ሲታወቅ ገበሬ እኽል አምርቶ ከምርቱ አይቀምስም ነበር አሉ። እኽሉ በንጉሥ እጅ ብቻ ተይዞ ይኖር ነበር። እኽሉ ሲደርስ ሽም ተቆጣጥሮ አውድማው ታይቶ ምርቱ ተገምቶ ይህንን ያኽል ቁና ትከፍላለህ ተብሎ ሳይነገረው ዘርቶ ካበቀለው እኽል አይቀምስም ነበር ይባላል። ጎላ ግን ጃንሆይ ከስደት ሲመለሱ ገበሬ ከነፋስ ጋር ተጋፍሎ እንዲበላ በየጉለቱ።

PDF Compressor Free Version

የቀደመው ሥራት ፈረሰ። ወርኃዊ ደመወዝ ተጀመረ። ጭቃ ሹም አየሽሙ ግብር ማስገበር ጀመሩ። ሕዝቡ የሚጉበረው ብር ስላልነበረው እርስ በርሱ ተላቀሰ። ልጆቻችንን ስፈረንጅ ለመሸጥ እንዲመቻቸው ግብሩን በብር አደረጉብን ብሎ ባለማወቅ ማንጎራጎር ያዘ። የዚህ ዋና ተቃዋሚ የጃንሆይ የነፍስ አባት ጭምር ነበሩ። ጎንደር ውስጥ እማማ ከምትባል ገዳም ውስጥ ይኖሩ ነበር አሉ። ንጉሠ ነገሥቱ ሲሰደዱ መንነው እማማ ገዳም ገቡ። ሲመለሱ ወደ ቤተ መንግሥት ይምጡ ብለው ላኩባቸው። ከምናኔ በኋላ ስምን? ብለው እምቢ አሉ። ይህን ሁሉ ዝባዝንኬ የምተርክልህ በከንቱ አይደለም። የሀገር ታሪክ ስለሆነ ነው። ታላቋ ጎንደር ግን ለዘላለም ታላቅ ናት። በቅርብ ጊዜ ደግሞ ጎንደር ውስጥ በልባቸው የሚሳቡ በእግራቸው የሚሽከረከሩ በክንፋቸው የሚበሩ የውጪ ሀገር አሞሮች እየታዩ ነው ይባላል። ያችን በቀደም ያነሳሁልህን ነገር ጎሠሣው ደርቷል እየተባለ ነው። ወደፊት ግን የጠቢባንም መንደር ብቻ ሆና ትቀጥላላች።" ብለው "በል! በል! ቅኔውን አምጣው።" አሉ።

ታሪኩ የዐራራይ ዜማ የሊቃውንት ሀገር፤

የምሥጢር እመቤት ሰላም ለኪ ጎንደር

ስምሽ የተጻፈው በሕይወት ውኃ ሥር" ብሎ ድጋሜ ቅኔዋን ነገራቸው።

"በነገው ጉባኤ የተሻለ መወድስ ጨምረህ -ና" አሉ ሊቁ።

"ቃለ ሕይወት ያሰማልኝ የኔታ! እርስም ስለ ጎንደር የነገሩኝም ማለፊያ ታሪክ ነው። አሁን ማታ ተማሪው ጭል ሲልልኝ ኩራዝ አብርቼ

PDF Compressor Free Version

እጽፈዋለሁ።" ብሎ ጉልበት ስሞ ተሰናበተ። ሁለተኛው ዘራፊ ሞራው
ገዱን እያሸሸ ተተካ።

PDF Compressor Free Version

ለቋ ፋራስ ጥጋብ የራሳቸው ይመስላል። ሆዳቸውን ቱሉ ቱሉ ይዳብሳሉ። ዐይናቸውም ጉም እየመሰለ ነው። ቢሆንም ማስተማሩን ከነፍሳቸው በላይ ይወዱታል። እንዲያውም ሳያስተማሩ ከዋሉ ያማቸዋል። ጥሩ ስሜት አይሰማቸውም። የዕለት ራታቸው ማስተማር፣የዓመት ልብሳቸው ከዘራፊዎች ቅኔ መስማት ነው። ታሪኩ ቅኔ ዘርፎ እንዳበቃ ገሞራው ተተካ። ፊት ለፊት እንደቆመ "ቀጥል!" አሉ ሊቁ።

"ማየ ሠማርያ መሪረ እንዘ ይፈጥር ፈጣሪ
ማየ ጥበባት ፈጠረ በዲማ ለሠረገላ ወዶሪ።" አለ ገሞራው።

ሊቁ በብሩህ ገጽ ተቀብለው "ፍታው" አሉ።

"..የሰማርያን መንዝ ሲፈጥር ፈጣሪ፤
አረጋት መራራ አረጋት ቅራሪ፤
የዲማን ውኃ ግን አረጋት ኮርኳሪ፤
ጥበብ እንዲቀስሙ ብርሃንና ዶራ.."

አለ ገሞራው ግእዙን ወደ አማርኛ ሲተረጉም።

"ደግሞ ዛሬ እንደ ክፉ ጋኔን ውኃ ለውኃ መዛር ጀመርክ። እስኪ በደንብ አፍታታው። የዲማ ውኃ፣ የሰማርያ ውኃ የምትለው ዝባዝንኬ ምን እንደሆነ ውስጤን አልነካውም?" አሉ ሊቁ።

ገሞራው ቀጠለ።

"በሰማርያ ውኃ በኩል ብዙ ማለት አልፈልግም። ያው የሰማርያ ውኃ መራራ እንደነበር በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል።

PDF Compressor Free Version

የዲማ ጊዮርጊስ ውኃ ግን የተለየ የአፈጣጠር ምሥጢር ሳይኖረው አይቀርም። በምሥራቅ ጎጃም የሚገኘው ዲማ ጊዮርጊስ በዐራቱ ማዕዘን በአፍላጋት የተከበበ ቅዱስ ሥፍራ ነው። ደብሳ ማለት መንበረ ሥላሴ ማለት ሲሆን ጥበብ የሚመነጨው አናላ እንደሆነ ደግሞም ፈለጥ ጥበባትናት። ከፈለገ ጥበብነቱ በተጨማሪ በዐይነ ሥጋ የሚታዩ አፍላጋቱ ከዐሥር አያንሱም። ዘጠኙ በዘጠኙ የዲማ ቅዱሳን ነው ተሰይመው መካነ-ጠበል ሆነዋል። ዐሥረኛዋ ምንጭ ግን ዝም ብላ ምንጭ ብቻ አይደለችም። ከዐለት ላይ የምትንበለበል ምሥጢራዊት ምንጭ ናት።" አለ በቅኔው ውስጥ እንደዋሃ በሰደራቸው የቅኔ ዘይቤዎች ተመርኩዞ ሀገራዊ ምሥጢራትን ሲዘክዝክ፤

"እሀ?" አሉ ሊቁ በአንክሮ እያደመጡ።

ገሞራው በውስጡ ያረገዘው ምሥጢር ፈንቅሎት ሊወጣ ምንም አልቀረው። ስለ ምንጯ ዲማ ሲማር ፍንጭ ሰምቶ ነበር። ቢሆንም ያኔ በልጅነት መንፈስ ልብ-ብሎ የመዘገበው ብዙ ነገር አልነበረም። ጊዜ ሲሰወጥ ዘመናት ሲፈራረቁ ትውልዱ በአባቶቹ ፍልስፍና ማመን ሲሳነው ገሞራው ከትውልዱ በተቃራኒ ቆመ።

ዐጥንቱ እየበሰለ እንደአባቱ ጢም እያወጣ ሲመጣ ድጋሜ ወደልጅነቱ ዘመን እየተመለሰ መመርመር ጀምሯል። ድሮ የዋኘባቸው አፍላጋት በመሉ በውስጣቸው ጎቡአ ነገር እንዳላቸው እየተጠራጠረ መጣ።

"እናስ?" አሉ ሊቁ ፋሬስ የምንጯን ምሥጢር ጨርሰው ለመስማት እየጓጉ።

PDF Compressor Free Version

"ይቺንን መናጢ ምንጭ ለማፈላለግ ኑዮንት አሰከ ዛሬ ብዙ ሊቃውንት ደክመዋል። የጥንቶቹን ከርስም ብረዳ ይሻላል።" ብሎ ዝም አለ።

ሊቁ ፋራስ ብስለቱ ድንቅ ብሏቸው ገሞራውን በደንብ ተመለከቱት። ወይኖቹ በርበራ የተረጨ መስለው በደም ተሰርፀዋል። አንገቱ ሳይ ብ.ን ብ.ጉን የምትለዋ ሐብል ትበረቀረቃለች።

ከዚያም ሊቁ ቀጠሉ።

"ዝቅኔው እንዳንሣኸው ይህ ጉዳይ ጥንት ጀምሮ የሚነገር ምሥጢር ነው" አሉ ሊቁ ፋራስ ሐሳቡን ከገሞራው ወደራሳቸው መልሰው።

"ጥንት ጀምሮ ሊቃውንቱ ዲማ ጊዮርጊስን ደጅ ይጠኑ እንደነበር ግልጥ ነው። ዲማ የቅኔ፣ የዜማ ያቋቋም ሀገር ነበር። ዛሬም ጭምር ያው ነው። አትሮንሱ አልታጠፈም። ብራናው እንደተከፈተ ነው። አንባቢ ይፈልጋል። ተመራማሪ ይሻል። ባለቅኔው ሠረገላ ብርሃንና ዶሪ የቅኔ ፈጣሪም ወደዲማ የሄዱት ቁልቁል ናፍቷቸው አይደለም። ያች መናጢ ምንጭ ናት የሳበቻቸው። በትኔው ሰምና ወርቅ 'ሠረገላ ብርሃንና ዶሪ የቅኔ ፈጣሪ'ን ተራ በተራ ስትሰድራቸው ስለማ ነገሩ ወደዚህ እንደወሰደኽ ምሥጢሩ ቶሎ ብልጭ አለልኝ።" አሉ።

ንሺ" የኔታዬ አለ ገሞራው።

"አዎ ሁለቱም የቅኔ ሰዎች ናቸው። ሠረገላ ብርሃን በእምዬ ምኒልክ ዘመን የነበረ በራስ ኃይሉ ፊት ቅኔ በመዝረፍ የሚታወቅ ሊቅ ነው። የቅኔ ባለሙያ ሊቀ-ሊቃውንት ነው። ዐይነ-ስዉር ሆኖ በዲማ ጊዮርጊስ ዘመናትን አሳልፏል። በመወድሱም የጎጃምን ሊቃውንት አስደምሟል። የዋሸራንና የሞጣን ባለቅኔዎች አስደንግጧል። ይህንን መደንግፅነት

PDF Compressor Free Version

የሰጠችው ግን ይች ምንጭ እንደሆነች ይገመታል። በአርግጥ ግምት ነው። ከዚያ በፊት ምንጯን አግኝቶ ለመጠጣት ግን ብዙ ዓመታት ደክሞ ነበር። ቁልቋል ለቁልቋል እንደሸሸብ እየተሰለለለለ ብዙ ጊዜ ፈሰሰ አጣት። መፍትሔው በመምህሩ እጅ እንዳለ ሲሰማ መምህሩ ተጠምቀን ደጅ መጥናት ያዘ። ድካሙ አሳዝኗቸው አምጥተው ምንጯን ጋቱት። አልም ያለ ባለ ቅኔ ሆነ። በኢትዮጵያ አሱን የሚተካከል ባሉቅኔ ነፍሩ። በእሱ ተደም ብሎ በቅኔው ይመሰገን የነበረው ጉዱ ካሳ ነበር። ጉዱ ካሳን ሠረገላ ብርሃን በቅኔ ሊፎካከሩ ቅኔ ዘረፋ ንጠሙ። ሠረገላ ብርሃን ዐሥር መዐድሰኝን ሲዘርፍ ጉዱ ካሣ ሁለት ብቻ ዘረፈ። እሱውንም በጭንቅ ነው።

"ቅኔው ምን ነበር?" አለ ንሞራው።

"እንዴት ነበር አያ! ቅኔው?" አሉ ሊቁ ፋሬስ ዐይኖቻቸውን በተቀነደ ሞርነ ጣራ ላይ እያንከላለሉ።

ከዚያም ዞሉ መጣላቸውና

"ቅኔው የመወድስ ጫፍ ሲሆን

'በእልኤ ጊጋይ ቃለ-መወድስ።

አክአብ ጉዱ ካሣ እስከ ማዕዜኑ ተሐነክስ።" ተብሎ ነው የተዘረፈበት። በዚህ ጊዜ በጉዱ ካሣ ተሳቀበት። ለሠረገላ ብርሃን ተጨበጨለት። ከዚህ ቀን ጀምሮ ከሠረገላ ፊት የማቆም የቅኔ ሰው ጠፋ። በወቅቱ መምህሩ ተጠምቆ ትምህርት የሚገልጥ ፍቱን መድኃኒት ሰጥተውት ነው ተብሎ በሀገር ተወራ። ዛሬ ላይ ቆም ተብሎ ሲፈተሽ ግን የሠረገላ ቅኔ ከምንጯ የተቀዳ እንደሆነ ተረጋገጠ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

PDF Compressor Free Version

"እኔም የአፌ ታሪኩን ጭራ ይገፍ "ውኃሞን ለመፈለግ ብዙ ደክሜ ነበር። ሰባሌ ጭምር ንብቼ ፈለግኋት። ነገር ግን ላገኛት አልቻልሁም። ዛሬስ ቢሆን መኖሯ ምን ያክል ይታመናል?" አለ ገሞራው ተመልሶ ዲማ ጊዮርጊስ ለመሄድ እያሰበ። በእርግጥ ገሞራው ተመልሶ ዲማ ጊዮርጊስ የሚሄድበት ሌላም ምሥጢር አለው። ወደዲማ ተመልሶ "ዝሙ ታእምሮ" ያለበትን ምጡቅ አቡሻክር መመርመር ይፈልጋል። ቶሎ እንዳይመሰስ ደግሞ በጎንጅ ደብረ-ጥበብ ያለችዋ ታብር ወደኋላ ትስበዋለች። አርፎ የማል ሕይወቱን እንዳይኖር እኒህ ሐሳቦች ከአውላላ ሜዳ ላይ ጥለው ይረግጡታል። በዚያ ላይ ወደፊት ደራሲ ለመሆን ይመኛል። ይህ ደግሞ ሐዲስ እጣ ፈንታ ነው። ሊተወው የማይችል የሕይወቱ ክፋይ ይመስለዋል። ደራሲነት ከባድ እዳ እንደሆነ ቢገባውም ገሞራው ታግሎ ሊወድቅ ወይም ሊጥለው ይፈልጋል።

"መኖሯ ይታመናል። መገኘቷ ግን እንዳልኸው ያጠራጠራል።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ለጥያቄው ሲመልሱ።

"እንዴት?" አለ ገሞራው።

"እንዴትማ! ቀደምት አባቶች እንደሚሉት መገኘቷ ከዓመት አንድ ቀን ብቻ ነው!" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"እንዴት እንዴት?" አለ ገሞራው በድጋሜ ተገርሞ ከወገቡ ጎብደድ ብሎ አንገቱን ወደሊቁ እያሰገገ።

"ልጅ እያለን ምን እንሠራ ነበር መሰለኽ" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ምን ትሠሩ ነበር" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

"ጳጉሜን ስትብት አቡሻክር ማጥናት እንጀምራለን። ለሁለት ቀን ያክል አቡሻክር ስናጠና እናሳልፍና በሦስተኛው ቀን ወንዝ ወርደን እንትልፍ እንጻይጥለን ፊታችንን በውኃ አያረጠብን ከወንዙ ዳር እንሰፍራለን።" አሉ ሊቁ።

"ለምን?" ገሞራው እየሳቀ ጠየቀ። ሲሰቅ እንባ ቀደመው። ምስኪኑ ገሞራው እንዲህ ነው። በደንብ ሰቆ ቀርቶ ገና ሲሰቅ ሲያስብ በዐይኑ እንባ ዝርግፍ ይልበታል። እንባውን እያበሰ ሰቆ ይጨርሳል።

"ጳጉሜ የተለየች ወር ናት። ባላገሩ ባለ አምስት ቀኗ ጳጉሜ ከሠላሳ ቀን አኩል ናት። አንድ አዝል በሠላሳ ቀን የሚያገኘውን ምግብና በአምስቷ ቀን ጳጉሜ ያገኘዋል።" ሲል ያሚርታል።

ጠቢባንም አድሜ እንዲረዝምላቸው በጳጉሜ ወር ሱባኤ ይገባሉ። ባለትኔዎች ደሞ በጳጉሜ ወራጁ ውኃ ድንገት ጸጥ ብሎ ሰትጽበት ይቆማል። ያን ጊዜ ከውኃው የቀመሰ ሊት ይሆናል እያሉ ወንዝ ዳር ያድሩ ነበር። ይህንን ጨዋታ እኔም ተጫውቸዋለሁ። ልጅ እያለሁ በዚህ ቀን ወንዝ ዳር አድር ነበር" ብለው ፈገግ አሉ።

ከዚያም "የሆነው ሆኖ ብሒሉ ለአንዳንዶች ባጋጣሚ ሠር:ቷል።" አሉ ሲቀ ሩፊስ።

"እንዴት ሠራ?" አለ ገሞራው።

"ይች ምንጭ የተገኘችው በዚህ አጋጣሚ ነው" አሉ ሊቁ።

"እንዴት" አለ ደቀመዝሙሩ።

PDF Compressor Free Version

ነው በተለመደው ብሂል የአለቃ ተጠምቆ ተማሪዎች በጓጉ ወር ወደውንዝ ወረዱ። እነሱ ወራጁ ወንዝ እስኪቆም ሲጠባበቁ ድንገት አንድ ነገር ተከሠተ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ።

"ምን ተከሠተ" አለ ገሞራው።

"ዝሀህ ሌሊት አንድ ሰው በልቡ እየተሳበ እየተሳበ ወደ ቁልቋሉ ውስጥ ገባ። የተጠመቆ ተማሪዎች ተከተሉት። ሰውየው ከሁሉቱ ቁልቋል ውስጥ አንዱን አልፋ ዋሻ በር በስተቀኝ በኩል ውኃ በቅምጫና ቀድቶ ጠጥቶ ወደ ዋሻ ጊዮርጊስ ሲሸበለል የቅኔ ተማሪዎች ወደ ምንጯ ተጠጉ። ምንም ምንጯ ነገር አላገኙም። ተመልሰው መጥተው ስተጠመቆ ነገሯቸው። አለቃ ተጠምቆ ግን እንደ ተማሪዎች ምንጯን ሳይሆን ሰውየውን ማፈላለግ ጀመሩ። አገኙት። ምሥጢሩን ነገራቸው። አደረጉት። ሊቀ-ሊቃውንት ሆኑ።" አሉ ሊቁ ፋሬስ ድንቁ።

"ታዲያ ዛሬ ምን ዋጣት?" አለ ገሞራው ከቆመበት ዐሰት ላይ እንደመንቀሳቀስ ብሉ።

"መዋጥማ ምን ይውጣታል? የምሥጢሩ ባለቤቶች ሲያልቁ ምሥጢር የሚነግረን ሊቅ አጥተን እንጂ ደግሞ ምን ይውጣታል?" አሉ ሊቁ ፋሬስ ትካዜ ገጻቸው ላይ እየተነበበ።

"ነቅዑ ቢጠፋ ቦታው ላይጠፋ ይችላል። ለመሆኑ በየት በኩል ነበር የነበረችው? የዲማ አፍላጋትክ ብዙ ናቸው?" አለ ገሞራው።

"በምዕራብ ነዋ! እሱማ መቼ ጠፋብን። ከዲማ ደብር ወደምዕራብ ስትመጣ ብዙ አፍላጋት አሉ።

PDF Compressor Free Version

መጀመሪያው ማሞ ምንጭ ናት። ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ስትንፎለፎል ታገኛታለህ። ለዮቃ ከዐሉቱ ላይ የምትፈልቀዋ ምንጭ ናት። ገበራው 'ማይ' እያለ ይጠራታል።

ማሞ ምንጭ ከከረምት እስከ በጋ አትደርቅም። የመጽሐፍ ተማሪዎች እየቀዱ ይጠጧታል። የቅኔ ተማሪዎች ቅኔ ይዘርፉባታል። የፊደል ተማሪዎች ደግሞ ይራጩባታል። ይችኛዋ ግን በጳጉሜ ብቻ ወጥታ ባዙ ምሥጢር ትከሥታለች። ዙሪያዋ በገደል የተከበበ ነው። ከራስጌዋ በተሰምዶ ሰይጣን ምንጭ የሚባል ጥቁር ባሕር አለ። ነቅዑ ከሲያጣ ባሕር ዝቅ ብሎ እንደነበር ይነገራል። እንግዲህ ያች ናት ለሠረገላ ብርሃን የቅኔ ፍቱን መድኃኒቱ። ይች ምንጭ ናት የአበው ጎቡኣ ምሥጢር። እያለች ያላየናት፣ ጥበብ እየጠማን ያልጠጣናት። ሠረገላ ብርሃን ከዚች የጠጣ ቀን መኖ መወድስ ዘረፈ ይባላል። ስመ በሀገር ንነን። ዐይነ ሥውሩ እየተመራ መጥቶ በሀገር የታወቀ ሊቅ ሆነ። በጎጃም ሊቃውንት ዘንዳ አልቦ ሊቅ ዘስማሁ ተብሎ ተወደሰ። ኃላም ወደትውልድ ሀገሩ ተመልሶ ቅኔውን ሲያወርደው የላስታ ሊቃውንት ታቦት አውጥተው በክበሮና በወረብ ተቀበሉት። በሀገሩ ቅኔ-ቤትሠርቶ እያስተማረ ሲኖር ብዙ ሊቃውንት ፈለጉን ለመከተል ፈለገ። ከእኒህ ተፎካከሪ ሊቃውንት አንዱ ዶራ ነበሩ።" ብለው በከዘራቸው መሬቱን ጫር ጫር እያረጉ ምሥጢሩን ጥቂት አሰላሰሉ።

ከዚያም "ስለ ዶሪስ ምን ታውቃለህ?" አሉ ሊቁ። ከሠረገላ ብርሃን እስከ ዶራ ያጠኑቱን የሊቃውንት ታሪክ እንደስንክሳር በረጅሙ እየዘከዘኩ። "ምንም አላወቅሁም" አለ ገሞራው።

PDF Compressor Free Version

"ከሰማይ ሲቃ እየተባለ ስለእነዚህ ዐራት ዐይና ሲታውንት አስማውቁ አደሳፈረጪ። ስለዚህማ ማወቅ ግድ ነው። ዶሪ የቅኔ ፈጣሪ። ዶሪ የቅኔ ሊቅ ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት "ዶሪ የቅኔ ፈጣሪ" እየተባለ ሀገር ሀገር ስሙ ይናኝ ነበር። ዘመኑም የሩቅ ሰው አያደለም። ከተዋነይ ወዲህ ነው" ብለው ትንሽ ዜማ ቢጤ ቃኙ። ዜማው ውስጥ የትዝታ ዜማ ተሰረቀረቀ። ተዋነይ ትዝ ብሏቸው ነው።

ገሞራው ዶሪ በምንኛ ቋንቋ እንደሆነ ቢያስብ ቢያስብ አጣው።

በዚህ ሐሳብ ውስጥ እንዳለ

"ሰማይ ምድርን የፈጠረ ማን ነው?" አሉ ሊቁ ፋሬስ ወደ ገሞራው እየተመለከቱ።

"ክቡታ በቀር ሌላ ማን ይፈጥራቸዋል። እስካሁን እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን እኔ ፈጠርኋቸው አላለም። መጽሐፉም በቀዳማ ገብረ እግዚአብሔር ሲል በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን እንደፈጠረ ተናግሯል።"

"ይኸውና!" አሉ ሊቁ ነጭ ጭራቸውን ወደተዋነይ ዋርካ ሸው አርገው። "ይኸውና! ቅኔን ደግሞ አሳምሮ የፈጠረው ዶሪ ነው። "ዶሪ የቅኔ ፈጣሪ" ተብሎበታል። ዶሪ ማለት የቅኔ አምላክ እንደማለት ነው። ቅዱስ ያሬድ የጀመረውን ተዋነይ በቀመር ቀመረው። ከተዋነይ ቀጥሎ ዶሪ ተፈላሰፈበት። የቅኔ ፈጣሪ ሆኖ ብቅ አለ። ሊታውንቱ ስለ ቅኔው ምሥጢር ተደንቀው ዶሪ የቅኔ ፈጣሪ ብለው አሞካሹት። የዶሪ ታሪክ በክፈልም ቢሆን በብራና ውስጥ ሠፍሯል፡ ፈልገህ አንብበው። ለእኔ

PDF Compressor Free Version

ከማዕበል ጋር በቅኔ የተሞሻለቁበት ታሪክ ብቻ ነው ትዝ የሚሉኝ አሉ።

"እሱ እንዴት ነበር?" አሰ ገሞራው።

ሊቁ ቀጠሉ።

"ዶሪ ከትግራይ መጥቶ በዚህ ጎንጅ ጽላሎ የቅኔውን መንገድ ይቀጥል ነበር። ማዕበልና ዶሪ ባንድ ወቅት ክብረ-በዓል ላይ ተገናኙ። ማዕበል አባሳሰሁ 'የቅኔው ማዕበል ይሉኻል እኔ ነኝ' አሰ ማዕበል።

"እኔም ዶሪ እባለሳሁ። የቅኔዉ ፈጣሪ እኔ ነኝ" ተባብለው ተዋወቁ። ከዚያም 'እስኪ በዚህ አጋጣሚ -ና- ቅኔ ዘረፋ እንግጠም?" አሰ ማዕበል። "ምን ገዶኝ ና ይዋጣልን" አለ ዶሪ የቅኔው ፈጣሪ። ተፎካከረው በቅኔ ዘረፋ ተሞሻለቁ። ሁለቱም በሊቃውንቱ ፊት እየተንጎራደዱ ቅኔ ሲዘርፉ ማዕበል መቶ ሐምሳ፣ ዶሪ ሐምሳ መወድሶች ዘረፉ። በቅኔ ዘረፋው ላይ ማዕበል ዶሪን ዘረረው። እንደተዘረረ ሲገባው የቅኔው ጥልቀት ይመርመር ወደሚል ሐሳብ መጣ። ማዕበልም በሐሳቡ ተስማሙ። በሊቃውንት ፊት ቀርበ የሁለቱ ቅኔ ቢመዘን በጥራት እኩል ሆነ። ስማዕበል ሐምሳው ሲቀር መቶው ቅኔ ገለባ ነው ተብሎ በሊቃውንት ተፈረደባቸው። ሁለቱ ሊቃውንት በሐምሳ በአምሳው ቅኔ እውቀታቸው ተመጣጠነ። ይህ ፍትሕ በሊቃውንቱ እንደ ተሰጠ ዶሪ ማዕበልን ስማመሰገን ፈልጎ።

"ማዕበል ቅኔህ ለእመ ገፍዐኒ።

ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ።" ሲል በቅኔው ማዕበልን አወደሰ።

PDF Compression Free Version

ይህን ሁሉ የምለፈልፈው የሚያጣጥማቸው አንድ ምሥጢር መኖሩን ለመንገር ነው።

"ምን አሉ አለ?" አለ ገሞራው።

"ደረን የቅኔ ፈላሪ ማዕበልን ማዕበል ያደረገቻቸው ያች የዲማዋ ተአምረኛ ምንጭ ናት ይባላል። በእርግጥ ዲማ ውስጥ ሌላ የምሥጢር አፍላጋት አሉ። ዐሥረኛዋን የቅኔ ፈለግ አነሣን እንጂ ያች በአቡነ ሠረቀ ብርሃንም ስም የምትጠራዋ ምንጭምክ ተአምረኛ ምንጭ ናት። ባሳገሩ ሠርቃ ብሎ ይጠራታል።" አሉ ሊቁ።

"ደግሞ እሷ ምን ታምር ትሠራለች?" አለ ገሞራው በድጋሜ ከሊቁ እንደበት አዲስ ነገር እየጠበቀ፤

"ሠረቀ ብርሃን ምንጭ ከዘጠኙ የዲማ ቅዱሳን በአንዱ በጻድቁ በሠርቀ ብርሃን ስም ትሰየም እንጂ የተለየ ምሥጢር ቢጤ አላት። ድሮ የአኽያ እሾክ ከብቧት ስንመለከታት የቆዳ መንከሪያ ትመስለንና ከቁብ አንቆጥራትም ነበር። የውኃ መጠኗ በጣም ትንሽ ነው። በተቃራኒው ክረምት ክረምት ትቀንሳለች። በጋ በጋ እንደ ገና ምላቷ ይጨምራል። ሲጠሟት እንደ ቅል ትመርራለች። ከሰውነት ጋር ስትወሐድ በመርፌ እንደተወሰደ መድኃኒት በዐሥራ ሁለት አካላት ትሠራጭና ሰውነት ትበዘብዛለች። ፍቱን መድኃኒትነቷ የሚጀምረው ከዚህ ጀምሮ ነው።" አሉ ሊቁ በሚጣፍጥ አንደበታቸው።

"እንዴት የኔታ?" አለ ገሞራው።

"ይህ መድኃኒትነቷ ከአስማት ወይም ከመተት የመጣ አይደለም። ቀድሞውኑ የሰይጣን መተት የጠንቋይ ድግምት ለሰው ልጅ ጠቃሚ

PDF Compressor Free Version

አባቶቹ አላስተማሩኝም። እኔም አላምንም። ወዲህም አላስተምርም። እናም ወደውታ ስንመጣ የሠርቃ መራራነቷ የተፈጥሮ ጠባይዋ ነው። በደም ሥር እየገባች እንደመድኃኒት መቆጠሯ ግን አሁን ድረስ አልገባኝም። ብቻ የአስኳላ ትምህርት ወደ ሀገራችን በገባ ወቅት የአስኳላ ተማሪዎች ሲራኮቱባት እመለከት ነበር።" አሉ ሊቁ።

"ለምን?" አለ ገሞራው።

"በዚያን ዘመን ብሒል የትምህርት መድኃኒት ናት ተብላ ትታመን ነበር። በፈተና ሳምንት የአስኳላ ተማሪ እየመጣ ይጠጣታል። አሷን ተንጭቶ ለፈተና የተቀመጠ ተማሪ የፈተና ነገር አያስጨንቀውም። በጥሶት ያልፋል። ነገር ግን ይህንን ምሥጢር የሚያውቁ አዲማ ተወላጆችም በክፈል ነው። እንዲያውም በቅኔ ነገሩን ያመጣኸው አንተ ነህ።

"ማየ ሠማርያ መሪረ እንዘ ይፈጥር ፈጣሪ
ማየ ጥበባት ፈጠረ በዲማ ለሠረገላ ወዶሪ" የምትለው ምን ለማለት ፈልገህ ነው?" አሉ ሊቁ።

"እርስዎ ካሉት የተለየ ምሥጢር የለኝም።"

"ሠረገላ ብርሃንና ዶሪ የቅኔ ሊቅነታቸው መረሳት የለበትም። ምንጪ ደሞ በጥበባዊ መንገድ ብትጠና መልካም ነው ለማለት ነው።" አለ ገሞራው።

"እመሰ አማን ጽድቀ ትነቡ" አለ ዳዊት። "ተማራማሪ ሊቅ ካገኘህስ ጥሩ ብለህ ነበር። በል! በል! ብዙ አታስወሽከተኝ ወደቅኔው እንግባ። ቅኔውን

PDF Compressor Free Version

መለሰው" አሉ ቡተሰመደው አንደበታቸው። ገሞራው ቅኔውን ጨርሶ
እጅ ነሥቶ ወደ መወድስ ገሠገሠ።